አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሴቶች ብቻቸውን እና ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ በሚማሩባቸው የግል ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ንጽጽራዊ ጥናት

በ

ለዘር አሌ

2004 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሴቶች ብቻቸውን እና ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ በሚማሩባቸው የግል ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ንጽጽራዊ ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለ በተግባራዊ ሥነ ልሣን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ለዘር አሌ

2004 ዓ.ም.

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሴቶች ብቻቸውን እና ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ በሚማሩባቸው የግል ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ንጽጽራዊ ጥናት

በ


ለዘር አሌ


2004 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

| አማካሪ ስም | ፊርማ |
| --- | --- |
| ___________ | ___________ |
| ___________ | ___________ |

| ፈታኝ ስም | ፊርማ |
| --- | --- |
| ___________ | ___________ |
| ___________ | ___________ |

# ምስጋና

ከሁሉም አስቀድሞ ለዚህ ያደረሰኝ አምላክ ምስጋና ይግባው፡፡ ከጥናቱ ርዕስ መረጣ ጀምሮ ጥናቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ደከመኝና ሰለቸኝ ሳይሉ ከፍተኛ ሙያዊ ድጋፍና ምክር በመለገስ ጥናታዊ ፅሁፉ አሁን የያዘውን ቅርፅ እንዲያገኝ ላደረጉት መምህሬና አማካሪዬ ለአቶ ጌታቸው እንዳለማው (ረዳት ፕሮፌሰር) ምስጋናየ ከፍ ያለ ነው፡፡

ለጥናቱ መረጃ በመሰብሰብ ወቅት የክፍል ውስጥ ምልከታውና የቪዲዮ ቀረጻው የተሳካ እንዲሆን ለማድረግ ውድ ጊዜዋን በመስጠት በገንዘብ ትብብር ላበረከተችልኝ ለህልፍቲ ተካ እንዲሁም የቪዲዮ ካሜራ ላዋሰኝ ለዶ/ር ጥላሁን አበባው ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡ መረጃውን ለመሰብሰብ ትብብር ላደረጉልኝ የልደታ ማርያም ልጃገረዶችና የልደታ ማርያም የወንዶች ትምህት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ የአስተዳደር ሰራተኞች እና በስራ ቦታየ ያለውን ክፍተት በመሙላት ከባድ የሆነ ሀላፊነት በመውሰድ ከፍተኛ ትብብር ላደረጉልኝ ለአቶ ተሾመ ማንደፍሮ እና ለወ/ሮ ወይንሸት በየነ ከፍተኛ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

ትምህርቴን እስካጠናቅቅ በገንዘብና በማቴሪያል እገዛ ከጎኔ ለነበርከው ለባለቤቴ ለአቶ አበራ ተመስገን፣ እንዲሁም ጊዜ በማጣት ፍቅርና እንክብካቤ ላጓደልኩብህ ልጄ ሚካኤል አበራ ለትእግስታችሁ እና ለትብብራቸሁ ብድር መላሽ ያድርገኝ፣ በትምህርት በነበርኩበት ወቅትም ለልጄ ፍቅርና እንክብካቤ በመስጠት ከጎኔ ለነበራችሁት ለትዕግስት፣ ለዲያና፣ ለሩት፣ ለቤዛና ለአበራ ትልቁን ስራ ሸፍናችሁልኛልና በጣም አመሰግናለሁ፡፡

የጽሑፉን ረቂቅ በማንበብና በማረም እንዲሁም በመጻፍ አስፈላጊውን ማበረታቻ በመስጠትና የማቴሪያል ድጋፍ በማድረግ ለተባበራችሁኝ ለበላይ ሰይድ፣ ለህልፍቲ ተካ፣ ለአበራ ተመስገን ለወይንሸት በየነ፣ ለወይሸት አሸናፊ፣ ለሰላም አረጋ እና ለቅድስት ታምራት፣ ለጽጌ አበራ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

የከበደኝን ነገር በማማከር ትምህርቴን ለመጨረስ እችል ዘንድ ከፍተኛ የሆነ የስነልቦና እርዳታ ላደረጋችሁልኝ ለአቶ አስማማው ሀይሉ፣ ለአቶ ሀይለመለኮት መዋእልና ለአቶ ጌታቸው እንዳላማው ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ

**አርዕስት** **ገፅ**


ምስጋና ..................................................... i

ማውጫ ..................................................... ii

የሰንጠረዥ ማውጫ ..................................................... v

አጠቃሎ ..................................................... vi

**ምዕራፍ አንድ** ..................................................... 1

1. መግቢያ ..................................................... 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ..................................................... 1

1.2 የጥናቱ አላማ ..................................................... 4

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ..................................................... 4

1.4. የጥናቱ ወሰን ..................................................... 5

**ምዕራፍ ሁለት** ..................................................... 6

2. ክለሳ ድርሳን ..................................................... 6

2.1 ተራክቦ ምንድን ነው? ..................................................... 6

2.2 ተራክቦ በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ..................................................... 6

2.3 ተራክቦን በመጠቀም ቋንቋን ማስተማር ያለው ጠቀሜታ ..................................................... 7

2.4 በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ምክንያቶች ..................................................... 8

2.4.1 በመማሪያ ክፍል ተሳትፎ ላይ የጾታ ልዩነት የሚያስከትለው ተጽዕኖ ..................................................... 8

2.4.2 መምህራን ለሴቶችና ለወንዶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረት መለያየት ..................................................... 10

2.4.3 ሴቶች ብቻቸውን መማራቸው እና ከወንዶች ጋር አብረው መማራቸው ከተሳትፏቸው ጋር ያለው ግንኙነት ..................................................... 15

2.4.3.1 ሴቶች ብቻቸውን መማራቸው ከተሳትፏቸው ጋር ያለው ግንኙነት ..................................................... 15

2.4.3.2 ሴቶች ከወንዶች ጋር አብረው መማራቸው ከተሳትፏቸው ጋር ያለው ግንኙነት ..................................................... 16

2.4.4 የጾታ ልዩነትና ለራስ የሚሰጥ ግምት (Self-esteem) በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ያለው ሚና ........ 18
ምእራፍ ሶስት ........ 21
የአጠናን ዘዴ ........ 21
3.1 የአጠናን ዘዴ ........ 21
3.2 የጥናቱ ተተኳሪዎች (የመረጃ ምንጮች) ........ 21
3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........ 21
3.3.1 የጥናቱ ክልል ናሙና አመራረጥ ........ 21
3.3.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........ 22
3.3.3 የክፍል ደረጃና ናሙና አመራረጥ ........ 22
3.3.4 የመምህራንና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 23
3.3.4.1 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 23
3.3.4.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ዘዴ ........ 23
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 24
3.4.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ ........ 24
3.4.2 የምስል ቀረጻ ........ 25
3.4.3 የጽሁፍ መጠይቅ ........ 26
3.4.4 ቃለ መጠይቅ ........ 26
3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 27
ምዕራፍ አራት ........ 28
የመረጃ ትንተናና ውጤት ........ 28
4.1 በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩ ያላቸውን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሁኔታ ምን እንደሚመስል በተመለከተ ........ 28
4.2 በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምን እንደሚመስል በተመለከተ ........ 38

4.3. ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎችና ከወንዶች ጋር የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያላቸውን የተሳትፎ ልዩነት በተመለከተ ........ 48

**ምዕራፍ አምስት** ........ 60

ማጠቃለያና አስተያየት ........ 60

5.1.ማጠቃለያ ........ 60

5.2 አስተያየት ........ 62

ዋቢ ጽሁፎች

ሙዳየ ቃላት

አባሪዎች

## የሰንጠረዥ ዝርዝር

የሰንጠረዥ ርዕስ ገፅ

ሠንጠረዥ -1 የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች መረጃ ........ 24

ሠንጠረዥ -2 ሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት መልስ የመመለስና ጥያቄ የመጠየቅ ዝንባሌያቸውን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ መረጃ ........ 29

ሠንጠረዥ -3 ሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት መልስ የመመለስና ጥያቄ የመጠየቅ ዝንባሌያቸውን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ........ 31

ሠንጠረዥ-4 መምህራን በክፍል ውስጥ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ ውጤት ........ 34

ሠንጠረዥ-5 መምህሩ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት ........ 36

ሠንጠረዥ-6 ሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት መልስ የመመለስና ጥያቄ የመጠየቅ ዝንባሌያቸውን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘው ውጤት ........ 39

ሠንጠረዥ-7 ሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት መልስ የመመለስና ጥያቄ የመጠየቅ ዝንባሌያቸውን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ........ 40

ሠንጠረዥ-8 መምህሩ ለሴት ተማሪዎቻቸው የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ ውጤት ........ 44

ሠንጠረዥ-9 መምህሩ በክፍል ውስጥ ለሴት ተማሪዎቻቸው የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት ........ 45

ሠንጠረዥ-10 ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን ሲማሩና ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ሲማሩ በራሳቸው ፍላጎት መልስ የመመለስና ጥያቄ የመጠየቅ ዝንባሌያቸውን በተመለከተ ከመልከታ የተገኘ መረጃ ........ 48

ሠንጠረዥ-11 ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩና ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ በራሳቸው ፍላጎት መልስ የመመለስና ጥያቄ የመጠየቅ ዝንባሌያቸውን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ........ 50

ሠንጠረዥ-12 መምህራን በክፍል ውስጥ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ ውጤት ........ 53

ሠንጠረዥ-13 መምህሩ ለተማሪዎቸቻቸው የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት ........ 56

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን ሲማሩና ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ጋር ሲማሩ ያላቸውን የተሳትፎ ሁኔታ በማነጻጸር መመርመር ነው፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ የአዲስ አበባ ከተማ በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልት ሲመረጥ የልደታ ማርያም የልጃገረዶች ትምህርት ቤትና የልደታ ማርያም የወንዶች ትምህርት ቤት በአመቺ የናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጠዋል፡፡ ትምህርት ቤቶቹ ከተመረጡ በኋላ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልት የተመረጡ ሲሆን የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም ጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ስልትን በመጠቀም ተመርጠዋል፡፡ ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት ምልከታ (በምስል ቀረጻ የታገዘ) በዋና መረጃ መሰብሰቢያነት፣ የፅሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠየቅ በአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያነት ተመርጠው መረጃው ተሰብበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች በአይነታዊና በገላጭ የመረጃ አተናተን ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተውም ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማዎች ከወንዶች ጋር ከሚማሩት ሴት ተማሪዎች የተሻለ ተሳታፊ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህንንም ለማረጋገጥ በምልከታ፣ በፅሑፍ መጠይቅ እና በቃለ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች በይዘት በመከፋፈል ያላቸውን ልዩነት በማነጻጸር የመረጃውን ውጤት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በመጨረሻም ሴት ተማሪዎች ብቻቸውንም ሆነ ከወንድ ተማሪዎች ጋር ሆነው በሚማሩበት ጊዜ እጃቸውን በማውጣት እንዲሳተፉ ለማድረግ መምህራኑ ቢያበረታቷቸው፣ ሴት ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ ተማሪዎቹ እንዳይደናገጡ በማድረግ ድጋሚ እንዲሞክሩት ወይም የተሳሳቱትን ጥያቄ እንዲያስተካከሉት እድል ቢሰጣቸው፣ በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ላይ ሴት ተማሪዎች መልስ በሚመልሱበት ጊዜም ሆነ በሚሳተፉበት ጊዜ ወንድ ተማሪዎች እንዳይስቁባቸው የሚያደርጉ ምክር አዘል የሆኑ ምንባቦች እንዲካተቱ ቢደረግ፣ የሚሉ የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዲጨምር ለማድረግ ያግዛሉ የተባሉ አስተያየቶች በአጥኚዋ ተሰንዝረዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

የሴት ተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎ በተመለከተ በሀገራችንም ሆነ በውጭ ሀገራት የተለያዩ ምሁራን ጥናቶችን አካሂደዋል፡፡ ለዚህም Seyoum (1991), Almaz (1991), Genet (1991) ያካሄዷቸው ጥናቶች እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ፡፡ የጥናቶቹ ውጤትም ሴት ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከወንድ ተማሪዎች ጋር ሲወዳደሩ ቁጥራቸው አነስተኛ እንደሆነና አብዛኞዎቹ የመማር እድል እንደማያገኙ፣ የመማር እድል ያገኙትም በትምህርታቸው ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዳልሆኑ፣ በመሀልም ትምህርታቸውን እንደሚያቋርጡና እስከመጨረሻው የመዝለቅ እድል ቢያጋጥማቸው እንኳን ውጤታቸው ከወንዶቹ ጋር ሲነጻጸር በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሴትና ወንድ ተማሪዎች ከመምህሮቻቸው ጋር የሚያደርጉትን ቃላዊ ተራክቦ በተመለከተም በተለያዩ ሀገሮች በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ለዚህም በታንዛንያ፣ በኡጋንዳ፣ በጋና እና በኢትዮጵያ የተሰሩትን ጥናቶች እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል በማለት Bendera and Mobaya (1996) እና Odaga and Henveld (1995) ደግሞ Kilo (1994) ን በመጥቀስ ይገልጻሉ፡፡

እንደ ምሁራኑ ገለጻ ጥናቶቹ ሴትና ወንድ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከመምህሮቻቸው ጋር የሚያደርጉትን ቃላዊ ተራክቦ መሰረት ያደረጉ ሲሆኑ ከጥናቶቹ የተገኘው ውጤትም ወንድ ተማሪዎች ከሴት ተማሪዎች የበለጠ ከመምህሮቻቸው ጋር ቃላዊ ተራክቦ እንደሚያደርጉ(እንደሚሳተፉ) የሚያሳይ ነው፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቅሱት ወንድ ተማሪዎች ከሴት ተማሪዎች ይልቅ ከመምህሮቻቸው የተሻለ ትኩረት እና ማበረታቻ ስለሚያገኙ ነው የሚል ነው፡፡ በዚህ የተነሳም ወንድ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረገው ቃላዊ ተራክቦ በልጠው እንደሚታዩ በጥናታቸው አመልክተዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች ብቻ የሚማሩበት ትምህርት ቤት (single sex school) የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ወንድና ሴት ተቀላቅለው በሚማሩበት ትምህርት ቤት (Mixed sex school) ካሉት ሴት ተማሪዎች የበለጠ ተሳታፊና ውጤታማ መሆናቸውን Potter (1978) ያስረዳሉ፡፡

ሴት ተማሪዎች ብቻ የሚማሩበት ትምህርት ቤት ለሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ እንዳለው ምሁራን ያመለክታሉ፡፡ Andrew Mullins (2005) Mayra and David Sadker(2000) ን ጠቅሰው እንደገለጹት፣ በነጠላ ጾታ ትምህርት ቤት(single sex school) የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ወቅት አድማጭነታቸውን በማቆም የክፍል ተሳትፎው መሪ ተዋናይ ይሆናሉ፤ ወንድና ሴት ተቀላቅለው በሚማሩበት ክፍል ውስጥ ግን ሴት ተማሪዎች እንደማይታዩ አባላት ይቆጠራሉ በማለት አመልክተዋል፡፡

የተለያዩ የስነልቦናና የማህበረሰባዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች በበኩላቸው ሴት ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ከመምህሮቻቸው ጋር ቃላዊ ተራክቦ ለማድረግ በሚሞክሩበት ጊዜ መምህሮቻቸው ከወንዶች እኩል እንደማያበረታቷቸውና ወንድ ተማሪዎችም ተጽዕኖ እንደሚያደርጉባቸው የሚገልጽ መረጃ እንዳላቸው በጥናታቸው አመልክተዋል፡፡ይህ ተጽዕኖ ደግሞ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዳያደርጉ፣ በትምህርታቸውም የተሻለ አቀባበል እንዳይኖራቸው በኋላም በስራ አለማቸው ስኬታማ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል በማለት Betz and Fitzgerald (1987) ይገልጻሉ፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ደግሞ ሴትና ወንድ ተማሪዎች በቋንቋ ችሎታ ረገድ ልዩነት እንደሌላቸው ጥናቶች ቢገልጹም የማህበረሰቡ አመለካከት፣ የአስተዳደግ ሁኔታ፣ በክፍል ውስጥ የመምህራን ወንድና ሴት ተማሪዎችን እኩል ያለማበረታታት፣ ወዘተ. ከሚያደርሰው ተጽዕኖ የተነሳ ሴቶች ራሳቸውን ዝቅ እንዲያደርጉ፣ ራሳቸውን የወንዶች ጥገኛ አድርገው እንዲመለከቱና በትምህርታቸውም ንቁ ተሳታፊ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ወንዶች ከጥገኝነት ነጻ ሆነው በራስ መተማመን እንዲኖራቸውና በትምህርታቸው ከሴቶች የበለጠ ተሳታፊ እንዲሆኑ ምክንያት ሆኗል በማለት Semunesh (1997) Haregewoin and Yusuf (1994) ን ጠቅሰው ገልጸዋል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት የተለያዩ ጥናቶች ለመረዳት እንደሚቻለው ሴትና ወንድ ተማሪዎች ተቀላቅለው በሚማሩበት ትምህርት ቤት ወንድ ተማሪዎች ከሴት ተማሪዎች በተሻለ ከመምህሮቻቸው ማበረታቻ እና ትኩረት ስለሚያገኙ በክፍል ውስጥ በሚደረገው ተሳትፎ ሰፊውን ቦታ ይይዛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ወንድ ተማሪዎች ከሴት ተማሪዎች በተሻለ የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መምህራን ሴት ተማሪዎችን ከወንዶች እኩል ያለማበረታታትም ሆነ የወንድ ተማሪዎች ተጽዕኖ በሴት ተማሪዎች ላይ ስነልቦናዊ ጫና ስለሚያስከትል ሴት ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ እና ከዛ በኋላ በሚኖራቸው የስራም ሆነ ማህበራዊ ኑሮ ሀሳባቸውን በበቂ ሁኔታ በንግግር እንዳይገልጹ ያደርጋቸዋል፡፡ በነጠላ ጾታ ትምህርት ቤት የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ግን ከወንዶች ጋር ከሚማሩት የበለጠ በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ጥናቶቹ ያመለክታሉ፡፡

ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ጋር በሚማሩበት ጊዜና ሴቶች ብቻቸውን በሚማሩበት ጊዜ በክፍል ውስጥ ያላቸውን የተሳትፎ ሁኔታ የመረመሩ ጥናቶች እንዳሉ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ ሆኖም በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የሴት ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የመረመሩት ጥናቶች ውስን ናቸው፡፡ እነሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ፋንቱ ደምሴ (1989) «የጾታ ልዩነት አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና» በሚል ርእስ፣ በላይ ሰይድ (1992) «የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ» በሚል ርእስና ማስተዋል ወርቁ (1999) «በባህር ዳር ከተማ በሚገኙ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የስርአተ ጾታ አያያዝና የክፍል ውስጥ ፍተሻ አተገባበር» በሚል ርእስ ጥናቶችን አካሂደዋል፡፡

ከተጠቀሱት ጥናቶች መረዳት እንደሚቻለው ጥናቶቹ የተካሄዱት ሴትና ወንድ ተማሪዎች ተቀላቅለው (አብረው) በሚማሩበት ትምህርት ቤት ነው፡፡ ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን ሲማሩ በክፍል ውስጥ የተሳትፎ ሁኔታቸው ምን ይመስላል? የሚል ጥናት እሳካሁን ድረስ ለአጥኚዋ አላጋጠማትም፡፡ የበላይ ሰይድ ጥናት ሴት እና ወንድ ተማሪዎች አብረው በሚማሩበት ትምህርት ቤት የሴቶቹ ቁጥር ከወንዶቹ ቁጥር ሲበዛ፣ ሲያንስና እኩል ሲሆን የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምን ይመስላል? የሚለውን የመረመረ ሲሆን ውጤቱም

በሁሉም ምድብ ያሉ ሴት ተማሪዎች ከወንዶቹ ያነሰ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ የሚያሳይ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የበላይ ጥናትም ሆነ ሌሎች በክፍለ ትምህርቱ የተሰሩት ጥናቶች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩና ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ የሚያሳዩት ን የተሳትፎ ሁኔታ በማነጻጸር አልመረመሩም፡፡በዚህም ምክንያት አጥኚዋ ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩና ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ የሚያሳዩትን የተሳትፎ ሁኔታ ቢፈተሽ ጠቀሜታ ይኖረዋል በማለት ጥናቱን ለማጥናት ተነሳስታለች፡፡

## 1.2 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ሴቶች ብቻቸውን እና ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ ያላቸውን የተሳትፎ ሁኔታ መመርመር ነው፡፡ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡

1. ሴቶች ብቻቸውን በሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ለጥናቱ የተመረጡት ተማሪዎች ተሳትፎ ምን ይመስላል?
2. ሴቶች እና ወንዶች አብረው በሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ለጥናቱ የተመረጡት ሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ምን ይመስላል?
3. በሁለቱ ትምህት ቤቶች ውስጥ ባሉ ሴት ተማሪዎች መካከል የተሳትፎ ልዩነት አለ? ካለ የልዩነቱ ምክንያት ምንድን ነው?

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና አላማ ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን እና ሴትና ወንድ ተማሪዎች አብረው በሚማሩበት ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ መመርመር ነው፡፡ በዚህም ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡

1. ሴቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የማይሳተፉ ከሆነ የማይሳተፉበትን ምክንያት በመጠቆም መምህራን ሴቶች ይበልጥ የሚሳተፉበትን ዘዴ እንዲቀይሱ ይረዳቸዋል፡፡

2. መምህራን በክፍል ውስጥ ባለው ተሳትፎ ውስጥ ሁሉም ሴት ተማሪዎች እኩል እንዲሳተፉ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ሀሳብ በመሰንዘር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡
3. በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ በሌሎች ትምህርት ቤቶችና የክፍል ደረጃዎች ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ አጥኚዎች እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሁለት የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ይካሄዳል፡፡ ትምህርት ቤቶቹም የልደታ ማርያም ካቶሊክ ካቴድራል ልጃገረዶች ትምህርት ቤትና የልደታ ማርያም ካቶሊክ ካቴድራል የወንዶች ትምህርት ቤት ናቸው፡፡ በእነዚህ በተመረጡት ሁለት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ2004 ዓ.ም የዘጠነኛ ክፍል ሴት ተማሪዎችና በክፍሉ መምህራን ላይ ተመስርቶ ይካሄዳል፡፡ ጥናቱ ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን (ሴቶች ብቻ በሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ) በሚማሩበት ጊዜና ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር (ሴትና ወንድ አንድ ላይ በሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ) በሚማሩበት ጊዜ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ማለትም ጥያቄ የመጠየቅ፣ መልስ የመመለስ፣ ሀሳብ የመሰንዘርና አስተያየት የመስጠት ሁኔታዎችን እና መምህራን ለሴቶችና ለወንዶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረትና ማበረታቻ ማለትም በተደጋጋሚ ስም መጥራት፣ ማሞገስ፣ መተቸት ላይ በማተኮር ብቻ ያቀርባል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የሚታየው የመምህሩና የተማሪዎቹ ቃላዊ ተራክቦ ብቻ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ የሚካሄዱ ኢ- ቃላዊ (Non-verbal activities) የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ማለትም ፈገግታ፣ ራስን ማወዛወዝ፣ የአይን እንቅስቃሴ፣ የመቁነጥነጥ ሁኔታዎች ...ወዘተ. አይታዩም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳን

### 2.1 ተራክቦ ምንድን ነው?

ተራክቦን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ ለተራክቦ የተሰጡት አብዛኞዎቹ ብያኔዎች ተመሳሳይ ናቸው፤ የተወሰኑት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ ተራክቦ (ቃላዊ ተግባቦት) ሰዎች እርስ በርስ በንግግር (በቃል) የሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ነው፡፡ በዚህ ሂደት ሰዎች የተነገረውን ሀሳብ በመረዳት ምላሽ የሚሰጡበትም ነው (Sunderland 1994)፡፡ Levinson (1983) በበኩላቸው ተራክቦ በንግግር ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተሳታፊዎች እየተፈራረቁ የሚነጋገሩበት የንግግር (የተግባቦት) ሂደት እንደሆነ አመልክተዋል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ በተናጋሪና በአድማጭ መካከል አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል፡፡ አለመግባባት ከተፈጠረ ደግሞ ተራክቦው ሊደናቀፍ ወይም ሊቋረጥ ስለሚችል ተራክቦውን የሚያካሂዱት ሰዎች ይህ እንዳይፈጠር ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፡፡

ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች እንደምንረዳው ተራክቦ (ቃላዊ ተግባቦት) የሚባለው ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በአንድ ላይ ወይም ፊት ለፊት ተገናኝተው የሚያካሂዱት የተግባቦት (የንግግር) ሂደት መሆኑን ነው፡፡ በዚህ የንግግር ሂደት ውስጥ ተናጋሪና አድማጭ ይኖራሉ፡፡ አድማጭም በተራው ላዳመጠው ንግግር ምላሽ የሚሰጥበት ነው፡፡

### 2.2 ተራክቦ በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ማንኛውም ትምህርት የሚተላለፈው በተራክቦ ነው፡፡ በተለይ በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ተራክቦ ወሳኝ ሚናን ይጫወታል፡፡ ተራክቦ ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ ሰዎች እርስ በርስ የሚያካሂዱት የተግባቦት ሂደት መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚካሄደው ተራክቦም በመምህሩና በተማሪዎች መካከል የሚከወን እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ይህም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተራክቦ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከናወን ሆኖ ቁጥራቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተሳታፊዎች የሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ነው፡፡ የተግባቦቱ አላማ ግልጽ ያልሆነን አንድ ሀሳብ የተግባቦቱ ተሳታፊዎች እስኪረዱት ድረስ የሚደረግ የሃሳብ ልውውጥ ነው (Nunan 1993):: በተመሳሳይ መልኩ Sunderland(1994) ተራክቦ ተናጋሪና አድማጭ ያለበት የሁለትዮሽ ግንኙነት ነው፤ በመማርያ ክፍል ውስጥ የሚካሄደው ተራክቦም እንደዚሁ ተናጋሪና አድማጭ ያለበት ሲሆን ክፍል ውስጥ በሚደረገው ተራክቦ የተራክቦው ተሳታፊዎች መምህሩና ተማሪዎች ናቸው፡፡ መምህሩና ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚኖራቸው ተራክቦ በሚከተሉት ፈርጆች ይገለጻል፤ እነዚህም ማስተማር (Lecturing)፣ መመለስ (answering)፣ መጠየቅ (Questioning) ፣ ማሞገስ (Praising)፣ መተቸት (Criticizing) ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡

ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች እንደምንረዳው ተራክቦ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመምህሩና በተማሪዎች መካከል የሚካሄድ የተግባቦት የንግግር ሂደት ሲሆን፣ የመምህሩንና የተማሪዎቹን የቃል ተሳትፎ የሚጠይቅም ነው፡፡ ይህም የሚገለጸው ወይም የሚካሄደው በማስተማር፣ በመጠየቅ፣ በመመለስ፣ በማብራራት፣ በመተቸት...ወዘተ. ነው፡፡ የክፍል ውስጥ የተራክቦ ሁኔታ የተሳካ ለማድረግ መምህራን ከፍተኛ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ እንደ Littlwood (1984) ገለጻ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመምህርና በተማሪ መካከል ለሚካሄደው ተራክቦ ውጤታማነት የቋንቋ መምህራን ከፍተኛ የሆነ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ለተሳትፎ ምቹ የሆነ ሁኔታ በመፍጠር ሁሉም ተማሪዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራኑ ይህን የሚያደርጉት የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን በማየትና አስተያየት በመስጠት፣ ጥያቄ በመጠየቅና ምላሽ እንዲሰጡ በማበረታታት... ወዘተ. ነው፡፡

## 2.3 ተራክቦን በመጠቀም ቋንቋን ማስተማር ያለው ጠቀሜታ

በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ተራክቦን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ የተለያዩ ምሁራን ተራክቦን በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ መጠቀም ተማሪዎችን በማሳተፍ በቋንቋው የመገልገል እድላቸውን እንደሚያሰፋው ያስረዳሉ፡፡
Sunderland (1994) በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ቃላዊ ተራክቦን በመጠቀም ቋንቋን ማስተማር ትልቅ እገዛ እንዳለው አመልክተዋል፡፡ ይህም በመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህር

ከተማሪ፣ ተማሪ ከተማሪ (እርስ በርስ) እንዲግባቡ፣ እንዲጠያየቁ፣ እንዲከራከሩ፣ እንዲወያዩና በአጠቃላይ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Allwrght (1991) በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተራክቦን በመጠቀም ቋንቋን ማስተማር በተማሪዎችና በመምህራን፣ በተማሪዎች (እርስ በርስ) በአጠቃላይ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመተጋዝና የመተባበር መንፈስ ስለሚያሳድር በክፍል ውስጥ መነሳሳትን ይፈጥራል፡፡ ይህም ከፍተኛ የሆነ የመነቃቃትና የመሳተፍ መንፈስ እንደሚያሳድር አስገንዝበዋል፡፡

ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች እንደምንረዳው መምህራን በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ወቅት ቃላዊ ተራክቦን (ንግግርን) እንደዋነኛ መሳሪያ መጠቀም እንዳለባቸው ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በመማሪያ ክፍልም ሆነ ከመማሪያ ክፍል ውጭ ሀሳባቸውን የሚገልጹት እና ከሌሎች ጋር የሚግባቡት በንግግር ስለሆነ ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸውን ቢያዳብሩ የተሳካ ተግባቦት ለማድረግ ስለሚያስችላቸው ነው፡፡

## 2.4 በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ምክንያቶች

### 2.4.1 በመማሪያ ክፍል ተሳትፎ ላይ የጾታ ልዩነት የሚያስከትለው ተጽዕኖ

ጾታ የሚለው ቃል በተፈጥሮ ሴት ወይም ወንድ ሆኖ መፈጠርን ሲያመለክት፣ ስርአተ ጾታ ደግሞ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሴት ወይም ወንድ ሆኖ መፈጠር ያለውን ባህላዊ እሳቤም አብሮ ያመለክታል፡፡ እንደ Santrock (2001) ገለጻ ጾታ የሚለው ቃል ሚያመለክተው የአንድን ሰው አካላዊ መለያ ማለትም ወንድ ወይም ሴት ሆኖ መፈጠርን ሲሆን ስርአተ ጾታ ግን በሴቶችና በወንዶች መካከል ቋሚ ያልሆኑ ልዩነቶችን የሚያሳይ ነው፤ ልዩነቶቹ በማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች አማካኝነት ሊወሰኑ የሚችሉ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Sunderland (1992) ጾታ የሚለው ቃል ሰዎች በተፈጥሮ ሴት ወይም ወንድ ሆነው መፈጠራቸውን የሚያመለክት ሲሆን ስርአተ-ጾታ ደግሞ በየማህበረሰቡ ለሴት እና ለወንድ የሚኖርን አመለካከትና ባህሪ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም ማለት ሴቶችና ወንዶች እንደሚኖሩበት ባህል ሴትና ወንድ ማድረግ ወይም መሆን ያለባቸው እንደዚህ ነው፤ ወይም

እንደዚህ አይነት ተግባር ማድረግ አለባቸው፤ ብሎ ማህበረሰቡ የሰጣቸውን ቦታም እንደሚያመለክት አስረድተዋል፡፡

ከላይ ከተገለለጹት ሀሳቦች እንደምንረዳው አንድ ማህበረሰብ ወንድና ሴት ማድረግ የሚገባቸው እንደዚህ አይነት ነገር ነው ብሎ የደነገገው ተግባር እንዳለ ነው፡፡ የአብዛኛው ማህበረሰብ ባህል በትምህርትም ሆነ በተለያዩ ማህበራዊ ተግባራት ሴቶችን ከወንድ ጋር እኩል የማያሳትፍ ነው፡፡ ይህ አመለካከትም በሴቶች ትምህርትና የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ተጽእኖ ያስከትላል፡፡ ስርአተ ጾታና ትምህርትን መሰረት ያደረጉ ጥናቶች በኢትዮጵያና በውጭ ሀገሮች ተካሂደዋል፤ ከእነዚህም መካከል የተወሰኑት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

Seyoum (1991)፣ Almaz (1991)፣ Genet (1991)፣ በካሄዱት ጥናት ሴት ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከወንዶች ጋር ሲተያዩ ቁጥራቸው አናሳ እንደሆነ፣ ትምህርት ለመማር እድል ያገኙትም በትምህርታቸው ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዳልሆኑ፣ በመሀልም ትምህርታቸውን የሚያቋርጡና እስከ መጨረሻው የመዝለቅ እድል ቢያጋጥማቸው እንኳን ውጤታቸው ከወንዶች ጋር ሲተያይ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡
Genet (1991) በጥናታቸው ለዚህ ምክንያት ብለው የጠቆሙት በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች ሀገሮች ለሴት ልጅ ያለ ዝቅተኛ አመለካከት ነው፡፡ ሴቶች በልጅነታቸው ባል አግብተው የባሎቻቸው ታዛዥ እንዲሆኑ እንጂ በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ለሚያካሂዱ ተግባራት ከወንዶች ጋር እኩል መሳተፍ እንደሌላባቸው የሚያደርግ ባህል ስላለ ነው፤
ከኢትዮጵያ ውጭም የጾታ ልዩነትንና የትምህርት ተሳትፎን የተመለከቱ የተለያዩ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ጥናቶቹ በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል በተለያዩ ትምርቶችና በክፍል ውስጥ በሚያሳዩት ተሳትፎ ልዩነት እንዳለ ያመለክታሉ፡፡ የልዩነቱ ምክንያት የተማሪዎቹ የጾታ መለያየት ሳይሆን ማህበረሰቡ ለሴቶች የሚሰጠው ዝቅተኛ ግምት የተነሳ የሴት ተማሪዎች በራስ ያለመተማመን ችግር፣ የወንድ ተማሪዎች ከሴት ተማሪዎች የተሻለ በራስ የመተማመንስሜትና ወንድ ተማሪዎች ከመምሮቻቸው የሚያገኙት ትኩረትና ማበረታቻ ነው፤(Betz and Fitzegerald 1987)፡፡

ባጠቃላይ ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች እንደምንረዳው አንድ ማህበረሰብ ለሴቶች የሰጠው የወንዶች የበታች የመሆን ቦታ ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ስለሚያንጸባርቁት ሴቶች በንቃት እንዳይሳተፉ ተጽዕኖ እንዳለው ነው፡፡ ይህ ተጽዕኖ ደግሞ በሴቶች የክፍል ውስጥ ተሳትፎም ሆነ በቀጣይ ህይወታቸው የቋንቋ አጠቃቀም ላይ ተጽዕኖ ያስከትላል፡፡ ይህን በመደገፍ Amanuel (1996) Lock head and Harris (1984) ን በመጥቀስ ወንድ ተማሪዎች ወንዶችና ሴቶች አብረው በሚማሩበት ክፍል ውስጥ ቃላዊ ተራክቦን በመጠቀም ተሳትፎ በሚደርጉበት ጊዜ ወንድ ተማሪዎች ቀድመው ምላሽ በመስጠትና ሰፊ የንግግር ጊዜ በመያዝ ሴት ተማሪዎች እንዳይሳተፉ እንደሚያደርጉ አመልክተዋል፡፡ በትምህርት ችሎታ ወይም በአእምሮ ተግባራት ረገድ ግን በሴቶችና በወንድ ተማሪዎች መካከል ልዩነት እንደሌለ ጥናቶቹ ሲያስረዱ ለልዩነቱ ዋና ምክንያት የሆነው ማህበረሰቡ ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጠው ዝቅተኛ አመለካከትና ይህን አመለካከት መምህራንና ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መተግበራቸው መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

## 2.4.2 መምህራን ለሴቶችና ለወንዶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረት መለያየት

በመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን ለሴቶችና ለወንዶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረት ልዩነት አለው የሚባለው ለወንድ ወይም ለሴት ተማሪዎች የተሻለ (የበለጠ) ትኩረት የሰጡ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም መምህሩ/ሯ ለወንድ ወይም ለሴት ተማሪዎች መልስ እንዲመልሱ፣ ጥያቄ እንዲጠይቁ፣ አስተያየት እንዲሰጡ… ወዘተ. ካደረጉ ለሴት ወይም ለወንድ ተማሪዎች የበለጠ ትኩረት ሰጥተዋል ይባላል፡፡

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ወንድ እና ሴት ተማሪዎችን በተለያየ ሁኔታ ትኩረት መስጠት፣ ማበረታታት ያስፈልጋል፤ የሚል መመሪያ ባይኖርም መምህራን ይህን ነገር ሲተገብሩት ይታያሉ፡፡ ይህን በተለያየ ሁኔታ ለተማሪዎች ትኩረት መስጠት፣ ማበረታታት መምህራን አውቀው የሚያደርጉት አይደለም፡፡ ነገር ግን መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች የማህበረሰቡ አንድ አካል ስለሆኑ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያንጸባርቁትም ይህንኑ የማህበረሰቡን አመለካከት ነው፡፡ ስለሆነም መምህራን ሴቶችና ወንዶች አብረው በሚማሩበት መማሪያ

ክፍል ውስጥ ተማሪዎቻቸውን በእኩል ሲያበረታቱ፣ ጥያቄ ሲጠይቁ... ወዘተ አይታዩም (Sunderland 1994)፡፡

መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ የበለጠ ትኩረት የሚሰጡትና ብዙ መመሪያዎችን የሚያቀርቡት ከሴቶች ይልቅ ለወንድ ተማሪዎች ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሴት ተማሪዎች ዝምታን ያበዛሉ፡፡ መምህራን ከባድ ጥያቄዎችን የሚጠይቁት ወንድ ተማሪዎችን በመሆኑ ወንድ ተማሪዎች ለሚጠየቁት አስቸጋሪ የሆነ ጥያቄ ከመምህሮቻቸው ያለምንም ፍርሀት እገዛ ይጠይቃሉ፡፡ ለመመለሻም ሰፋ ያለ ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚህም ሌላ የተሳሳተ መልስ በሚመልሱበት ጊዜ በድጋሚ እንዲሞክሩ ማበረታቻ ይሰጣቸዋል፤ (Santrock 2001)፡፡

መምህራን ለሴትና ለወንድ ተማሪዎች የሚጠይቁት ጥያቄ አይነት መለያየትም በሴት ተማሪዎች የተሳትፎ ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ ያስከትላል፡፡ ይህን ጉዳይ በማስመልከት ማስተዋል (1999) Alexander (1997) እና Greenberg (1996) ን በመጥቀስ፣ መምህራን በአብዛኛው ለሴት ተማሪዎች ቀላል ጥያቄዎችን የሚጠይቁ ሲሆን ለወንድ ተማሪዎች ደግሞ የተለያዩ አይነት ከበድ ያሉ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያደርጋሉ፡፡ ይህም ወንድ ተማሪዎች ለተሰጣቸው ጥያቄ የቀረበውን መመሪያዎች በማየት ችግሮችን እንዴት መፍታት እንደሚችሉ ይለማመዳሉ፤ ይህ ሁኔታ ደግሞ ለወንዶች በራስ የመተማመን ብቃታቸውን ሲያጎለብት ለሴቶች ግን ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ከእነዚህ ሀሳቦች እንደምንረዳው ወንድ ተማሪዎች ከባድ ጥያቄ ሲጠየቁ ጥያቄዎቹን ለመመለስ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የእውቀት አድመሳቸውን የማስፋት እድል ከማገኘታቸውም በላይ እችላለሁ የሚል በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲያድርባቸው ሲያደርግ ለሴት ተማሪዎችም ወንድ ተማሪዎች ከእነሱ መብለጣቸውን እንዲያምኑ የሚያደርግና በክፍል ውስጥ እኩል የመሳተፍ መንፈስ እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ነው፡፡

መምህራን በቋንቋ ክፍለ ጊዜ ብዙ ጥያቄ የሚጠይቁት፣ በተደጋጋሚ ስማቸውን የሚጠሩት፣ አጭርና ገንቢ ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡት ለወንድ ተማሪዎች ብቻ በመሆኑ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከመሳተፍ ይልቅ ዝምታን ይመርጣሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ሴት ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ እንደማይታዩ የክፍሉ አባላት ይቆጠራሉ (Bank and Hall 1997)፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Sunderland (1994) ና Spender (1982) መምህራን ለሴት

ተማሪዎች የሚያሳዩት ትኩረት እና አዎንታዊ ምጋቤ ምላሽ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ሴቶች ተማሪዎች በትምህርታቸው ጎበዝ፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ለመሳተፍ የሚፈልጉ ቢሆኑም ከመምህሮቻቸው የሚያገኙት መጋቤ ምላሽ ግን ከወንዶች ያነሰ እና አሉታዊ በመሆኑ ተስፋ የሚያስቆርጥ እና ከመማር ማስተማሩ ሂደት የተገለሉ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ለወንዶች ተማሪዎች የሚያበረታታ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች እንደምንረዳው የመምህራን ትኩረት አሰጣጥ (ጥያቄ አለመጠየቅ፣ አለማበረታታት፣ ተማሪዎቹ ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ የሚሰጡበት ስፉ ያለ ጊዜ አለመስጠት… ወዘተ) በተማሪዎች የመማሪያ ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አለው፡፡ Ashcroft and Foreman-peck (1994) ተማሪዎችን ማሳተፍ በራሳቸው እንዲተማመኑና ከሚነሳው ሀሳብ የተለያየ እውቀት እንዲጨብጡ ስለሚያደርጋቸው በክፍል ውስጥ ተማሪዎች እንዲሳተፉና ወደ ተራክቦ እንዲገቡ ጥያቄ መጠየቅ፣ መልስ ለሚመልሱበት ሰፋ ያለጊዜ መስጠትና ማበረታታት እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያየዘ መምህራን በመማሪያ ክፍል ተራክቦ ጊዜ ለሴትና ለወንድ ተማሪዎች እኩል የመሳተፍ እድል በመስጠት በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ጥሩ የሆነ የተሳትፎ መንፈስ እንዲኖር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንን ሀሳብ በመደገፍም Nunan and Lamb (1996) መምህራን ተማሪዎቻቸው ጥያቄ በሚጠይቁበት ጊዜ ተማሪዎቹ ጥያቄውን አስበው የሚመልሱበት ሰፋ ያለ ጊዜ መስጠት አለባቸው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ተማሪዎቹ ስለጥያቄው ሁኔታ ሳያስቡ ቢመልሱ እንሳሳታለን የሚል ፍራቻ ስለሚያድርባቸው ዝምታን ይመርጣሉ፡፡ ይህም በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያስከትል አመልክተዋል፡፡ እንደ Semunesh (1997) ገለጻ ደግሞ ወንድ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተራክቦ ጊዜ ሳይመረጡ ሰፊ የተሳትፎ (የንግግር) ጊዜ በመያዝ፣ ሴቶች ያፍራሉ ወይም አይችሉም የሚል ምክንያት እየሰጡ፣ ሴቶችን ወክለው ንግግር ለማድረግ በመሞከርና ሴቶች ምላሽ በሚሰጡበት ወይም ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ በማቋረጥ፣ በሴቶች ላይ ጫና (ተጽዕኖ) ያሳድራሉ፤

መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ እንዲሳተፉ የሚያደርጉት (እድል የሚሰጡት) ከሴት ተማሪዎች ይልቅ ለወንድ ተማሪዎች ነው፡፡ ምን አልባትም ይህ ሊሆን የቻለው ወንድ ተማሪዎች በፍጥነት ወደ ቃል ተሳትፎ በቅልጥፍና እና በንቃት ስለሚገቡ ነው፤ Bailey

(1993)፡፡ Sunderland (1992፣88), Spender (1992) ን ጠቅሰው እንዳመለከቱት መምህራን ሴትና ወንድ ተማሪዎች አብረው በሚማሩበት ክፍል ውስጥ የተሻለ (የበለጠ) ትኩረት የሚሰጡት ለወንድ ተማሪዎች ሲሆን፣ መምህራን ይህን የሚያደርጉት ሆነ ብለው በተማሪዎች የጾታ መለያየት ምክንያት አድሎ ለማድረግ አስበውበት ሳይሆን ባጋጣሚ የሚታይ (የሚከሰት) ነው፡፡ በተመሳሳይም Kidane (2006) Albright (1997)ን ጠቅሰው ወንድም ሆነ ሴት መምህራን ብዙ ጊዜ ትኩረት የሚሰጡትና በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያበረታቱት ወንድ ተማሪዎችን ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ ሴት ተማሪዎች ጥያቄ በሚጠይቁበት፣ በሚመልሱበት እና ባጠቃላይ በሚሳተፉበት ጊዜ ጥሩ የሆነ ማበረታቻም ሆነ ምላሽ ከመምህሮቻቸው እንደማያገኙ አመልክተዋል፡፡ ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው መምህራን ማህበረሰቡ ባሳደረባቸው የባህል ተጽዕኖ ሳቢያ ሴት ተማሪዎችን የወንዶች የበታች አድርገው እንደሚመለከቱ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በሴቶች የመማሪያ ክፍል ተሳትፎ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ያስከትላል፡፡ ሴቶች ሲናገሩ ወይም ሲሳተፉ ከመምህሮቻቸው በጎ የሆነ ምላሽ ወይም ማበረታቻ የማያገኙ ከሆነ ይህን የሚታዘቡት ወንድ ተማሪዎች ሴቶች በሚናገሩበት ጊዜ ማፌዝና መሳቅ ይጀምራሉ፡፡ ሴቶችም ስንሳተፍ ብንሳሳት መምህሩ ወይም ተማሪዎቹ መጥፎ የሆነ ምላሽ ቢሰጡኝስ፣ ቢስቁብኝስ፣ ቢያፌዙብኝስ... ወዘተ የሚል ስጋት በውስጣቸው እንዲያድግ እና በዚህ ፍራቻ የተነሳ በክፍል ውስጥ ዝምታን እንዲመርጡ ይሆናሉ ፡፡

ከላይ የተገለጹትን ሀሳቦች በማጠናከር በላይ ሰይድ (1992፣11) Golombok and Fivush (1994) እና Good and Brophy (1987፡596-597) ን በመጥቀስ በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ያደረጉትን ጥናት በመጥቀስ እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡

መምህር፡- ‹‹ካሮል! በአመት ውስጥ ስንት ወቅቶች አሉ?››

ካሮል፡- ‹‹ሶስት››

መምህር፡- ‹‹አይደለም፡፡ ባለፈው የጻፉችሁት ከሶስት የሚበልጥ ነው፤ ትንሽ አሰብ››

ካሮል፡- ‹‹አራት››

መምህር፡- ‹‹ጥሩ! ስማቸውን ልትጠራልኝ ትችላለህ?››

ካሮል፡- (ሶስቱን መለሰ)

መምህር፡- ‹‹አራተኛውን አልጻፍክም?››

ካሮል፡- ‹‹አላስታውስም››

መምህር፡- ‹‹እንደገና አራቱንም እንድትጽፍ! አራቱን የሚያውቅ ማነው? ጆን! ትመልሳለህ?››

ጆን፡- ( አራቱንም መለሰ)

መምህር፡- ጥሩ ‹‹አስታውሰሀል››

ከላይ ከተጠቀሰው የመምህር ተማሪ ተራክቦ ዘርፍ በመጀመሪያው የተጠየቀው ተማሪ መልሱን ባለማወቁ እንደገና እንዲሞክር እድል በመስጠት መምህሩ እንዲበረታታ ማድረጋቸውን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው የመምህር ተማሪ ተራክቦ ደግሞ በመምህርና በሴት ተማሪ መካከል የተደረገ ንግግር ሲሆን የመምህሩ ምላሽ ከላይ ከቀረበው ለየት ያለ ነው፡፡ ትምህርቱ ስለ አመቱ ወራትና የበአል ቀን ስሞች ነበር፡፡

መምህር፡- የ ‹‹ ፎል ሲዝን›› ሌላ መጠሪያው ምን ይባላል? ሊኒ!

ሊኒ፡- ‹‹ሀሎዊን››

መምህር፡- የበአል ስም አልጠየኩሽም! ሌላ መጠሪያ ቃሉን እንጂ?

ሊኒ፡- (መልሱን እንደማታውቀው ገለጸች)

መምህር፡- ‹‹ጥቂር ሰሌዳው ላይ እጽፈዋለሁ፤ ሮቢ ያነበዋል ተመልከቱ!››

ሮቢ፡- (መልስ አልሰጠም)

መምህር፡- ‹‹የሚታወስ ቃል ነው ሮቢ! እረዳሀለሁ!››

ከላይ ከተገለጹት ምሳሌዎች እንደምንረዳው መምህራን ከሴት ተማሪዎች በተሻለ ወንድ ተማሪዎችን እንደሚያበረታቱ ነው፡፡ ለምሳሌ ከመጀመሪያው ወንድ ተማሪ ከካሮልና ከመምህሩ ንግግር ብንነሳ ካሮል ላላወቀው ምላሽ የተሰጠ የነቀፌታ ቃል የለም፡፡ እንዲያውም እንዲበረታታ እና እንዲሞክር ነው የተደረገ ነው፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ላይ ባለውም ወንድ ተማሪ ሮቤ ጋር የተደረገው ተመሳሳይ ነው፡፡ መልሱን ባያውቀውም ማበረታቻ ተሰጥቶትና ከመምህሩም እርዳታ እንደሚያገኝ ተነግሮት መመለስ እንዲችል ነበር የተደረገው፡፡ ከሊኒ ጋር ግን ይህ የማበረታታት ሂደት ሲደረግ አልታየም፤ ሁለተኛ እድልም አልተሰጣትም፡፡ እንዲያውም ከመምህሯ የተሰጣት ምላሽ መልሱን ባለማወቋ እንድታፍር የሚያደርግ ነው፡፡

ይህ ነገር ደግሞ ከላይ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው የወንድ ተማሪዎች በራስ የመተማመን መንፈስ ሲገነባ፣ የሴቶችን በራስ የመተማመን መንፈስ ያሳጣል፣ ሴት ተማሪዎች የወንዶች የበታች የመሆን ስሜት በውስጣቸው እንዲያድግም ያደርጋል፡፡ ባጠቃላይ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በጾታቸው መለያየት የተነሳ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተለያየ ተኩረት የሚሰጧቸው ከሆነ በተሳትፏቸው ላይ ተጽእኖ ያስከትላል፡፡

### 2.4.3 ሴቶች ብቻቸውን መማራቸው እና ከወንዶች ጋር አብረው መማራቸው ከተሳትፏቸው ጋር ያለው ግንኙነት

#### 2.4.3.1 ሴቶች ብቻቸውን መማራቸው ከተሳትፏቸው ጋር ያለው ግንኙነት

የነጠላ ጾታ ትምህርት ቤት ጠቀሜታ የለውም በሚል የተለያዩ ምሁራን አስተያየት እየሰጡበት የቆየ ጉዳይ ቢሆንም የቅርብ ጥናቶች ግን የነጠላ ጾታ ትምህርት ቤት በተለይ ሴቶች ብቻ የሚማሩበት ትምህርት ቤት በጾታ ልዩነት ምክንያት የሚመጣ ተጽእኖ እንዳይኖር እገዛ እንደሚያደርግ ያመለክታሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሴቶች የትምህርት አቀባበልም ሆነ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው ላይ ጠቀሜታ አለው፤ ይህም ሴቶች በጾታቸው የተነሳ ከሚደርስባቸው ባህላዊ ተጽዕኖ ነጻ ሆነው እንዲማሩ ይረዳቸዋል፤ (Jimenez and Lock head 1989) ፡፡

Jimenez and Lock head (1989) በታይላንድ ሀገር በስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተደረገውን ጥናት ጠቅሰው እንዳመለከቱት ሴቶች ብቻቸውን የሚማሩባቸው ክፍሎች በሂሳብና በሳይንስ ትምህርት የሴቶች ውጤት ከወንዶቸች ጋር ከሚማሩት ሴት ተማሪዎች ከፍተኛ ነበር፡፡ ይህም የሚያመለክተው ሴቶች ብቻቸውን የሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ ከወንዶች ተማሪዎችም ሆነ ከመምህራን የሚመጣ ተጽዕኖ ስለሌለ በነጻነት ትምህርታቸውን ብቻ ስለሚከታተሉ ውጤታማ መሆናቸውን ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ Bank and Hall (1997) ሴቶች ብቻ የሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር አብረው ከሚማሩበት ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ የበለጡ (የተሻሉ) ሆነው መገኘታቸውን አስረድተዋል፡፡ ከምሁራኑ ሀሳብ

እንደምንረዳው በነጠላ ጾታ የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከመምህራንም ሆነ ከወንድ ተማሪዎች የሚመጣ ተጽእኖና ጫና ስለሌለባቸው ያለፍርሀት በክፍል ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡ ከወንዶች ጋር በሚማሩበት ጊዜ ግን መምህራኑ ለወንድ ተማሪዎች ቅድሚያ ስለሚሰጡና ሴት ተማሪዎችን ስለማያበረታቱ፡ በክፍል ውስጥ በነጻነት እንዳይሳተፉ ይሆናሉ፡፡

## 2.4.3.2. ሴቶች ከወንዶች ጋር አብረው መማራቸው ከተሳትፏቸው ጋር ያለው ግንኙነት

ሴቶችና ወንዶች አብረው የሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በተመለከተ የተለያዩ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ የአብዛኞቹ ጥናት ውጤት ሴቶችና ወንዶች አብረው ሲማሩ የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንድ ተማሪዎች ያነሰ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

Kidane (2006) Albright (1997)ን ጠቅሰው ወንድና ሴት ተማሪዎች አብረው በሚማሩበት ጊዜ ወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተራክቦን ይቆጣጠራሉ፡፡ ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑትም ራሳቸው ወንድ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ይህም ማለት ጥያቄ የሚጠይቁት፣ መልስ የሚመልሱት ከመምህሮቻቸው ማበረታቻ የሚያገኙት፣ በተሳሳቱ (በተደናገሩ) ጊዜ እርዳታ የሚያገኙት እና ባጠቃላይ የተሳትፎው ዋና አንቀሳቃሽ የሚሆኑት ወንድ ተማሪዎች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ሴቶችና ወንዶች አብረው በሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ ሴት ተማሪዎች ጥያቄ በሚጠየቁበት ጊዜ ምላሽ አይሰጡም፣ አንዳንዴ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ መልሳቸው በጣም አጭርና ያልተሟላ ነው (Sunderland 1992)፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያለውን የመምህር ተማሪን ተራክቦ ለመመርመር በታንዛንያ፣ በማላዊ፣ በሩዋንዳ፣ በኬንያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት መምህራን ወንዶች ጋር ለሚማሩ ሴት ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረትና ማበረታቻ በጣም አነስተኛ እንደሆነና በዚህም የተነሳ የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎም ሆነ አጠቃላይ የትምህርት ውጤታቸው ከወንድ ተማሪዎች ጋር ሲተያይ አነስተኛ መሆኑን Odaga and Henveld (1995) Kilo (1994)ን በመጥቀስ አመልክተዋል፡፡

ባጠቃላይ ጥናቶቹ እንደሚያስረዱት  ሴቶችና ወንዶች አብረው በሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተሳትፎ ሁኔታቸው ከወንድ ተምሪዎች ያነሰ እንደሆነ ነው፡፡ ለዚህም እንደ ዋና ምክንያት ሊጠቀሱ የሚችሉት ማህበረሰቡ ለሴቶች የሚሰጠውን አመለካከት መምህራኖቹም ሆኑ ወንድ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስለሚያንጸባርቁትና ሴት ተማሪዎቹም ይህን አመለካከት አምነው በመቀበላቸውም ወይም  በፍራቻ በክፍል ውስጥ ስለማይሳተፉ  ነው፡፡
ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ Amanuel (1996) የጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው ወንድና ሴት ተማሪዎች ተቀላቅለው በሚማሩበት የግል ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንድ ተማሪዎች በልጠው መገኘታቸውን አመልክቷል፡፡ Amanuel (1996)  በግል ትምህርት ቤት ባካሄደው ጥናት ሴቶችና ወንዶች አብረው መማራቸው በክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው ላይ ምንም አይነት ተጽእኖ እንደሌለውና እንዲያውም ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች የተሻለ ተሳታፊ እንደሆኑ አረጋግጧል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በአሜሪካ ሀገር በአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ የተሰራው ጥናት ውጤት ሴት ተማሪዎች በአጠቃላይ የትምህርት ውጤታቸውም ሆነ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንድ ተማሪዎች የተሻሉ እንደሆኑና የመምህራኑንም ትኩረት ከወንዶቹ የበለጠ የሚወስዱት ሴት ተማሪዎች መሆናቸውን አረጋግጧል (Macoby 1990)፡፡  ነገር ግን ጥናቱ የተሰራው በአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ በመሆኑ የጥናቱ ውጤት ሁሉንም ተመማሪዎች ላይወክል ይችላል የሚል አስተያታቸውንም ምሁሩ ጠቁመዋል፡፡

ባጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች እንደምንረዳው ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን በሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ በትምህርታቸው ውጤታማ መሆናቸውን እና ከወንዶች ጋር የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ደግሞ ውጤታቸው እና የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች የሚነሳው ጫናም ሆነ ከመምህራን የሚመጣ የትኩረት ልዩነት ባለመኖሩ ተማሪዎቹ ሳይፈሩ (ሳይሳቀቁ) ትምህርታቸውን ስለሚማሩ ነው፡፡ በነጠላ ጾታ ትምህርት ቤት የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከእነሱ በፊት በትምህርታቸውና በትምህርት ቤት እንቅስቃሴያቸው ውጤታማ የሆኑ የሴት ተማሪዎች ስለሚያዩና እነሱን ለመምሰል ስለሚጥሩ ተማሪዎቹ በጥሩ ሁኔታ ትምህርታቸውን ይከታተላሉ፡፡ ከተማሪዎቹ በተጨማሪ ሴቶች ብቻ የሚማሩበት ትምህርት

ቤት ያሉ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች አብዛኛዎቹ ሴቶች ስለሆኑ ተማሪዎቹ ገና በትምህርት ቤት እያሉ የሴቶችን ውጤታማነት እያዩ ስለሚማሩ እና እንደ እነሱ የመሆን ጉጉት ስለሚያድርባቸው በተገቢው መልኩ ትምህርታቸውን ይከታተላሉ በማለት Jimenez and Lock head (1989) ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከላይ ተደጋግሞ እንደተገለጸው ሴቶቸችና ወንዶች አብረው የሚማሩበት ትምህርት ቤት የሚማሩ ሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒም ሴቶችና ወንዶች ተቀላቅለው በሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ የተሻሉ ሆነው መገኘታቸው ተጠቁሟል፡፡ ነገር ግን ጥናቶቹ የተካሄዱት አንደኛው በግል ትምህርት ቤት ሌላው ደግሞ በአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ በመሆኑ ውጤቱ እንደዚህ የሆነው ተማሪዎቹ የትምህርትን ጥቅም ከተረዱ ቤተሰብ በመምጣታቸውና የተማሪዎቹ እድሜ ዝቅተኛ ስለሆነ ነው የሚል ጥያቄ ስለሚያስነሳ የጥናቱን ውጤት ትክክለኛነት ግምት ውስጥ ይጥለዋል፡፡ ይህም ሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለውጥ የሚኖረው በአካባቢያቸው ያለውን የማህበረሰብ አመለካከት መረዳት በሚጀምሩበት በኩርድና ጊዜያቸው ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤት ባሉበት ወቅት ነው (Betz and Fitzegerald 1987)፤ ሚለው ሀሳብ ጋር ስለሚጣረስ ነው፡፡

## 2.4.4 የጾታ ልዩነትና ለራስ የሚሰጥ ግምት (Self-esteem) በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ያለው ሚና

በራስ የመተማመን ስሜት ከጾታ ልዩነት አንጻርና ከትምህርት ተሳትፎ ጋር ያለውን ግንኙነት የመረመሩ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ የተገኘው ውጤትም ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ ያሉ ሴት ተማሪዎች ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ከወንድ አቻዎቻቸው ጋር ሲነጻጸር በጣም አነስተኛ እንደሆነ ነው፡፡

ሴቶችና ወንዶች አብረው በሚማሩበት ትምህርት ቤት የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የሚታየው በክፍል ውስጥ ከወንድ ተማሪዎች ያነሰ ውጤትና ተሳትፎ ባላቸው ሴት ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን በትምህርታቸው ጎበዝ ከሆኑትና ክፍል ውስጥ በሚሳተፉት ሴት ተማሪዎችም ላይ ነው፤ (Betz and Fitzegerald 1987)፡፡

ሴት ተማሪዎች ለራሳቸው ያላቸው ግምት ዝቅ ያለበት ምክንያት፣ ማህበረሰቡ ለሴት ልጆች በሚሰጠው ዝቅተኛ ግምት ምክንያት እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ አመለካከት ለወንድ ተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜት ከፍተኛ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ወንድ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ቢሳሳቱ ድጋሚ ለመሞከር እድል ይጠይቃሉ እንጂ ተደናግጠው ተሳትፎ ከማድረግ አይታቀቡም፡፡ ሴት ተማሪዎች ግን በክፍል ውስጥ መልስ ሰጥተው ሲሳሳቱ ብቻ ሳይሆን ገና ብንመልስና ብንሳሳት ተማሪዎች ይስቁብናል የሚል ፍራቻና በራስ ያለመተማመን ስሜት ስለሚያድርባቸው ወደ ተሳትፎ አይገቡም፡፡

ሴት ተማሪዎች በራስ ያለመተመማመን ግምት በተሳትፏቸው ላይ ችግር የሚፈጥረው ከወንድ ተማሪዎች ጋር ሲማሩ ነው፡፡ ብቻቸውን በሚማሩበት ወቅት ግን ብንሳሳት ሌሎች ተማሪዎች ይስቁብናል የሚል ፍራቻ ስለማይኖርባቸው በክፍል ውስጥ ያላቸውን ችሎታ ተጠቅመው ለመሳተፍና ሰፊ የተሳትፎ ጊዜ ለመውሰድ ይጥራሉ፤ Jimenez and Lock head (1989)፡፡

ባጠቃላይ የጾታ ልዩነትን መሰረት ያደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በሴቶችና በወንድ ተማሪዎች መካከል የችሎታ ልዩነት ባይኖርም የአንድ ማህበረሰብ ባህል በሚፈጥረው አመለካከት፣ መምህራን ባላቸው የተለያየ የተማሪዎች አያያዝ (ትኩረት የመስጠት) ሁኔታና ሴት ተማሪዎች ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ማነስ የተነሳ በክፍለ ውስጥ ተሳትፎም ሆነ አጠቃላይ ውጤታቸው ላይ ልዩነት ይታያል፡፡

### የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩና ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ ያላቸውን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ልዩነት መመርመር ነው፡፡ ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተዛምዶ ያላቸው በአማርኛ ቋንቋ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶችን ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡

የፋንቱ ደምሴ (1989) «የጾታ ልዩነት አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና» በሚል ርእስ የቀረበ ሲሆን የጾታ ልዩነት በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያለውን ሚና መመርመር በሚል አላማ የተዘጋጀ ነው፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ረገድ የሴትና የወንድ ጾታ መለያየት ምንም ሚና እንደሌለው ያመለክታል፡፡

ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያለው የበላይ ሰይድ (1992) ጥናት ነው፡፡በላይ ሰይድ «የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ» በሚል ርእስ ጥናት አቅርባለች፡፡ የጥናቱ አላማም በአማርኛ ትምህርት መማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ መስተጋብር የሴት ተማሪዎችን ቃላዊ ተራክቦ መጠን መመርመርና የመምህራን ትኩረት ከተሳትፏቸው ጋር ያለውን ግንኙነት መፈተሽ ነው፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ወንድ ተማሪዎች ከሴት ተማሪዎች የበለጠ ይሳተፋሉ የሚል ነው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች በተጨማሪ ከዚህ ጥናት ጋር በተዘዋዋሪ ቀረቤታ ያለው የማስተዋል ወርቁ (1999) ጥናት ሲሆን የማስተዋል ጥናት « በባህር ዳር ከተማ በሚገኙ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የስርአተ ጾታ አያያዝና የክፍል ውስጥ ፍተሻ አተገባበር» የሚል ሲሆን አላማውም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የስርአተ ጾታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበርን መመርመር ነው፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤትም መምህራን ሴትና ወንድ ተማሪዎችን የሚይዙበት መንገድ የተለያየ (ለወንድ ተማሪዎች ያደላ) መሆኑን ያሳያል ፡፡

በአጠቃላይ ጥናቶቹ የጾታ ልዩነት በትምህርት ተሳትፎ ላይ ያለውን ሚና፣ መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች ያላቸውን አመለካከትና በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የሴት ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በመመርመር ላይ ያተኮሩ መሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ ሆኖም ይህ ጥናት ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን ሲማሩና ሴቶች ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው ሲማሩ ያላቸውን የክፍል ውስጥ ቃላዊ ተራክቦ የሚመረምር መሆኑ፣ ጥናቱ በግል ትምህርት ቤት ላይ መካሄዱ፣ እንዲሁም በተጠኝዎች የክፍል ደረጃና በጊዜ ከተጠቀሱት ጥናቶች ይለያ

# ምእራፍ ሶስት

## የአጠናን ዘዴ

### 3.1 የአጠናን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ሴቶች ብቻቸውን እና ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ በሚማሩባቸው የግል ትምህርት ቤቶች የሴት ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በማነጻጸር መመርመር ነው፡፡ ጥናቱ የተነሰሳበትን የምርምር ጥያቄ በመመለስ አላማውን ከግብ ለማድረስ ይችል ዘንድም አይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴን (Qualitative Researceh)ና ገላጭ የመረጃ አተናተን ዘዴን (Descriptive Research) ተጠቅሟል፡፡ ጥናቱን ለማከናወን ጥቅም ላይ የዋሉት የናሙና አመራረጥና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 3.2 የጥናቱ መረጃ ምንጮች

ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የልደታ ማርያም ልጃገረዶች ትምህርት ቤትና በልደታ ማርያም ወንዶች ትምህርት ቤት በመማር እና ማስተማር ላይ በሚገኙ የ2004ዓ.ም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችና የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ነው፡፡

### 3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

#### 3.3.1 የጥናቱ ክልል ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው ክልል አዲስ አበባ ክልላዊ መስተዳድር ነው፡፡ የጥናቱ ክልል የተመረጠው አላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴን (Purposive Sampling Method) በመጠቀም ነው፡፡ አዲስ አበባ መስተዳድር የተመረጠበት ምክንያት አጥኚዋ በዚሁ ክልል በመምህርነት በማገልገሏ አስፈላጊውን መረጃና ሴቶች ብቻቸውን እና ሴቶችና ወንዶች ተቀላቅለው የሚማሩበት ትምህርት ቤት በቀላሉ አገኛለሁ ብላ በማመኗ ነው፡፡

### 3.3.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩና ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ ያላቸውን የክፍል ውስጥ ቃላዊ ተሳትፎ ልዩነት ለማወቅ በሁለቱ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎችን ማነጻጸር ዋና አላማው እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ ይህን አላማ ለመሳካትም አመቺ የናሙና አመራረጥ (Convince sampling method) ስልትን በመጠቀም የልደታ ማርያም የልጃገረዶች(ሴቶች ብቻ የሚማሩበት) ትምህርት ቤትና የልደታ ማርያም የወንዶች(ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ የሚማሩበት) ትምህርት ቤት ተመርጠዋል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ሁለቱም አይነት ትምህርት ቤቶች (ሴቶች ብቻቸውን የሚማሩበትና ሴቶችና ወንዶች አብረው የሚማሩበት ትምህርት ቤት) በአንድ ቦታና በቅርበት በመገኘቱ ምክንያት ነው፡፡

### 3.3.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ትምህርት ቤቱ ከተመረጠ በኋላ ቀጣዩ ተግባር የሚሆነው የክፍል ደረጃን መወሰንና ተጠኝዎችን መምረጥ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ዘጠነኛ ክፍል የአላማ ተኮር ናሙና አመራረጥ ስልትን (Purposive Sampling method) በመጠቀም ተመርጧል፡፡ የዚህም ምክንያት ወንድና ሴት ተማሪዎች ተቀላቅለው በሚማሩበት ጊዜም ሆነ ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩ በጾታቸው የተነሳ በክፍል ውስጥ ተሳትፎም ሆነ አጠቃላይ ትምህርታቸው ላይ ለውጥ የሚያሳዩት፣ በአካባቢያቸው የሚነሳውን የባህል ልዩነት መረዳት በሚጀምሩበት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ወይም በኩርድና ጊዜያቸው ነው ብለው Betz and Fetzegerald,(1987) የገለጹትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ስለዚህም ካሉት የሁለተኛ ደረጃ ክፍሎች መካከል የአስረኛና የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች የብሄራዊ ፈተና ተፈታኞች በመሆናቸው መረጃውን ለመሰብሰብ እንደልብ ላይገኙ ስለሚችሉ አልተመረጡም፡፡ ከቀሩት የዘነኛና የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ደግሞ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የብሔራዊ ፈተና ዝግጅት የሌለባቸው በመሆናቸውና ጀማሪ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በመሆናቸው ሁሉንም ትምህርት በእኩል ፍላጎት ይቀበላሉ ተብሎ በመታሰቡ ዘጠነኛ ክፍል ተመርጧል፡፡

### 3.3.4 የመምህራንና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

#### 3.3.4.1 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

የመምህራን የናሙና አመራረጥን በተመለከተ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ያሉት የዘጠነኛ ክፍል መምህራን ሁለት ናቸው፡፡ በሴቶቹ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል አንድ መምህርና ወንዶችና ሴቶች በሚማሩበት ደግሞ ያለው አንድ መምህር በመሆኑ ጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ዘዴን (comprehensive sampling method) በመጠቀም ሁለቱም ተመርጠዋል፡፡

#### 3.3.4.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ በተጠኝነት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አላማ ተኮር ናሙና አመራረጥ ስልትን (Purposive Sampling method) በመጠቀም መመረጣቸው ተገልጿል፡፡ የክፍሎቹ ብዛት ደግሞ ቀላል እጣ ንሞና (Simple Random Sampling) አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ተመርጠዋል፡፡ ይህም በሴቶቹ ትምህርት ቤት ካሉት ሶስት የዘጠነኛ ክፍሎች ውስጥ ሁለቱን ወንዶችና ሴቶች ከሚማሩበት ትምህርት ቤት ደግሞ ካሉት አራት ክፍሎች ውስጥ ሁለቱን በመውሰድ በጠቅላላው አራት ክፍሎች ተመርጠዋል፡፡ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ካሉት ክፍሎች ብዛት አንጻር አራት ናሙና መወሰዱ ናሙናው ወካይ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለምልከታው ከተመረጡ ምድቦች ውስጥ በሚገኙ በሴቶቹ ትምህርት ቤት ካሉት 113 የዘነኛ ክፍል ተማሪዎች 44 (40%ቱን) በመውሰድ እና ወንዶች ጋር ከሚማሩት ደግሞ ካሉት 51 ተማሪዎች 20(40%ቱን) ተማሪዎች የብድግ ብድግ ናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ተማሪዎቹ በቃለ መጠይቁ ላይ አልተሳተፉም፡፡

ሠንጠረዥ -1 የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች መረጃ

| ተ.ቁ | ሴክሽን | የሴት ተማሪዎች ብዛት | ድምር | የትምህርት ቤቱ ስም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 9B | 57 | 113 | ልደታ ማርያም ልጃገረዶች ትምህርት ቤት |
| 2 | 9C | 56 | | |
| 3 | 9A | 27 | 51 | ልደታ ማርያም የወንዶች(ወንዶችና ሴቶች አብረው የሚማሩበት) ትምህርት ቤት |
| 4 | 9D | 24 | | |

ከሠንጠረዥ- 1 ከቀረበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው ከሁለቱም ትምህርት ቤቶች የተመረጡት ሴክሽኖች ሁለት ሁለት ናቸው፡፡ ብቻቸውን የሚማሩት ተማሪዎች አጠቃላይ ብዛታቸው 113 ሲሆን ከወንድ ተማሪዎች ጋር የሚማሩት ተማሪዎች ብዛት ደግሞ 51 ነው፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጡት ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ናቸው፡፡ እነሱም በምስል ቀረጻ (Video recording) የሚታገዝ የክፍል ውስጥ ምልከታ (Observation)፣ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ሲሆኑ ለጥናቱ በዋናነት መረጃ ለመሰብሰብ የዋለው የክፍል ውስጥ ምልከታ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ በጥናቱ ውስጥ በአጋዥ መረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

### 3.4.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ

የክፍል ምልከታ የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ የክፍል ውስጥ ምልከታ የሚካሄደው ውስን የምልከታ ስልት በመጠቀም ነው፡፡ ውስን ምልከታ የሚባለው በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ከሚታዩት ክንውኖች

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ቀደም ብሎ የመከታተያ ቅጽ አዘጋጅቶ መከናኑን ወይም አለመከናወኑን በማየት መመዝገብ ነው (Richards and Nunan 1990) በማለት ገልጸዋል፡፡

የመከታተያ ቅጹ (checklist) የተለያዩ ምሁራን ያነሷቸውን ሀሳቦች ትወራዎች መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በአማካሪ ተገምግሞ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ ይህንን የምልከታ መከታተያ ቅጽ በመጠቀም በናሙናነት በተመረጡት አራት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የመምህርና ተማሪ ቃላዊ ተራክቦን ለመገምገም በእያንዳንዱ ክፍል ሶስት ጊዜ ያህል ምልከታ ተካሂዷል፡፡ ምልከታው የተካሄደው በአጥኚዋና በአንድ ረዳት ተመልካች ነው፡፡ረዳት ተመልካች ያስፈለገበት ምክንያት በክፍል ውስጥ የሚካሄደውን እያንዳንዱን ድርጊት አንድ ሰው ብቻውን ለመከታተል አስቸጋሪ ስለሚሆን ነው፡፡ ረዳት ተመልካቿ በቋንቋና ስነጽሁፍ መጀመሪያ ዲግሪ ያላትና የቋንቋ መምህር ስትሆን በተግባራዊ ስነልሳን የትምህርት ክፍልም ሁለተኛ ዲግሪዋን እየሰራች ትገኛለች፡፡ ከምልከታው በፊትም ረዳት ተመልካቿ ከአጥኚዋ ጋር ውይይት በማድረግ ስለጥናቱ አጠቃላይ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራት ተደርጓል፡፡

### 3.4.2 የምስል ቀረጻ

የክፍል ውስጥ ምልከታው በምስል ቀረጻ እንዲታገዝ ተደርጓል፡፡ ይህም በምልከታ ወቅት የተዘለሉ ሁኔታዎችን እንደገና ለማጤን ስለሚረዳ ነው፡፡ በመጀመሪያ ለአማርኛ መምህራኑ ስለጥናቱ አላማና ስለ ምስል ቀረጻው ሁኔታ በማስረዳትና መምህራኑ ለተማሪዎቹ እንዲያስረዱ በማድረግ ቀረጻው ተካሂዷል፡፡ በዚህ መሰረትም በሁሉም ክፍሎች ውስጥ ለሙከራ አንድ ጊዜ ቀረጻ የተካሄደ ሲሆን ዋናው ቀረጻ ደግሞ ምልከታው በተደረገባቸው ሁለት ክፍለ ጊዜዎች ተካሂዷል፡፡ በአጠቃላይ ለናመናነት በተመረጡት ክፍሎች ውስጥ ለሙከራ የተቀረጸውን ሳያካትት ለስምንት ጊዜ ያህል ቀረጻ ተካሂዷል፡፡ የስምንቱም የምስል ቀረጻ ወደ ጽሁፍ ተገልብጦ በአባሪነት ቀርቧል (አባሪ ሁለትን ይመልከቱ)፡፡

### 3.4.3 የጽሁፍ መጠይቅ

ጥናቱን ለማካሄድ በጥቅም ላይ ከዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አንዱ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ በጽሁፍ መጠይቁ ምሁራን ካካሄዷቸው ጥናቶችና ትውረቶች በመነሳት የመምህርና ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎን በተመለከተ መረጃ ያስገኛሉ ተብለው የታሰቡ ጥያቄዎች ተካተዋል፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ የተዘጋጀው ለተማሪዎች ነው፡፡ ጥያቄዎቹ ክፍትና ዝግ ሲሆኑ ብዛታቸው ዘጠኝ ነው (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)፡፡ መጠይቁ ተማሪዎቹ ከመሙላታቸው በፊት ለአማካሪ ቀርቦ አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ ከዚህ በኋላ ሴቶች ብቻ ከሚማሩበት ትምህርት ቤት 44(40%)፣ ከወንዶቹ ጋር ከሚማሩት 20(40%)ተማሪዎችን የብድግ ብድግ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ በመጠቀም ተማሪዎቹ ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡትን ተማሪዎች ወደ ቤተ መጻህፍት በመውሰድና አጥኚዋ ለተማሪዎቹ ስለመጠይቁ አስፈላጊውን ገለጻ በመስጠት መጠይቁን እንዲሞሉ አድርጋለች፡፡ ተማሪዎቹ የሞሉት መጠይቅም በጥናቱ ትንተና ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በመጨረሻም የተገኙት መረጃዎች በቁጥርና በመቶኛ በመተንተን አስፈላጊውን ማብራሪያ ተደርጎባቸዋል፡፡

### 3.4.4 ቃለ መጠይቅ

በዚህ ጥናት ውስጥ ቃለ መጠይቅ የቀረበዉ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ነው፡፡ ለመምህራኑ ቃለ መጠይቅ የተዘጋጀው ቁጥራቸው አናሳ በመሆኑ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን ጥያቄዎች ከጽሁፍ መጠይቅ ከማቅረብ ይልቅ በቃለ መጠይቅ የተሟላ መረጃ ማግኘት ይቻላል ተብሎ በመታመኑ፡፡ ቃለ መጠይቆቹ ከተለያዩ ትወራዎች በመነሳት በቋንቋ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ ስለሚታየው የመምህር ተማሪ ተራክቦና የተማሪዎች የተሳትፎ ሁኔታ መረጃ የሚያስገኙ ናቸው ተብሎ የታሰቡ ናቸው፡፡ የተዘጋጁት ጥያቄዎች ብዛታቸው አስር ሲሆን ሁሉም ክፍት ናቸው፡፡ ቃለ መጠይቁ ከመካሄዱ በፊት ጥያቄዎቹ ለአማካሪ ቀርበው አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል፡፡ በቃለ መጠይቁ ወቅት ከተዘጋጁት ጥያቄዎች በተጨማሪ ከጥያቄዎቹና መልሶቹ በመነሳት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ሀሳቦች ላይ ተጠኚ መምህሩ ምላሽ(ማብራሪያ) እንዲሰጡባቸው ተደርጓል፡፡ ለተጨማሪ መረጃ አባሪ አራትን ይመልከቱ፡፡

## 3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በክፍል ውስጥ ምልከታ፣ በምስል ቀረጻ፣ በቃለ መጠይቅና በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን አይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴ (Qualitative Researceh) እና ገላጭ የመረጃ አተናተን ዘዴ (Descriptive Research) በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ ሙሉ በሙሉ በትንተናው ውስጥ ያልተካተቱት መረጃዎች በአባሪ መልክ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተናና ውጤት

ይህ ክፍል በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች የሚተነተኑበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በምልከታ፣ በምስል ቀረጻ፣ በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የክፍል ውስጥ ምልከታ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በክፍል ውስጥ ምልከታ ሁሉንም ተግባር መከታተል አስቸጋሪ በመሆኑ ምልከታው በምስል ቀረጻ እንዲታገዝ ተደርጓል፡፡ ምልከታው ለአስራሁለት ክፍል ጊዜያት ያህል የተካሄዱል፡፡ ውጤት አሰጣጡ በምልከታው መከታተያ ቅጽ በቀረቡት ሀሳቦች መሰረት በጥያቄዎቹ ላይ የቀረቡት ሀሳቦች በክፍል ጊዜው ከተተገበሩ አዎ፣ ካልተተገበሩ ደግሞ አይደለም በሚለው ስር የድርጊቶቹን ክንውን ምልክት ( ✓) በማድረግ ነው፡፡ የተማሪዎቹ መጠይቅ በምርጫ መልክ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በመቶኛ የቀረቡ ሲሆን በምርጫ መልክ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምክንያት ተብለው የቀረቡት ጥያቄዎችና ቃለ መጠይቁ በትንተና መልክ ተገልጸዋል፡፡

## 4.1 በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩ ያላቸውን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሁኔታ ምን እንደሚመስል በተመለከተ

በምእራፍ ሁለት እንደተገለጸው ተራክቦ (ቃላዊ ተግባቦት) ሰዎች እርስ በርስ በንግግር (በቃል) የሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ነው፡፡ በዚህ ሂደት ሰዎች የተነገረውን ሀሳብ በመረዳት ምላሽ የሚሰጡበትም ነው፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ማንኛውም ትምህርት የሚተላለፈው በተራክቦ ነው፡፡ በተለይ በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ተራክቦ ወሳኝ ሚናን ይጫወታል፡፡ በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚካሄደው ተራክቦም በመምህሩና በተማሪዎች መካከል የሚከወን ነው (Levinson 1983)፡፡

ተራክቦ ተናጋሪና አድማጭ ያለበት የሁለትዮሽ ግንኙነት ነው፤ በመማርያ ክፍል ውስጥ የሚካሄደው ተራክቦም እንደዚሁ ተናጋሪና አድማጭ ያለበት ሲሆን ክፍል ውስጥ

በሚደረገው ተራክቦ የተራክቦው ተሳታፊዎች መምህሩና ተማሪዎች ናቸው፡፡ መምህሩና ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚኖራቸው ተራክቦ በሚከተሉት ፈርጆች ይገለጻል፤ እነዚህም ማስተማር (Lecturing)፣ መመለስ (answering)፣ መጠየቅ (Questioning)፣ ማሞገስ (Praising)፣ መተቸት (Criticizing) ናቸው (Sunderland 1994) ፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ተራክቦ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በማሳተፍ ለማስተማር ጠቀሜታ አለው፡፡

በዚህ ንኡስ ክፍልም ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን ሲማሩ በቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምን እንደሚመስል ለጥናቱ በተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ሠንጠረዥ -2 ሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት መልስ የመመለስና ጥያቄ የመጠየቅ ዝንባሌያቸውን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ | የታዩ ዝርዝር ነጥቦች | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1 | ለጥያቄዎች መልስ ለመመለስ በራሳቸው ፍላጎት በተደጋጋሚ እጃቸውን ያወጣሉ? | 6 | 0 |
| 2 | በራሳቸው ፍላጎት ጥያቄ ለመጠየቅ እጃቸውን ያወጣሉ? | 4 | 2 |
| 3 | በክፍል ውስጥ ሌሎች ተማሪዎች በሚመልሱት መልስ ላይ አስተያየት ይሰጣሉ? | 4 | 2 |
| 4 | ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ ይደናገጣሉ? | 0 | 6 |

ከሰንጠረዥ-2 መረዳት እንደሚቻለው ምልከታ በተደረገባቸው በስድስቱም ክፍለ ጊዜያት ተማሪዎቹ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት በራሳቸው ፍላጎት እቸውን አውጥተዋል፡፡ ያልገባቸውን ወይም ግልጽ ያልሆነላቸውን ሀሳብ ለመጠየቅ እጃቸውን ያወጡት በአራቱ ክፍለ ጊዜ ሲሆን በቀሪዎቹ ሁለት ክፍለ ጊዜያት በራሳቸው ፍላጎት ጥያቄ ሲያቀርቡ አልታዩም፡፡

ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሌሎች ተማሪዎች በሰጡት መልስ ወይም ሀሳብ ላይ አስተያየት ይሰጣሉ? ለሚለው ጥያቄ ምልከታ በተደረገባቸው ክፍለ ጊዜያት በአራቱ ክፍለ ጊዜ አስተያየት የሰጡ ሲሆን በቀሩት ሁለት ክፍለ ጊዜያት አስተያየት ሲሰጡ አልታዩም፡፡ ከምስል ቀረጻው የተገኘው መረጃም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡

ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ ይደናገጣሉ? ለሚለው ጥያቄ የተገኘው መረጃ ተማሪዎቹ መልስ በሚመልሱበት ጊዜ ሲሳሳቱ እንደማይደናገጡ ያስረዳል፡፡ በክፍል ውስጥ የተሳሳተ መልስ የሰጠች ተማሪ ተደናግጣ መልስ ከመስጠት ከመቆጠብ ይልቅ ድጋሚ ለመሞከር ጥረት እንደምታደርግ በመልከታም ሆነ በምስል ቀረጻው የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡

ባጠቃላይ ከምልከታውና ከምስል ቀረጻው የተገኘው መረጃ ተማሪዎቹ መልስ ለመመለስ በሚፈልጉበት ጊዜም ሆነ ጥያቄ ለመጠየቅ በሚፈልጉበት ጊዜ ያለምንም ፍርሀት እጃቸውን ያወጣሉ፡፡ መልስ በሚመልሱበት ጊዜ ሲሳሳቱም ምንም አይነት የፍርሃትም ሆነ የመደናገጥ ሁኔታ አይታይባቸውም፤ እንዲያውም የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ ከመፍራትና ከመደናገጥ ይልቅ መልሰው ለመሳተፍ እንደሚጥሩ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ- 3 ሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት መልስ የመመለስና ጥያቄ የመጠየቅ ዝንባሌያቸውን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | በመጠየቁ ላይ የቀረቡ ጥያቄዎችና አማራጮች | የተገኙ መልሶች በቁጥርና በመቶኛ | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ % |
| 1 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ--------- | | |
| | ሀ. እሳተፋለሁ | 29 | 65.9% |
| | ለ. አልሳተፍም | 0 | 0% |
| | ሐ. አልፎ አልፎ | 15 | 34.1% |
| 3 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በተደጋጋሚ በራስ ተነሳሽነት እጅ በማውጣት ትመልሻለሽ? | | |
| | ሀ. እመልሳለሁ | 25 | 56.8% |
| | ለ. አልመልስም | 12 | 27.2% |
| | ሐ. አልፎ አልፎ | 7 | 16% |
| 4 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በራስሽ ተነሳሽነት ላልተረዳሽው ሀሳብ ጥያቄ ታቀርቢያለሽ? | | |
| | ሀ. እጠይቃለሁ | 25 | 56.8% |
| | ለ. አልጠይቅም | 9 | 20.5% |
| | ሐ. አልፎ አልፎ | 10 | 22.7% |
| 5 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የተሳሳተ መልስ ስትመልሺ ትፈሪያለሽ? | | |
| | ሀ. እፈራለሁ | 5 | 11.4% |
| | ለ. አልፈራም | 39 | 88.6% |

በሰንጠረዥ -3 በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ትሳተፊያለሽ? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ 65.9% ያህሉ እሳተፋለሁ፣ 34.1% ያህሉ ደግሞ አልፎ አልፎ እሳተፋለሁ ብለው መልሰዋል፡፡ ተማሪዎቹ እሳተፋለሁ ወይም አልፎ አልፎ እሳተፋለሁ ያሉበት ምክንያት ምንድን ነው? ተብሎ

በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረት በክፍል ውስጥ እንዲሳተፉ ያደረጋቸው ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስለሆነ የሚፈልጉትን ሀሳብ ያለጭንቀት መግለጽ ስለሚያስችላቸው፣ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ስለሚቀላቸውና በቋንቋው መሳተፋቸው ለወደፊት ሰው በተሰበሰበበት ቦታ ለመናገር የሚያስችል ጠቀሜታ እንዳለው በመረዳታቸው መሆኑን አመልክተዋል፡፡ አልፎ አልፎ እንሳተፋለን ያሉት ተማሪዎች ደግሞ መምህሩ ብዙ ጊዜ እድል የሚሰጡት ለጎበዝ ተማሪዎች በመሆኑ፣ ብዙ የማያቋቸው የአማርኛ ቃላት በመኖራቸውና ሀሳባቸውን የመግለጽ ችግር ስላለባቸው እንደሆነ አመልክተዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ በራሳቸው ፍላጎት በተደጋጋሚ እጅ በማውጣት ምላሽ የሚሰጡ ተማሪዎች 56.8%፣ 16% ያህሉ አልፎ አልፎ እጅ በማውጣት የሚመልሱ ሲሆኑ 27.2% ያህሉ ደግሞ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ በራሳቸው ፍላጎት እጃቸውን በማውጣት ምላሽ የሚሰጡ አይደሉም፡፡ በራሳቸው ተነሳሽነት ላልተረዱት ሀሳብ ጥያቄ የሚያቀርቡ ተማሪዎች 56.8%፣ አልፎ አልፎ የሚጠይቁት 12.7% ሲሆኑ 20.5% ያህሉ ደግሞ በራሳቸው ፍላጎት ላልገባቸው ሀሳብ ጥያቄ የሚያቀርቡ አይደሉም፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የተሳሳተ መልስ ስትመልሽ ትፈሪያለሽ? ለሚለው ጥያቄ አልፈራም ያሉ ተማሪዎች ብዛት 88.6% ሲሆኑ እፈራለሁ ያሉ ተማሪዎች ደግሞ 11.4% ናቸው፡፡ ለሰጡት ምላሽ ምክንያታቸው ምን እንደሆነ እንዲመልሱ በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረት የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ ማይደናገጡት መምህሩ በተማሪዎች ፊት ስለማያሳፍሯቸው፣ በድጋሚ እንዲሞክሩ ስለሚያበረታቷቸውና ሁሉም ሴቶች በመሆናቸው ሰለሚግባቡ የሚያስፈራቸውም ሆነ የሚያስደነግጣቸው ነገር ስለሌለ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ እንፈራለን ያሉት ደግሞ በተማሪ ፊት ቆሞ መናገር ስለሚያስፈራቸውና የማያውቋቸው የአማርኛ ቃላት በመኖራቸው የተነሳ እንሳሳታለን የሚል ፍራቻ ስለሚያድርባቸው መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ከመምህሩ ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት ለሚቀርብላቸው ጥያቄ መልስ እንደሚሰጡ፣ ላልገባቸው ሀሳብ ገለጻ እንዲደረግላቸው ጥያቄ እንደሚያቀርቡና በክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንደሆኑ ያስረዳል፡፡ መምህሩ ለዚህ ምክንያት ብለው ያቀረቡት ተማሪዎቹን እንደ አባት

ሆነው ስለሚቀርቧቸውና በነጻነት እንዲናገሩ ስለሚያደርጓቸው፣ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ስለማይቆጧቸውና በራሳቸው ተነሳሽነት ጥያቄ እንዲጠይቁ ስለሚያበረታቷቸው መሆኑን ገልጸ ዋል፡፡ ሴት ተማሪዎች መልስ በሚመልሱበት ጊዜም ሆነ ጥያቄ በሚጠይቁበት ጊዜ ይፈራሉ? ተብሎለቀረበላቸው ጥያቄም መምህሩ አዎ ይፈራሉ! ብለው የመለሱ ሲሆን ለዚህ ምክንያቱ ከሰው ፊት ደፍሮ ለመናገር ብሳሳትስ የሚል ፍራቻ ስላለባቸውና ማህበረሰቡ ለሴቶች የሚሰጠውን ግምት ከቤተሰቦቻቸው ይዘው ስለሚመጡ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ይህ ደግሞ በምልከታ ሴቶች በክፍል ውስጥ እንደሚሳተፉ ከተሚያመለክተው ውጤት ጋርም ሆነ ከጽሁፍ መጠይቁ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ እንሳተፋለን ብለው ከመለሱት መልስ ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ባጠቃላይ ከምልከታ፣ ከምስል ቀረጻውና ከመጠይቆቹ የተገኙት መረጃዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ በራሳቸው ተነሳሽነት መልስ ለመስጠት በተደጋጋሚ እጃቸውን ያወጣሉ፣ ላልተረዱት ወይም እንዲብራራላቸው ለሚፈልጉት ሀሳብ ጥያቄ ለማቅረብ በራሳቸው ፍላጎት እጃቸውን ያወጣሉ፣ በክፍል ውስጥ ሌሎች ተማሪዎች በሰጡት መልስ ላይ አስተያየት ይሰጣሉ፣ የተሳሳተ መልስ በሚመልሱበት ጊዜም የመደናገጥና የመረበሽ ሁኔታ አይታይባቸውም የሚል ውጤት አስገኝተዋል፡፡ ይህ ደግሞ Bank and Hill(1996) ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ያለፍርሀት በክፍል ውስጥ ይሳተፋሉ ብለው ከደረሱበት የጥናት ውጤት ጋር የሚዛመድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሠንጠረዥ- 4 መምህራን በክፍል ውስጥ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ ውጤት

| ተ.ቁ | የታዩ ዝርዝር ነጥቦች | ተተግብሯል | አልተተገበረም |
|---|---|---|---|
| 5 | ተማሪዎቹ በፍላጎታቸው መልስ ለመመለስ እጃቸውን ሲያወጡ መምህሩ ያለማዳላት እድል ይሰጣሉ? | 4 | 2 |
| 6 | ተማሪዎቹ መልስ እንዲመልሱ እጃቸውን ላላወጡ ተማሪዎች መምህሩ እድል ይሰጣሉ? | 2 | 4 |
| 7 | ተማሪዎቹ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እጃቸውን በሚያወጡበት ጊዜ መምህሩ ያለማዳላት እድል ይሰጣሉ? | 4 | 2 |
| 8 | መምህሩ ትክክለኛ መልስ ለሚሰጡ ተማሪዎች ማበረታቻ ይሰጣሉ? | 6 | 0 |
| 9 | ተማሪዎች በሚሳተፉበት ጊዜ መምህሩ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ ይገባሉ? | 4 | 2 |

ተማሪዎቹ መልስ ለመመለስ እጃቸውን ሲያወጡ መምህሩ በአራቱ ክፍለ ጊዜ እድል የሰጡት ያለማዳላት ነው፡፡ ይህም ከፊትም፣ከኋላም፣ከመካከልም... ወዘተ ለሚቀመጡ ተማሪዎች እድል እንደሰጡ ከምስል ቀረጻው የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡ በቀሩት ሁለት ክፍለ ጊዜያት ግን እድል የሰጡት ለተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ ነው፡፡ መምህሩ በተደጋጋሚ መልስ እንዲመልሱ እድል የሚሰጧቸው ተማሪዎች ከአብዛኛዎቹ ተማሪዎች በፍጥነት እጃቸውን የሚያወጡና ወደ ተሳትፎው የሚገቡ ናቸው፡፡ ይህንንም መረጃ ከምስል ቀረጻው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ መምህሩ ለሚጠየቁት ጥያቄ እጃቸውን ላላወጡ ተማሪዎች መልስ እዲመልሱ እድል የሰጡት በሁለቱ ክፍለ ጊዜያት ብቻ ሲሆን ቀሪውን አራቱን ክፍለ ጊዜ እጃቸውን ላወጡ ተማሪዎች ብቻ እድል ሰጥተዋል፡፡ ተማሪዎቹ ላልተረዱት ሀሳብ ጥያቄ ለመጠየቅ እጃቸውን ሲያወጡ በአራቱ ክፍለ ጊዜ እድል ሲሰጡ ቀሪዎቹን ሁለት ክፍለ ጊዜ እድል ሳይሰጡ ቀርተዋል፡፡ ከምስል ቀረጻው የተገኘው መረጃ መምህሩ እድል ያልሰጡት

ክፍለ ጊዜው በማለቁ ምክንያት በመሆኑ ጥያቄውን ለቀጣይ ክፍለ ጊዜ እንደሚመልሱ ቃል መግባታቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡

መምህሩ በክፍል ውስጥ ባለው የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎቹ በሚሳተፉበት ጊዜና ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በሚመልሱበት ጊዜ ተማሪዎቹን አበረታተዋል፡፡ ተማሪዎቹ ንግግር ሲያደርጉና መልስ ሲሰጡ በአራቱ ክፍለ ጊዜያት በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ንግግራቸውን አቋርጠዋል፡፡ ቀሪዎቹን ሁለት ክፍለ ጊዜያት ግን የተማሪዎቹን ንግግር ሳያቋርጡ እስከ መጨረሻው ሲያዳምጡ ነበር፡፡ ከምስል ቀረጻው የተገኘው መረጃ መምህሩ ተማሪዎቹ በሚናገሩበት ጊዜ መልሱ ሳይጠፋቸውና ሳይሳሳቱ ዝም ብለው በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ተማሪዎቹ የጀመሩትን ሀሳብ ራሳቸው መምህሩ እንደሚጨርሱት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ መምህሩ ለሚያቀርቡት ጥያቄ ተማሪዎቻቸው እንዲመልሱ ያለ ማዳላት ሁሉንም ተማሪዎች ለማሳተፍ ጥረት አድርገዋል፡፡ ነገር ግን ምልከታ በተካሄደባቸው በሁሉም ክፍለ ጊዜያት ጥያቄ በተነሳ ቁጥር ለመሳተፍ የሚፈልጉና መምህሩም በየክፍለ ጊዜው ከአብዛኞቹ ተማሪዎች በበለጠ መልኩ የሚያሳትፏቸው ጥቂት ተማሪዎች እንዳሉ ከምስል ቀረጻው ከተገኘው መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ባጠቃላይ ከላይ የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የአማርኛ መምህሩ ሁሉንም ተማሪዎች ያለማዳላት እንዲሳተፉ የሚያደርጉት አልፎ አልፎ ነው፡፡ መምህሩ ጊዜ ለመቆጠብ በማለትና ሌሎች የተለያዩ ምክንያቶችን በመስጠት ምንባብ እንዲያነቡ፣ ንግግር እንዲያቀርቡ እና መልስ እንዲሰጡ የሚያደርጉት ጎበዝ ተማሪዎችን እንደሆነና ይህንንም እንደምሳሌ ከምስል ቀረጻው ማረጋገጥ እንደሚቻል ተማሪዎቹ በጽሁፍ መጠይቃቸው ላይ ያላቸውን አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ ከምልከታ የተገኘው መረጃም የሚያመለክተው ይህንን በመሆኑ መምህሩ በክፍል ውስጥ ለጎበዝ (ለተወሰኑ) ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች በተሻለ እድል እንደሚሰጡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ በሚያደርጉበት ጊዜ እኩል የተሳትፎ እድል የማይሰጣቸው ከሆነ የመሳተፍ ፍላጎታቸው እንደሚቀንስ በምእራፍ ሁለት ተብራርቷል፡፡

ሠንጠረዥ- 5 መምህሩ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት

| ተ.ቁ | በመጠየቁ ላይ የቀረቡ ጥያቄዎችና አማራጮች | የተገኙ መልሶች በቁጥርና በመቶኛ | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ% |
| 7 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ በክፍል ውስጥ የሁሉንም ተማሪዎች ስም በመጥራት እንድትሳተፉ ያደርጋሉ?<br>ሀ. ያደርጋሉ<br>ለ. አያደርጉም<br>ሐ. አልፎ አልፎ | 7<br>14<br>23 | 15.9%<br>31.8%<br>52.3% |
| 8 | የአማርኛ መምህራችሁ የተሳሳተ ምላሽ በምትሰጪበት ጊዜ ምን አይነት ምላሽ ይሰጡሻል?<br>ሀ. በድጋሚ እድትሞክሪ ማበረታታት<br>ለ. ድጋሚ እንድትሞክሪ እድል አለመስጠት | 30<br>14 | 68.2%<br>31.8% |
| 9 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ተማሪዎች በሚሳተፉበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ተሳትፎው እንዲቀንስ ያደርጋሉ?<br>ሀ. ያደርጋሉ<br>ለ. አያደርጉም<br>ሐ. አልፎ አልፎ | 19<br>10<br>15 | 43.2%<br>22.7%<br>34.1% |

የአማርኛ መምህራችሁ በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ስም በመጥራት እንድትሳተፉ ያደርጋሉ? ተብሎ በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረት 15.9% ያህሉ ያደርጋሉ ፣ 31.8% ያህሉ አያደርጉም፣ 52.3% ያህሉ ደግሞ መምህሩ አልፎ አልፎ ሁሉንም ተማሪዎች ለማሳተፍ ጥረት እንደሚያደርጉ አመልክተዋል፡፡ የአማርኛ መምህራችሁ የተሳሳተ መልስ በምትሰጪበት ጊዜ ምን አይነት ምላሽ ይሰጡሻል? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ 68.2% ያህሉ ድጋሚ እንድንሞክር ያበረታቱናል ሲሉ 31.8% ያህሉ ደግሞ ድጋሚ ለመሞክር

አድል እንደማይሰጧቸው አመልክተዋል፡፡ መምህሩ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ተሳትፎው እንዲቀንስ ያደርጋሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ 43.2% ያህሉ ያደርጋሉ፣ 34.1% ያህሉ አልፎ አልፎ ጣልቃ በመግባት ተሳትፎው እንዲቀነስ ያደርጋሉ፣ 22.7% ያህሉ ደግሞ ምንም ጣልቃ አይገቡም ብለው መልሰዋል፡፡ ከተገለጹት መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው የአማርኛ መምህሩ በክፍል ውስጥ በሚደረገው የተሳትፎ ሁኔታ የሁሉንም ተማሪዎች ስም በመጥራት እንዲሳተፉ የሚያደርጉት አልፎ አልፎ ነው፤ ተማሪዎቹ የተሳሳተ ምላሽ በሚመልሱበት ጊዜ ድጋሚ እንዲሞክሩ እድል ይሰጧቸዋል፤ ተማሪዎች በሚሳተፉበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት በተወሰነ መልኩ ተሳትፎው እንዲቀንስ ያደርጋሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ከመምህሩ ጋር የተደረገው ቃለ መጠይቅ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ በተደጋጋሚ እድል የሚሰጡት ለምን አይነት ተማሪዎች ነው? ተብሎ በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረት መምህሩ ለሁሉም ተማሪዎች እድል ለመስጠት እንደሚሞክሩና እጃቸውን ለሚያወጡት ተማሪዎች ግን ቅድሚያ እንደሚሰጡ አስረድተዋል፡፡ ተማሪዎች መልስ በሚሰጡበት ጊዜ «እጅግ በጣም ጥሩ፣ በጣም ጥሩ፣ ጎበዝ!፣ ሀሳባችሁ ተደብቆ እንዳይቀር የመሰላችሁን ብትናገሩ መልካም ነው…ወዘተ. የሚሉ የማበረታቻ ቃላትን በመጠቀም እንዲመልሱ አደርጋለሁ» ብለዋል፡፡ የተሳሳተ መልስ በሚመልሱበት ጊዜም «ስህተታቸውን ራሳቸው እንዲያርሙት አደርጋለሁ፤ ይህንን የማደርገው በንግግር መሃል መሳሳት እንዳለ እንዲያውቁና ስህተትን ራስ ማረም እንደሚቻል እንዲረዱ ስለምፈልግ ነው» በማለት አስረድተዋል፡፡ ተማሪዎቹ በሚሳተፉበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ ይገባሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህሩ ተማሪዎቹ በሚመልሱበት ጊዜ ሲሳሳቱ ወደ ትክክለኛው መንገድ እንዲመጡ ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር ዝም ብለው የተማሪዎቹን ንግግር እንደማያቋርጡ አስረድተዋል፡፡

ባጠቃላይ ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን ሲማሩ ያላቸውን የተሳትፎ ሁኔታ ለመመርመር በተደረገው ጥረት ከምልከታ፣ ከቃለ መጠይቅና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ ሴት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት በራሳቸው ፍላጎት እጃቸውን በማውጣት ይመልሳሉ፣ ጥያቄዎችን ለመጠየቅም በራሳቸው ፍላጎት እጃቸውን ያወጣሉ፣ በተማሪዎች ፊት ቆመው ያለፍርሀት

ይናገራሉ፣ የተሳሳተ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜም ምንም አይነት ፍራቻ አይታይበቸውም የሚል ነው:: መምህሩ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቻቸው ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ያበረታቷቸዋል፣ የተሳሳተ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜም ድጋሚ እንዲሞክሩ እድል ይሰጧቸዋል፣ ሁሉንም ተማሪዎች እኩል እድል በመስጠት እንዲሳተፉ የሚያደርጉት ግን አልፎ አልፎ መሆኑን ከምልከታና ከመጠይቆቹ ከተገኙት መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል:: በተጨማሪም መምህሩ ተማሪዎቹ ንግግር ሲያደርጉ ጣልቃ በመግባት ንግግራቸውን እንደሚያቋርጧቸው መረዳት ተችሏል:: መምህሩ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ የሚገቡት ተማሪዎቹ እንዳይናገሩ ለማድረግ ወይም በሌሎች ተማሪዎች ፊት ለማሳፈርና እንዲሸማቀቁ ለማድረግ ሳይሆን የተማሪዎቹን ንግግር ለማጉላት የሚያደርጉት መሆኑን ተማሪዎቹ በቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ አመልክተዋል፣ ከመምህሩ ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅም ታውቋ ል:: ነገር ግን ይህ ተግባራቸው ተማሪዎቹን ስለሚያበሳጫቸው ንግግራቸውን እንዳይቀጥሉና ንግግራቸውን እንዳያብራሩ እንደሚያደርጋቸም ተማሪዎቹ በጽሁፍ መጠይቃቸው ላይ አመልክተዋል:: በመረጃ መሰብሰቢያዎቹ ከተሰበሰቡት መረጃዎችና ከተገኙት ውጤቶች ለመረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ከመምህራን በኩል የሚመጣባቸው ተጽእኖ ባለመኖሩ በክፍል ውስጥ ያለፍርሀት እንደሚሳተፉ ነው፤ ይህ ደግሞ Jimenez and Lock head(1998) ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከመምህራን የሚመጣ ጫናም ሆነ የወንድ ተማሪዎች ተጽእኖ ባለመኖሩ የተነሳ በነጻነት ይሳተፋሉ፤ ካሉት ሀሳብ ጋር ይመሳሰላል::

## 4.2 በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምን እንደሚመስል በተመለከተ

በምእራፍ ሁለት ላይ በስፋት እንደተገለጸው ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ ያላቸውን የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ በተመለከተ የተለያዩ ጥናቶች ተካሂደዋል:: ከእነዚህም መካከል ሁለቱ እንደሚከተለው ቀርበዋል:: ሴቶችና ወንዶች አብረው በሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ ሴት ተማሪዎች ጥያቄ በሚጠየቁበት ጊዜ ምላሽ አይሰጡም፣ አንዳንዴ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ መልሳቸው በጣም አጭርና ያልተሟላ ነው (Sunderland 1992):: በተመሳሳይ መልኩ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያለውን የመምህር ተማሪን ተራክቦ ለመመርመር በታንዛንያ፣ በማላዊ፣ በሩዋንዳ፣ በኬንያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት መምህራን ወንዶች ጋር ለሚማሩ ሴት ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረትና ማበረታቻ በጣም አነስተኛ እንደሆነና

በዚህም የተነሳ የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎም ሆነ አጠቃላይ የትምህርት ውጤታቸው ከወንድ ተማሪዎች ጋር ሲተያይ አነስተኛ መሆኑን Odaga and Henveld (1995) Kilo (1994)ን በመጥቀስ አመልክተዋል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ የKidane (2006) ጥናት ውጤት ሴትና ወንድ ተማሪዎች አንድ ላይ የሚማሩበት ትምህርት ቤት የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንድ ተማሪዎች የተሻለ እንደሆነ አረጋግጧል፡፡ በዚህ ንኡስ ክፍልም ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ጋር ሲማሩ በአማርኛ ቋንቋ ክፍል ጊዜ ተሳትፏቸው ምን ይመስላል? የሚለው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ- 6 ሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት መልስ የመመለስና ጥያቄ የመጠየቅ ዝንባሌያቸውን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘው ውጤት

| ተ.ቁ | የታዩ ዝርዝር ነጥቦች | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1 | ሴት ተማሪዎች ለጥያቄዎች መልስ ለመመለስ በራሳቸው ፍላጎት በተደጋጋሚ እጃቸውን ያወጣሉ? | 4 | 2 |
| 2 | ሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት ጥያቄ ለመጠየቅ እጃቸውን ያወጣሉ? | 0 | 6 |
| 3 | ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሌሎች ተማሪዎች በሚመልሱት መልስ ላይ አስተያየት ይሰጣሉ? | 0 | 6 |
| 4 | ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ ይደናገጣሉ? | - | - |

ከሠንጠረዥ- 6 መረዳት እንደሚቻለው ከወንድ ተማሪዎች ጋር ተቀላቅለው የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጃቸውን ያወጡት በአራቱ ክፍል ጊዜ ነው፡፡ ቀሪውን ሁለት ክፍል ጊዜ ግን በራሳቸው ፍላጎት እጃቸውን እያወጡ ሲሳተፉ አልታዩም፡፡ በክፍል ውስጥ ጥያቄ ለመጠየቅ በሚደረገው ሂደት ውስጥ ሴት ተማሪዎች ምልከታ በተደረገባቸው ስድስት ክፍል ጊዜዎች ውስጥ በአንዱም ጥያቄ አልጠየቁም፡፡

ሌሎች ተማሪዎች በሰጡት መልስ ላይም እንደዚሁ አስተያየት አልሰጡም፡፡ ሴት ተማሪዎች ምልከታ በተደረገባቸው ክፍለ ጊዜያት እጃቸውን በማውጣት ምላሽ የሰጡት በሁለቱ ክፍለ ጊዜ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ በዚህ ጊዜ የተመለሱት መልሶች ትክክል በመሆናቸው የተሳሳተ ምላሽ ሲሰጡና በዚህ የተነሳ የሚያሳዩትን መደናገጥና የመፍራት ሁኔታ በምልከታው ወቅት መረጃ ለማግኘት  አልተቻለም፡፡ ባጠቃላይ ከወንዶች ጋር የሚማሩት ሴት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ መልስ ለመመለስ እጃቸውን ያወጣሉ፡፡ ያልገባቸውን ነገር ለመጠየቅና ሌሎች ባነሱት ሀሳብ ላይ አስተያየት ለመስጠት እጃቸውን አያወጡም፡፡ ይህን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ- 7 ሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት መልስ የመመለስና ጥያቄ የመጠየቅ ዝንባሌያቸውን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | በመጠየቁ ላይ የቀረቡ ጥያቄዎችና አማራጮች | የተገኙ መልሶች በቁጥርና በመቶኛ | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ% |
| 1 | በአማርኛ ክፍለ ጊዜ-----------<br>ሀ. እሳተፋለሁ<br>ለ. አልሳተፍም<br>ሐ. አልፎ አልፎ | <br>5<br>2<br>13 | <br>25%<br>10%<br>65% |
| 3 | በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በተደጋጋሚ በራስሽ ተነሳሽነት እጅ በማውጣት ትመልሻለሽ?<br>ሀ. እመልሳለሁ<br>ለ. አልመልስም<br>ሐ. አልፎ አልፎ እመልሳለሁ | <br><br>4<br>7<br>9 | <br><br>20%<br>35%<br>45% |
| 4 | በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በራስ ተነሳሽነት ላልተረዳሽው ሀሳብ ጥያቄ ትጠይቂያለሽ?<br>ሀ. እጠይቃለሁ<br>ለ. አልጠይቅም<br>ሐ. አልፎ አልፎ | <br><br>5<br>7<br>8 | <br><br>25%<br>35%<br>40% |
| 5 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የተሳሳተ መልስ ስትመልሽ ትፈሪያለሽ?<br>ሀ. እፈራለሁ<br>ለ. አልፈራም | <br>3<br>17 | <br>15%<br>85% |

ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ከተሰበሰበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የሚሳተፉ ተማሪዎች 25%፣ የማይሳተፉት 10% ሲሆኑ አልፎ አልፎ የሚሳተፉ ደግሞ

65% ናቸው፡፡ ለተራ ቁጥር አንድ ለሰጠሽው መልስ ምክንያትሽ ምንድን ነው? ተብሎ ለተማሪዎቹ በቀረበው ጥያቄ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የሚሳተፉት ትምህርቱን በጣም ስለሚወዱት፣ የራሳቸው ቋንቋ በመሆኑ ሀሳባቸውን እንደልብ ለመግለጽ ስለሚያስችላቸውና በሚሳተፉበት ወቅት ከሚሰሩት ስህተት ተምረው ለወደፊት የመናገር ልምድ እንዲኖራቸው ስለሚፈልጉ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ አልፎ አልፎ የሚሳተፉ ተማሪዎች ለመመለስ እጃቸውን ሲያወጡ የመመረጥ እድል ስለማይኖራቸውና ሁልጊዜ የሚጠየቁትን ጥያቄዎች መልስ ስለማያውቁት ብንሳሳትስ ብለው ስለሚፈሩ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ አንሳተፍም ያሉ ተማሪዎች የማይሳተፉትበት ምክንያትም መልስ ስንመልስ ብንሳሳትና ሌሎች ተማሪዎች ቢስቁብንስ የሚል ፍራቻ ስላለባቸው እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት በተደጋጋሚ በራሳቸው ተነሳሽነት እጅ በማውጣት የሚመልሱ ተማሪዎች 20%፣ አልፎ አልፎ የሚመልሱት 45% ሲሆኑ 35% ያህሉ ደግሞ ለሚጠየቁት ጥያቄዎች እጅ በማውጣት ምላሽ የማይሰጡ ናቸው፡፡ ላልተረዱት ጥያቄዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ጥያቄ የሚያቀርቡ ሴት ተማሪዎች 25%፣ አልፎ አልፎ የሚጠይቁት 40% ሲሆኑ 35% ያህሉ ደግሞ በራሳቸው ተነሳሽነት ጥያቄ የማያቀርቡ ናቸው፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የተሳሳተ መልስ ስትመልሽ ሌሎች ተማሪዎች ሲመለከቱሽ ትፈሪያለሽ? ለሚለው ጥያቄ 15% ያህሉ እፈራለሁ፣ 85% አልፈራም ብለው መልሰዋል፡፡ ተማሪዎቹ አልፈራም ያሉበትን ምክንያት ሲገልጹ ሌሎቹ ተማሪዎች እንደነሱ ተማሪዎች በመሆናቸው እንደ ጓደኛ ስለሚቆጥሯቸው፣ በትምህርት ቤትም ሆነ በወላጆቻቸው በኩል በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲኖራቸው ተደርገው ስላደጉ፣ ቢሳሳቱ እንኳን ከስህተታቸው ለመማር ስለሚፈልጉና ሌሎቹም ተማሪዎች በመሆናቸው እነሱም ተነስተው በሚሞክሩበት ጊዜ ሊሳሳቱ እንደሚችሉ ስለሚገምቱ እነሱን ፈርተው ከመሳተፍ እንደማይቀሩ አመልክተዋል፡፡ እፈራለሁ ብለው የመለሱት ተማሪዎች ደግሞ ብንሳሳት ሌሎች ተማሪዎች ሊስቁብን ይችላሉ፣ የሚል ፍራቻ ስላለባቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከተዘረዘሩት ሀሳቦች ለመረዳት እንደሚቻለው ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ተሳትፏቸው ዝቅተኛ ነው፣ ለሚጠየቁት ጥያቄዎች እጅ በማውጣት የመመለስ ሁኔታቸውና ጥያቄ የማቅረብ ሁኔታቸው ዝቅተኛ ነው፤ የተሳሳተ መልስ

በሚመልሱበት ጊዜም ይፈራሉ፡፡ ባጠቃላይ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚደረገው የተሳትፎ ሂደት ውስጥ አልፎ አልፎ ይሳተፋሉ፣ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ መልስ ለመስጠትና ያልተረዱትን ሀሳብ ለመጠየቅ እጃቸውን በማውጣት የመጠየቅ ሁኔታቸው ዝቅተኛ ነው፣ የተሳሳተ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ግን የፍራቻ ሁኔታ አይታይባቸውም፡፡ ይህን በተመለከተ ከመምህሩ ጋር የተደረገው ቃለ መጠይቅ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ለመምህሩ ሴት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ይሳተፋሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ  በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች በተሻለ በክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተሳታፊ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የጠቆሙት ሴት ተማሪዎች የሚሰጣቸውን የክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ በትክክል አስበውበት ስለሚሰሩና ተዘጋጅተውበት ስለሚመጡ የሰሩትን ነገር በክፍል ውስጥ ለማቅረብ ስለሚፈልጉ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ሴት ተማሪዎች ያልተረዱትን ነገር ለመጠየቅ በራሳቸው ተነሳሽነት እጃቸውን ያወጣሉ? ለሚለው ጥያቄም መምህሩ የሰጡት ምላሽ ተማሪዎቹ ያልተረዱትን ሀሳብ ለመጠየቅም ሆነ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ቀድመው እጃቸውን እንሚያወጡ አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሌሎች በሰጡት መልስ ወይም ሀሳብ ላይ አስተያየት ለመስጠት በራሳቸው ፍላጎት እጃቸውን በማውጣት እንደሚሳተፉ ገልጸዋል፡፡ ይህ የመምህሩ መረጃ ግን ከምልከታ ከታየውና በጽሁፍ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር የተራራቀ ነው፡፡

ሴት ተማሪዎች መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ያላቸውን በራስ የመተማመን ሁኔታ በተመለከተ ያላቸውን ሀሳብ እንዲገልጹ በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረትም መምህሩ አብዛኛዎቹ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተወሰነ የማፈር ሁኔታ ይታይባቸዋል፤ ይህ ነገር የተሳሳተ መልስ በሚመልሱበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ መልስ መልሰው ሲጨበጨብላቸውም ይስተዋላል፡፡ ይህ ቢሆንም ሴት ተማሪዎች ብዙ ጊዜ ከወንዶቹ የተሻለ ግልጽና የተብራራ መልስ ስለሚሰጡ አልፎ አልፎ ቢሳሳቱ፡ እንኳን አብዛኛውን ጊዜ ወንድ ተማሪዎች ምንም አይነት የማሾፍም ሆነ የመሳቅ ምልክት አያሳዩም፤ አንዳንዴ የማሾፍም ሆነ የመሳቅ ነገር ሲያጋጥም ሴት ተማሪዎች እንዳይፈሩና ድጋሚ እንዲሞክሩ ለማድረግ እድል

እንደሚሰጧቸውና እንደሚያበረታቷቸው አስረድተዋል፡፡ ተማሪዎቹ ትክክለኛ መልስ ሲሰጡና ሲጨበጨብላቸው የሚያፍሩት ለምን ይመስልዎታል? ለሚለው ጥያቄም መምህሩ ተማሪዎቹ የማህበረሰቡ አካል እንደመሆናቸው መጠን ማህበረሰቡ ለሴት ልጅ ያለውን አመለካከት ስለሚያወቁና እነሱም በተወሰነ መለኩ ስለሚቀበሉት ነው፤ ሴት ተማሪዎች ሲሳሳቱም ሆነ ሲመልሱ አንዳንድ ተማሪዎች የመሳቅ ወይም የማሾፍ ነገር የሚያሳዩት ከዚሁ ጋር የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም ብለው መልሰዋል፡፡ ባጠቃላይ ከመምህሩ ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው ከወንዶች ጋር የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በራሳቸው ፍላጎት እጃቸውን በማውጣት ይመልሳሉ፣ ያልገባቸውን ሀሳብ ለመጠየቅ በራሳቸው ፍላጎት እጃቸወን ያወጣሉ፣ ሌሎች በሰጡት ሀሳብ ወይም መለስ ላይ አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መልስ በሚሰጡበት ጊዜና ማበረታቻ በሚደረግላቸው ጊዜ (ለምሳሌ ሲጨበጨብላቸው) የተወሰነ የማፈር ሁኔታ እንደሚታይባቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ውጤት በምእራፍ ሁለት እንደተጠቀመው በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል የተሳትፎ ልዩነት እንዲኖር የሚያደርገው የተማሪዎቹ ጾታ መለያት ሳይሆን ማህበረሰቡ ለሴቶች የሚሰጠው ዝቅተኛ ግምት የተነሳ የሴት ተማሪዎች በራስ ያለመተማመን ችግር ስለሚፈጥር ነው (Betz and Fitzegerald 1987) ካሉት ሀሳብ ጋር ይመሳሰላል፡፡

ከወንዶች ጋር የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት መልስ የመመለስና ጥያቄ የመጠየቅ ዝንባሌያቸውን በተመለከተ ከምልከታ፣ከምስል ቀረጻ፣ ከጽሁፍ መጠይቅና ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት መልስ ለመመለስ፣ ያልገባቸውን ሀሳብ ለመጠየቅና ሌሎች በሰጡት ሀሳብ ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያደርጉት የተሳትፎ ሁኔታ ዝቅተኛ እንደሆነ ማወቅ ተችሏል፡፡ ሴት ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ ሲሰጡ የሚያሳዩትን የመፍራትም ሆነ የመደናገጥ ሁኔታ በተመለከተ በምልከታው ወቅት በሴት ተማሪዎች የተመለሱት መልሶች በሙሉ ትክክለኛ በመሆናቸው የተነሳ መረጃ ማግኘት አልተቻቸለም፤ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ፍራቻ እንደሌለባቸው ሲያመለክት ከቃለመጠይቁ የተገኘው መረጃ ደግሞ መጠነኛ የሆነ ፍራቻ እንዳለባቸው ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ- 8 መምህሩ ለሴት ተማሪዎቻቸው የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ ውጤት

| ተ.ቁ | የታዩ ዝርዝር ነጥቦች | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 5 | ሴት ተማሪዎቹ በፍላጎታቸው መልስ ለመመለስ እጃቸውን ሲያወጡ መምህሩ ያለማዳላት እድል ይሰጣሉ? | 4 | 2 |
| 6 | መምህሩ እጃቸውን ላላወጡ ሴት ተማሪዎች መልስ እንዲመልሱ እድል ይሰጣሉ? | 0 | 6 |
| 7 | ሴት ተማሪዎች ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እጃቸውን በሚያወጡበት ጊዜ መምህሩ ያለማዳላት እድል ይሰጣሉ? | - | - |
| 8 | ትክክለኛ መልስ ለሚሰጡ ሴት ተማሪዎች ማበረታቻ ይሰጣሉ? | 2 | 4 |
| 9 | ሴት ተማሪዎች በሚናገሩበት/በሚሳተፉበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ያቋርጣሉ? | 0 | 6 |

ከሰንጠረዥ- 8 የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ሴት ተማሪዎች በፍላጎታቸው መልስ ለመመለስ እጃቸውን በሚያወጡበት ጊዜ መምህሩ በሁለቱ ክፍለ ጊዜያት ለሴትም ለወንድም ተማሪዎች እድል የሰጡ ሲሆን በቀሪዎቹ አራት ክፍለ ጊዜያት ግን እጃቸውን ላወጡ ወንድ ተማሪዎች ብቻ እድል ሰጥተዋል፡፡ እጃቸውን ላላወጡ ሴት ተማሪዎች ግን እድል ሲሰጡ አልታዩም፡፡ በምልከታው ወቅት ሴት ተማሪዎች ላልተረዱት ነገር ጥያቄ ለመጠየቅ እጃቸውን አላወጡም፤ መምህሩም ያልገባቸው ነገር ካለ ጥያቄ እንዲያቀርቡ ሲያበረታቱ አልታዩም፡፡ መምህሩ ትክክለኛ መልስ ለሰጡ ሴት ተማሪዎች ጥሩ እና በጣም ጥሩ የሚሉ ቃላትን በመጠቀም አበረታተዋል፤ የመለሱት መልስ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ከሆነ መልሳቸውን ግልጽ እንዲያደርጉ እንዳበረታቷቸው ከምልከታውና ከምስል ቀረጻው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ መምህሩ ሴት ተማሪዎች በሚናገሩበት ወይም በሚሳተፉበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት አላቋረጡም፡፡ እንዲያውም ተናግረው እስኪጨርሱ ከጠበቁ በኋላ ማብራሪያ የሚፈልግ የመሰላቸው ሀሳብ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጡ ድጋሚ በመጠየቅ ተማሪዎቹ የተብራራ ምላሽ እንዲሰጡ አድርገዋል፡፡ ባጠቃላይ ከምልከታውና ከምስል ቀረጻው የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው መምህሩ

ተማሪዎቻቸው መልስ እንዲመልሱ እጃቸውን ላወጡ ተማሪዎች እድል ይሰጣሉ፣ ትክክለኛ መልስ ለሚሰጡ ተማሪዎች ማበረታቻ ይሰጣሉ፣ ሴት ተማሪዎች በሚናገሩበት ጊዜ በንግግር መሀል ጣልቃ በመግባት ንግግራቸው እንዲቋረጥ አያደርጉም፡፡ ይህን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ- 9 መምህሩ በክፍል ውስጥ ለሴት ተማሪዎቻቸው የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት

| ተ.ቁ | በመጠይቁ ላይ የቀረቡ ጥያቄዎችና አማራጮች | የተገኙ መልሶች በቁጥርና በመቶኛ | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ% |
| 7 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የሴት ተማሪዎችን ስም በተደጋጋሚ በመጥራት እንድትሳተፉ ያደርጋሉ? | | |
| | ሀ. ያደርጋሉ | 3 | 15% |
| | ለ. አያደርጉም | 12 | 60% |
| | ሐ. አልፎ አልፎ | 5 | 25% |
| 8 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ በክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ መልስ እንዲሰጡ የሚያበረታቱት የትኞቹን ተማሪዎች ነው? | | |
| | ሀ. ወንዶቹን | 3 | 15% |
| | ለ. ሴቶቹን | 2 | 10% |
| | ሐ. ሁለቱንም | 15 | 75% |
| 9 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ሴት ተማሪዎች በሚሳተፉበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ተሳትፎው እንዲቀነስ ያደርጋሉ? | | |
| | ሀ. ያደርገሉ | 0 | 0% |
| | ለ. አያደርጉም | 17 | 85% |
| | ሐ. አልፎ አልፎ | 3 | 15% |
| 10 | የአማርኛ መምህራችሁ ሴት ተማሪዎች የተሳሳተ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ምን አይነት ምላሽ ይሰጣሉ? | | |
| | ሀ. በድጋሚ እንድትሞክሪ ማበረታታት | 17 | 85% |
| | ለ. ድጋሚ እንድትሞክሪ እድል አለመስጠት | 3 | 15% |

በሠንጠረዥ-9 ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የአማርኛ መምህራችሁ የሴት ተማሪዎችን ስም በተደጋጋሚ በመጥራት እንድትሳተፉ ያደርጋሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው

ጥያቄ 15% ያህሉ ያደርጋሉ፣ 25% ያህሉ አልፎ አልፎ፣ 60% ያህሉ ደግሞ አያደርጉም በማለት መልሰዋል፡፡ የአማርኛ መምህሩ በክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ መልስ እንዲመልሱ የሚያበረታቱት የትኞቹን ተማሪዎች ነው? ተብሎ በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረት 15% ያህሉ ወንድ ተማሪዎችን፣ 10% ያህሉ ደግሞ ሴት ተማሪዎችን፣ 75% ደግሞ ሁለቱንም (ሴቶቹንም ወንዶቹንም) ያለማዳላት እንደሚያሳትፉ አመልክተዋል፡፡
የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ሴት ተማሪዎች በሚሳተፉበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ተሳትፎው እንዲቀንስ ያደርጋሉ? ለሚለው ጥያቄ 85%ያህሉ አያደርጉም፣ 15% ያህሉ ደግሞ አልፎ አልፎ ጣልቃ ይገባሉ ብለው መልሰዋል፡፡ ሴት ተማሪዎች የተሳሳተ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ መምህራችሁ ድጋሚ እንድትሞክሩ እድል ይሰጧችኋል? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ በተመሳሳይ 85% ያህሉ ይሰጡናል፣ ሲሉ 15% ያህሉ ደግሞ ድጋሚ እንዲሞክሩ እድል እንደማይሰጧቸው አስረድተዋል፡፡

ባጠቃላይ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው ውጤት መምህሩ ወንዶቹንም ሴቶቹንም ተማሪዎች እኩል እድል በመስጠትና በማበረታታት እንዲሳተፉ ያደርጋሉ፣ ሴት ተማሪዎች በሚናገሩበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ተሳትፎው እንዲቀንስ አያደርጉም፣ የተሳሳተ መልስ በሚመልሱበት ጊዜ ድጋሚ እንዲሞክሩ እድል ይሰጧቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሴት ተማሪዎችን ስም በተደጋጋሚ በመጥራት እንዲሳተፉ አያደርጉም፡፡ ይህን በተመለከተ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መምህሩ በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከቃለ መጠይቅ የተገኘ ውጤት እንደሚያሳየው መምህሩ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ ወንድም ይሁን ሴት ቅድሚያ እጅ ላወጣ እድል ይሰጣሉ፡፡ ወንድና ሴት በአንድ ላይ እጃቸውን ካወጡ ግን ሴቷ እንድትመልስ ያደርጋሉ፡፡ እጃቸውን ላላወጡ ሴት ተማሪዎች እንዲመልሱ እድል ይሰጣሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁል ጊዜ የማይሳተፉና እጃቸውን የማያወጡ ሴት ተማሪዎች በሚኖሩበት ጊዜ ድንገተኛ ጥያቄ እንደሚጠይቁ ገልጸዋል፡፡ ሴት ተማሪዎች የተሳሳተ ምላሽ በሚሰጡበት ግዜም ምን ያደርጋሉ? ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ «ሴትም ሆኑ ወንድ ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ተሳስተሻል የሚል ቃል ሳልናገር መልሶቹን ትክክል የሆኑትንም ስህተት የሆኑትንም በሰሌዳ ላይ በመጻፍ የትኛው ስህተት የትኛው ደግሞ ትክክል መሆኑን ከለዩ በኋላ ድጋሚ እንዲሞክሩ እድል እሰጣለሁ እንጂ

ተሳስታችኋል አልላቸውም፤ በንግግራቸው መሃል ጣልቃ በመግባትም ንግራቸው እንዲቋረጥ አላደርግም፤ ተሳስታችኋል የማልለውና በንግራቸው መሃል ጣልቃ በመግባት ንግግራቸው እንዲቋረጥ የማላደርገው ድጋሚ ለመሳተፍ በሚፈልጉበት ጊዜ ልሳሳት እችላለሁ የሚል ፍራቻ እንዳያድርባቸው ለማድረግ ነው» ብለዋል፡፡ ከቃለ መጠይቁ ለመረዳት እንደሚቻለው መምህሩ ሴት ተማሪዎች ለመሳተፍ እጃውን በሚያወጡበት ጊዜ ከወንዶቹ በተሻለ እድል ይሰጧቸዋል፣ የተሳሳተ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ እንዲያፍሩ ወይም እንዲሸማቀቁ አያደርጓቸውም፣ እንዲያውም ድጋሚ እንዲሞክሩ ለማድረግ ተማሪዎቹን በማበረታታትና በንግግራቸው መሀል ጣልቃ ባለመግባት ተሳትፎቸው እንዲቀጥል ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ ቃለ መጠይቅ እንደምንረዳው ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ጋር በሚማሩበት ጊዜ መምህሩ ለሴት ተማሪዎችም ሆነ ለወንድ ተማሪዎች ያለማዳላት እድል ይሰጣሉ የሚል ነው፡፡ ይህም በምእራፍ ሁለት እንደተጠቀሰው መምህራን በክፍል ውስጥ ከሴት ተማሪዎች ይልቅ እንዲሳተፉ እድል የሚሰጡት ለወንድ ተማሪዎች ነው Bailey (1994) ካሉት ሀሳብ ጋር የተለየ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ባጠቃላይ ከምልከታ፣ ከምስል ቀረጻው፣ ከጽሁፍ መጠይቁና ከቃለ መጠይቁ ከተገኘው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው ከወንድ ተማሪዎች ጋር ተቀላቅለው የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት በራሳቸው ፍላጎት እጃቸውን የሚያወጡት አልፎ አልፎ ነው፣ ላልተረዱት ሀሳብ ማብራሪያ እንዲያገኙ ጥያቄ የማቅረብ ሁኔታቸው ዝቅተኛ ነው፣ መምህሩ ሴት ተማሪዎች እንዲሳተፉ ለማድረግ ያለማዳላት አድል ይሰጣሉ፣ በንግራቸውም መሀል ጣልቃ ባለመግባት ተናግረው እስኪጨርሱ በመጠበቅ ተሳትፎው ወይም ንግግሩ እንዲቀጥል ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ መምህሩ በክፍል ውስጥ ለሴት ለማሪዎቻቸው እንዲሳተፉ ሲያደርጉት የነበረው ጥረትና በምእራፍ ሁለት እንደተጠቆመው ደግሞ መምህራን ሴቶችና ወንዶች አብረው በሚማሩበት መማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎቻቸውን በእኩል ሲያበረታቱ፣ ጥያቄ ሲጠይቁ... ወዘተ አይታዩም፤ ምክንያቱም መምህራኑ የማህበረሰቡ አንድ አካል በመሆናቸው የሚያንጸባርቁትም ይኸኑ የማህበረሰቡን አመለካከት ነው (Sunderland 1994) ካሉት ሀሳብ ጋር የማይዛመድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 4.3. ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎችና ከወንዶች ጋር የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያላቸውን የተሳትፎ ልዩነት በተመለከተ

ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎችና ከወንዶች ጋር የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በቋንቋ ክፍለ ጊዜ የሚያሳዩትን የተሳትፎ ውጤት በተመለከተ በ4.1ና በ4.2 ስር ተዘርዝረዋል፡፡ በዚህ ንኡስ ክፍል ደግሞ የሁለቱ ውጤት እንደሚከተለው በማነጻጸር ተተንትኗል፡፡

ሠንጠረዥ- 10 ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን ሲማሩና ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ሲማሩ በራሳቸው ፍላጎት መልስ የመመለስና ጥያቄ የመጠየቅ ዝንባሌያቸውን በተመለከተ ከመልከታ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | የታዩ ዝርዝር ነጥቦች | ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩ | | ከወንድ ተማሪዎች ጋር ሲማሩ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | አይደለም | አዎ | አይደለም |
| 1 | ለጥያቄዎች መልስ ለመመለስ በራሳቸው ፍላጎት በተደጋጋሚ እጃቸውን የማውጣት ሁኔታ | 6 | 0 | 4 | 2 |
| 2 | በራሳቸው ፍላጎት ጥያቄ ለመጠየቅ እጃቸውን የማውጣት ሁኔታ | 4 | 2 | 0 | 6 |
| 3 | በክፍል ውስጥ ሌሎች ተማሪዎች በሚመልሱት መልስ ላይ አስተያየት የመስጠት ሁኔታ | 4 | 2 | 0 | 6 |
| 4 | ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ ይደናገጣሉ | 6 | 0 | - | - |

በሠንጠረዥ-10 እንደሚታየው ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን በሚማሩበት ጊዜ በራሳቸው ፍላጎት በስድቱም ክፍለ ጊዜ እጃቸውን ያወጡ ሲሆን ከወንዶች ጋር የሚማሩት ደግሞ

በአራቱ ክፍለ ጊዜ ብቻ እጃቸውን አውጥተዋል፡፡ ተማሪዎቹ በራሳቸው ፍላጎት ጥያቄ ለመጠየቅ እጃቸውን አውጥተዋል? ለሚለው ጥያቄ የተገኘው ውጤት ደግሞ ብቻቸውን የሚማሩት በአራቱ ክፍለ ጊዜያት ጥያቄ ለመጠየቅ እጃቸውን ያወጡ ሲሆን ከወንዶች ጋር የሚማሩት ሴት ተማሪዎች ደግሞ በአንዱም ክፍለ ጊዜ ጥያቄ ለመጠየቅ እጃቸውን አላወጡም፡፡ ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በተሰጠው ሀሳብ ላይ አስተያየት ለመስጠት በአራቱ ክፍለ ጊዜ እጃቸውን አውጥተዋል፤ ከወንዶች ጋር የሚማሩት ግን በአንዱም ክፍለ ጊዜ አስተያየት ሲሰጡ አልታዩም፡፡

ከምስል ቀረጻው የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው ከሚማሩ ተማሪዎች በተሻለ በክፍል ውስጥ ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በተደጋጋሚ እጃቸውን ያወጣሉ፡፡ ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ ሌሎች በሰጡት ሀሳብ ላይ አስተያየት ለመስጠት እጃቸውን የማውጣት ሁኔታቸው ከወንዶቹ ጋር ከሚማሩት ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን የሚማሩት የተሻለ ይሳተፋሉ፡፡ ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ የመደናገጥ ሁኔታ አይታይባቸውም፡፡ ከወንድ ተማሪዎች ጋር የሚማሩት ግን ምላሽ በሰጡባቸው ክፍለ ጊዜያት የመለሱት መልሶች በሙሉ ትክክል በመሆናቸው የተሳሳተ መልስ ሲመልሱና የሚያሳዩትን የመደናገጥም ሆነ የመፍራት ሁኔታ ለማየት አልተቻለም፡፡

ባጠቃላይ ከምልከታና ከምስል ቀረጻው የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ከሚማሩት ሴት ተማሪዎች በተሻለ በክፍል ውስጥ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እጃቸውን ያወጣሉ፤ ያልገባቸውን ሀሳብ እንዲብራራላቸው በራሳቸው ፍላጎት እጃቸውን በማውጣት ይጠይቃሉ፤ ሌሎች በሰጡት ሀሳብ ላይም አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ- 11 ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩና ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ በራሳቸው ፍላጎት መልስ የመመለስና ጥያቄ የመጠየቅ ዝንባሌያቸውን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | በመጠይቁ ላይ የቀረቡ ጥያቄዎች አማራጮች | የተገኙ መልሶች በቁጥርና በመቶኛ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩ | | ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ --------<br>ሀ. እሳተፋለሁ<br>ለ. አልሳተፍም<br>ሐ. አልፎ አልፎ | <br>29<br>0<br>15 | <br>65.9%<br>0%<br>34.1% | <br>5<br>2<br>13 | <br>25.%<br>10%<br>65% |
| 3 | በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ለሚጠየቁ ጥያቄዎችና መልስ ለመስጠት በተደጋጋሚ እጅሽን በማውጣት ትመልሻለሽ?<br>ሀ. እመልሳለሁ<br>ለ. አልመልስም<br>ሐ. አልፎ አልፎ | 25<br>12<br>7 | 56.8%<br>27.2%<br>16% | 4<br>7<br>9 | 20%<br>35%<br>45% |
| 4 | በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ላልተረዳሽው ሀሳብ በራስሽ ተነሳሽነት ጥያቄ ታቀርቢያለሽ?<br>ሀ. አቀርባለሁ<br>ለ. አላቀርብም<br>ሐ. አልፎ አልፎ | 25<br>9<br>10 | 56.8%<br>20.5%<br>22.7% | 5<br>7<br>8 | 25%<br>35%<br>40% |
| 5 | በአማርኛ ቋንቋ የተሳሳተ መልስ ስትመልሽ ትፈሪያለሽ?<br>ሀ. እፈራለሁ<br>ለ. አልፈራም | 5<br>39 | 11.4%<br>88.6% | 3<br>17 | 15%<br>85% |

ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ብቻቸውን በሚማሩ ሴት ተማሪዎችና ከወንዶች ጋር በሚማሩት ሴት ተማሪዎች መካከል የተሳትፎ ልዩነት አለ፡፡ ብቻቸውን የሚማሩት 65.9% ያህሉ እንሳተፋለን ሲሉ ከወንዶቹ ጋር የሚማሩትም 25% ያህሉ እንሳተፋለን በማለት መልሰዋል፡፡ ብቻቸውን የሚማሩት አልሳተፍም የሚል መልስ አልሰጡም፡፡ 10% ያህል

ከወንዶች ጋር የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ግን እንደማይሳተፉ ገልጸዋል፡፡ ብቻቸውን የሚማሩት ሴት ተማሪዎች 34.1% ያህሉ አልፎ አልፎ እንሳተፋለን ሲሉ 65% ያህሉ ከወንዶች ጋር የሚማሩትም አልፎ አልፎ እንደሚሳተፉ አመልክተዋል፡፡ ባጠቃላይ መረጃው በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ከሚማሩ ሴት ተማሪዎች የተሻለ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ያሳያል፡፡ አልፎ አልፎ በሚሳተፉት ተማሪዎች መካከል ግን የተወሰነ ልዩነት መኖሩን መገንዘብ ተችሏል፡፡

በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በራስሽ ተነሳሽነት በተደጋጋሚ እጅ በማውጣት ትመልሻለሽ? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ ብቻቸውን የሚማሩት 56.8% ያህሉ እመልሳለሁ፣ 27.2% ያህሉ አልመልስም፣ 16% ያህሉ አልፎ አልፎ እመልሳለሁ፤ ብለው የመለሱ ሲሆን ከወንዶች ጋር የሚማሩት ደግሞ 20% ያህሉ እመልሳለሁ፣ 35% ያህሉ አልመልሰም፣ 45% ያህሉ አልፎ አልፎ እመልሳለሁ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ከሚማሩት ሴት ተማሪዎች የተሻለ እንደሚሳተፉ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በራሳቸው ተነሳሽነት ላልተረዱት ሀሳብ ጥያቄ የማቅረብ ሁኔታቸውን በምናይበት ጊዜም ብቻቸውን የሚማሩት 56.8% ያህሉ እጠይቃለሁ፤ 20.5% ያህሉ አልጠይቅም፣ 22.7% ያህሉ አልፎ አልፎ እጠይቃለሁ ሲሉ ከወንዶች ጋር የሚማሩት ተማሪዎች ደግሞ 25% ያህሉ እጠይቃለሁ፣ 35% ያህሉ አልጠይቅም፣ 40% ያህሉ አልፎ አልፎ እጠይቃለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚህ ጥያቄ ከተገኘው ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ጋር ከሚማሩት የተሻለ በራሳቸው ፍላጎት ላልተረዱት ሀሳብ ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ ባጠቃላይ ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ጥያቄ ለመመለስ እጅ በማውጣትም ሆነ ላልተረዱት ሀሳብ ጥያቄ ለማቅረብ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከወንድ ተማሪዎች ጋር ከሚማሩት ሴት ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸሩ የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በክፍል ውስጥ አጠቃላይ የተሳትፎ ሁኔታቸውን ለማወቅ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ትሳተፋለችሁ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽም ብቻቸውን የሚማሩት ከወንዶች ጋር ከሚማሩት የተሻለ ተሳታፊ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡ የተሳሳተ መልስ ስትመልሽ ትፈሪያለሽ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች 88.6% ያህሉ አልፈራም፣

11.4% ያህሉ እፈራለሁ፣ ብለው ሲመልሱ ከወንድ ተማሪዎች ጋር አብረው የሚማሩት ደግሞ 85% ያህሉ አልፈራም፣ 15% ያህሉ ደግሞ እፈራለሁ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ መረጃ ብቻቸውን የሚማሩት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ከሚማሩት ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸሩ የተሳሳተ መልስ በሚመልሱበት መጠነኛ የሆነ ልዩነት እንዳላቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ እንፈራለን ያሉት ተማሪዎች ቁጥር ከወንድ ተማሪዎች ጋር ከሚማሩት ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን የሚማሩት ሴት ተማሪዎች ቁጥር ትንሽ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህን በተመለከተ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ከመምህሩ ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ብቻቸውን የሚማሩትን ሴት ተማሪዎች የሚያስተምሩት መምህር ተማሪዎቻቸው በክፍል ውስጥ ለሚያቀርቡት ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት እጃቸውን ያወጣሉ፣ ያልገባቸው ሀሳብ በሚኖርበት ጊዜ በራሳቸው ፍላጎት እጃቸውን ያወጣሉ፣ ባጠቃላይ በክፍል ውስጥ በሚደረገው የተሳትፎ እንቅስቃሴ ተሳታፊ ናቸው በማለት አስረድተዋል፡፡ ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው የሚማሩበት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምህርም በበኩላቸው ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ከወንድ ተማሪዎች በተሻለ እጃቸውን ያወጣሉ፣ ግልጽ ያልሆነላቸው ሀሳብም እንዲብራራላቸው በራሳቸው ፍላጎት እጃቸውን ያወጣሉ፣ በክፍል ውስጥ በሚደረገው የተሳትፎ ሁኔታ ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚያደርጉት ሴት ተማሪዎች ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ሴት ተማሪዎች የተሳሳተ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ይፈራሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሴቶችን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር ተማሪዎቻቸው በክፍል ውስጥ የተሳሳተ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ምንም አይነት የፍራቻ ሁኔታ እንደማይታይባቸውና ድጋሚ ለመሞከርም እድል እንደሚጠይቁ ሲያመለከቱ ወንዶችና ሴቶች የሚያስተምሩት መምህር ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መልስ በሚመልሱበት ጊዜ ሲጨበጨብላቸው እንኳን ይፈራሉ፣ ይህ የመጣው ከማህበረሰቡ ተጽእኖ የተነሳ ነው፤ ነገር ግን በክፍል ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ትክክለኛ መልስ የሚሰጡት ሴት ተማሪዎች በመሆናቸው ሲሳሳቱ እንደ ትልቅ ነገር ተቆጥሮ አይሳቅባቸውም፡፡ አልፎ አልፎ የመሳቅ ሁኔታ ሲያጋጥምም መምህራኑ የሚስቁትን ተማሪዎች ስለሚቆጧቸው ሴቶቹ ፈርተው ከመሳተፍ የሚታቀቡበት አጋጣሚ አይታይም፡፡ ባጠቃላይ ከመምህራኑ የተገኘው መረጃ ሴት ተማሪዎች ብቻቸውን ሲማሩም ሆነ ከወንዶች ጋር ሲማሩ በክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው ላይ ልዩነት የለም፡፡ የተሳሳተ መልስ በሚመልሱበት ጊዜ ግን ብቻቸውን የሚማሩ ሴት

ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ከሚማሩት ሴት ተማሪዎች የተሻለ የመረጋጋትና ድጋሚ ለመሳተፍ የመፈለግ ሁኔታ እንደሚታይባቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ባጠቃላይ ከምልከታ፣ ከምስል ቀረጻ፣ ከጽሁፍ መጠይቅና ከመምህሩ ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ከሚማሩ ሴት ተማሪዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ለመስጠት፣ ያልገባቸውን ሀሳብ ለመጠየቅ፣ ሌሎች በሰጡት ሀሳብ ላይ አስተያት ለመስጠት በራሳቸው ፍላጎት እጃቸውን በማውጣት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የተሻሉ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ የተሳሳተ መልስ በሚመልሱበት ጊዜም ሳይደናገጡ ድጋሚ መልስ ለመስጠት የሚያደርጉት ጥረትም ብቻቸውን የሚማሩት ከወንዶቹ ጋር ከሚማሩት የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህም በምእራፍ አንድ እንደተብራራው በነጠላ ጾታ ትምህርት ቤት የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ወቅት አድማጭነታቸውን በማቆም የክፍል ተሳትፎው መሪ ተዋናይ ይሆናሉ ብለው Andrew Mullins (2005) Mayra and David Sadker(2000)ን በመጥቀስ ከለጹት ሀሳብ ጋር የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ሠንጠረዥ- 12 መምህራን በክፍል ውስጥ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ ውጤት**

| ተ.ቁ | የታዩ ዝርዝር ነጥቦች | ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩ | | ከወንድ ተማሪዎች ጋር ሲማሩ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | አይደለም | አዎ | አይደለም |
| 5 | ሴት ተማሪዎች በፍላጎታቸው መልስ ለመመለስ እጃቸውን ሲያወጡ መምህሩ ያለማዳላት እድል ይሰጣሉ? | 4 | 2 | 4 | 2 |
| 6 | መምህሩ እጃቸውን ላለወጡ ሴት ተማሪዎች መልስ እንዲመልሱ እድል ይሰጣሉ? | 2 | 4 | 0 | 6 |
| 7 | ሴት ተማሪዎች ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እጃቸውን በማያወጡበት ጊዜ መምህሩ ያለማዳላት እድል ይሰጣሉ? | 4 | 2 | - | - |
| 8 | መምህሩ ትክክለኛ መልስ ለሚሰጡ ሴት ተማሪዎች ማበረታቻ ይሰጣሉ | 6 | 0 | 2 | 4 |
| 9 | ሴት ተማሪዎች በሚናገሩበት በሚሳተፉበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ያቋርጣሉ? | 4 | 3 | 0 | 6 |

በሠንጠረዥ- 12 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው ሴት ተማሪዎች በፍላጎታቸው መልስ ለመስጠት እጃቸውን ሲያወጡ መምህሩ ያለማዳላት እድል ይሰጣሉ? ለሚለው ጥያቄ ሴቶች

ብቻ የሚያስተምሩት መምህር በአራቱ ክፍለ ጊዜ እድል የሰጡ ሲሆን በቀሪዎቹ ሁለት ክፍለ ጊዜያት እድል ሲሰጡ አልታዩም፡፡ ከወንዶች ጋር አብረው የሚማሩትን የሚያስተምሩት መምህርም በተመሳሳይ በአራቱ ክፍለ ጊዜያት እድል የሰጡ ሲሆን በቀሪዎቹ ሁለት ክፍለ ጊዜያት እድል አለመስጠታቸው ተስተውሏል፡፡ ባጠቃላይ መረጃው እንደሚያሳየው ብቻቸውን የሚማሩትም ሆኑ ከወንዶች ጋር የሚማሩት ሴት ተማሪዎች መምህሮቻቸው ከወንዶች ጋር አብረው ሲማሩ ያለማዳላት እንደሚያሳትፏቸው ነው፡፡

የመምህሩ እጃቸውን ላላወጡ ሴት ተማሪዎች መልስ እንዲመልሱ እድል መስጠት ሁኔታቸውን ለማየት በቀረበው ጥያቄ መሰረት ሴት ተማሪዎችን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር በሁለቱ ክፍለ ጊዜያት መልስ እንዲመልሱ እጃቸውን ላላወጡ ሴት ተማሪዎች እንዲመልሱ ሲያደርጉ በአራቱ ክፍለ ጊዜያት ግን እጃቸውን ላላወጡት ተማሪዎች እድል ሲሰጡ አልታዩም፡፡ ወንዶችና ሴቶችን የሚያስተምሩት መምህር ምልከታ በተደረገባቸው ክፍለ ጊዜያት ውስጥ አንድም ጊዜ እጃቸውን ላላወጡ ሴት ተማሪዎች እድል አልሰጡም፡፡

ሴት ተማሪዎችን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር ተማሪዎቹ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እጃቸውን በሚያወጡበት ጊዜ በአራቱ ክፍለ ጊዜ እድል የሰጡ ሲሆን በሁለቱ ክፍለ ጊዜ ግን እድል አልሰጡም፡፡ ወንድና ሴቶችን የሚያስተምሩት መምህር ግን ምልከታ በተደረገባቸው ከስድስቱ ክፍለ ጊዜያት በአንዱም ጥያቄ ለመጠየቅ እጃቸውን ያወጡ ሴት ተማሪዎች ባለመኖራቸው በምልከታው ወቅት ይህን ለማየት አልተቻለም፡፡

ትክክለኛ መልስ ለሚሰጡ ተማሪዎች ማበረታቻ ይሰጣሉ? ለሚለው ሀሳብ ምልከታ በተደረገባቸው በስድስቱም ክፍለ ጊዜ ሴቶችን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር ማበረታቻ የሰጡ ሲሆን፣ ሴቶችና ወንዶቹን የሚያስተምሩት መምህርም በሁለቱ ክፍለ ጊዜ ማበረታቻ ሲሰጡ በአራቱ ክፍለ ጊዜ ግን ማበረታቻው አልሰጡም፡፡ ከምስል ቀረጻው መረዳት እንደተቻለውም ሴቶቹን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር ተማሪዎቻቸው ትክክለኛ መልስ በመለሱ ቁጥር ጥሩ፣ በጣም ጥሩ፣ የመሳሰሉ ቃላትን በመጠቀም ማበረታቻ ሰጥተዋል፡፡ከወንዶች ጋር ያሉትን የሚያስተምሩት መምህር ምልከታ በተደረገባቸው በሁለቱ ክፍለ ጊዜያት ብቻ ማበረታቻ ሰጥተው በቀሪዎቹ አራት ክፍለ ጊዜያት ግን

ለተማሪዎቹ ማበረታቻ አለመስጠታቸውን መረዳት ተችሏል፤ ከምስል ቀረጻው የተገኘው መረጃም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡

ሴቶችን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር ተማሪዎቻቸው ሲሳተፉ በአራቱ ክፍለ ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ እየገቡ ያቋረጡ ሲሆን በሁለቱ ክፍለ ጊዜ ግን ይህን ሲተገብሩ አልታዩም፡፡ ሴቶችና ወንዶችን የሚያስተምሩት መምህር ግን በአንዱም ክፍለ ጊዜ ሴቶች በሚናገሩበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ ሲገቡና ንግግራቸው እንዲቋርጥ ሲያደርጉ አልታዩም፡፡ ሴቶቹን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር ይህን ያደረጉት ተማሪዎቹ ሀሳብ በመደገፍ አይነት ሁኔታ ቢሆንም ተማሪዎቹ ንግግራቸውን ከዛ በኋላ ከመቀጠል ይልቅ በአጭር እደሚጨርሱት ከምስል ቀረጻው ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ ሴቶችና ወንዶችን የሚያስተምሩት ግን እስከ ንግግራቸው መጨረሻ ከጠበቁ በኋላ ማብራሪያ ለሚያስፈልገው ሀሳብ ጥያቄ ሲጠይቁ ይታያሉ እንጂ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ንግግራቸውን እንደማያቋርጧቸው ከምስል ቀረጻው ተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡

ባጠቃላይ በምእራፍ ሁለት እንደተብራራው በክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎችን ማሳተፍ በራሳቸው እንዲተማመኑና ከሚነሳው ሀሳብ የተለያየ እውቀት እንዲጨብጡ ስለሚያደርጋቸው እንዲሳተፉና ወደ ተራክቦ እንዲገቡ ጥያቄ መጠየቅ፣ መልስ ለሚመልሱበት ሰፋ ያለ ጊዜ መስጠትና ማበረታታት እንደሚያስፈልግ (Ashcroft and Foreman-peck1994) አመልክተዋል፡፡ በዚህ ጥናትም ከመልከታውና ከምስል ቀረጻው ከተገኘው መረጃ ለመገንዘብ እንደተቻለውም ሁለቱም መምህራን ተማሪዎቻቸው መልስ ለመስጠት እጃቸውን በሚያወጡበት ጊዜ ያለማዳለት እድል እንደሚሰጡ፣ መልስ እንዲመልሱ እጃቸውን ላላወጡ ተማሪዎች እድል የመሰጠት ሁኔታቸው የሁለቱም ዝቅተኛ ቢሆንም ሴቶችን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር በመጡኑ እድል እንደሚሰጡ፣ ትክክለኛ መልስ ለሚሰጡ ተማሪዎች ማበረታቻ በመስጠት ረገድም ሰቶችን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር የተሻሉ መሆናቸውን ማወቅ ተችሏል፡፡ ሴቶችና ወንዶችን የሚያስተምሩት መምህር ደግሞ ሴት ተማሪዎች በሚናገሩበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ተማሪዎቹ ንግግራቸው እንዲቋረጥ ስለማያደርጉ ሴቶቹን ብቻ ከሚያስተምሩት መምህር በዚህ ረገድ የተሻሉ መሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ሰንጠረዥ- 13 መምህሩ ለተማሪዎቻቸቸው የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት

| ተ.ቁ | በመጠይቁ ላይ የቀረቡ ጥያቄዎችና አማራጮች | ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩ | | ከወንድ ተማሪዎች ጋር ሲማሩ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 7 | የአማርኛ መምህራችሁ የሴት ተማሪዎች ስም በተደጋጋሚ በመጥራት እንድትሳተፉ ያደርጋሉ? | | | | |
| | ሀ. ያደርጋሉ | 7 | 15.9% | 3 | 15% |
| | ለ. አያደርጉም | 14 | 31.8% | 12 | 60% |
| | ሐ. አልፎ አልፎ | 23 | 52.3% | 5 | 25% |
| 8 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ሴት ተማሪዎች በሚሳተፉበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ተሳትፎው እንዲቀንስ ያደርጋሉ? | | | | |
| | ሀ. ያደርጋሉ | 19 | 43.2% | 0 | 0% |
| | ለ. አያደርጉም | 10 | 22.7% | 17 | 85% |
| | ሐ. አልፎ አልፎ | 15 | 34.1% | 3 | 15% |
| 9 | የአማርኛ መምህራችሁ ሴት ተማሪዎች የተሳሳተ ምልሻ በሚሰጡበት ጊዜ ምን አይነት ምላሽ ይሰጡሻል? | | | | |
| | ሀ. በድጋሚ እንድትሞክሪ ማበረታታት | 30 | 68.2% | 17 | 85% |
| | ለ. ድጋሚ እንድትሞክሪ እድል አለመስጠት | 14 | 31.8% | 3 | 15% |

የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የሴት ተማሪዎችን ስም በተደጋጋሚ በመጥራት እንድትሳተፉ ያደርጋሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች 15.9% ያህሉ ያደርጋሉ፣ 31.8% አያደርጉም፣ 52.3% ያህሉ አልፎ አልፎ ያደርጋሉ ሲሉ ከወንዶችው ጋር አብረው የሚማሩት ሴት ተማሪዎች ደግሞ 15% ያህሉ ያደርጋሉ፣ 60% ያህሉ አያደርጉም፣ 25% አልፎ አልፎ ያደርጋሉ፣ ብለው መልሰዋል። ባጠቃላይ ሴቶቹን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር የሁሉንም ስም በመጥራት አልፎ አልፎ እንዲሳተፉ ያደርጋሉ፤ ወንዶቹንና ሴቶቹን የሚያስተምሩት መምህር ግን ለሁሉም ተማሪዎች ያለማዳላት እድል የመስጠት ሁኔታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ከተገኘው መረጃ ማወቅ ተችሏል።

የአማርኛ መምህራችሁ በንግግራችሁ መሀል ጣልቃ በመግባት ንግግራችሁ እንዲቋረጥ ያደርጋሉ? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች 43.2% ያህሉ ያደርጋሉ፣ 22.7% ያህሉ አያደርጉም፣34.1% ያህሉ አልፎ አልፎ ያደርጋሉ፣ ብለው ሲመልሱ ከወንድ ተማሪዎች ጋር አብረው የሚማሩት ደግሞ 85% አያደርጉም፣ 15% ያህሉ አልፎ አልፎ ያደርጋሉ ብለው መልሰዋል። ከዚህ መረጃ መገንዘብ እንደሚቻው ከወንዶች ጋር የሚማሩትን የሚያስተምሩት መምህር ሴት ተማሪዎች ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ ጣልቃ በመግባት ንግግራቸው ወይም ተሳትፏቸው እንዲቋርጥ እንደማያደርጉ ነው። ይህ ደግሞ ከምልከታ ከተገኘው መረጃ ጋር ይዛመዳል።

የአማርኛ መምህራችሁ የተሳሳተ መልስ በምትሰጡበት ጊዜ ምን አይነት ምላሽ ይሰጣሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች 68.2% ያህሉ ድጋሚ እንድንሞክር እድል ይሰጡናል ሲሉ 31.8% ያህሉ ድጋሚ እንዲሞክሩ እድል እንደማይሰጧቸው ጠቁመዋል፤ ከወንድ ተማሪዎች ጋር የሚማሩት ሴት ተማሪዎች ደግሞ 85% ያህሉ ድጋሚ እንድንሞክር እድል ይሰጡናል፣ 15% ያህሉ ደግሞ እድል አይሰጡንም ብለው አመልክተዋል። የተገኘው መረጃ ወንዶችና ሴቶችን የሚያስተምሩት መምህር ሴት ተማሪዎችን ብቻ ከሚያስተምሩት መምህር የተሳሳተ ምላሽ ለሚሰጡ ተማሪዎች ድጋሚ እንዲሞክሩ ለማድረግ የተሻለ እድል እንደሚሰጡ ያስረዳል።

ባጠቃላይ ከመጠይቁ ከተገኙት መረጃዎች ማወቅ እንደሚቻለው ሁለቱም መምህራን በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ያለማዳላት ስማቸውን በመጥራት እንዲሳተፉ በማድረግ

በኩል ድክመት አለባቸው፡፡ ሴት ተማሪዎችን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር ግን ለሁሉም እድል ለመስጠት አልፎ አልፎ እንደሚሞክሩ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ተሳትፎው እንዲቀንስ የማያደርጉት መምህር ሴቶቹንና ወንዶችን የሚያስተምሩት መምህር ሲሆኑ ሴቶቹን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር ግን በንግግር መሀል ጣልቃ በመግባት ተሳትፎ እንዲቀንስ ያደርጋሉ፡፡ የተሳሳተ ምላሽ ለሚሰጡ ሴት ተማሪዎች ድጋሚ እድል በመስጠቱ ረገድ ሁለቱም መምህራን የተሻለ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ እነዚህን መረጃዎች በተመለከተ ከመምህራኑ ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ለመምህራኑ በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ እድል የሚሰጡት ለምን አይነት ተማሪዎች ነው? ተብሎ በቀረበው ጥያቄ መሰረት ሴቶቹን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር ለሁሉም ተማሪዎች እድል ለመስጠት እንደሚሞክሩና እጃቸውን ላወጡት ግን ቅድሚያ እንደሚሰጡ ገልጸዋል፡፡ ወንድና ሴት ተማሪዎችን የሚያስተምሩት መምህርም በተመሳሳይ ሁሉንም ተማሪ ለማሳተፍ ጥረት ቢያደርጉም እጃቸውን ላወጡ ተማሪዎች ቅድሚያ እንደሚሰጡ አስረድተዋል፡፡ ትክክለኛ ምላሽ ለሚሰጡ ተማሪዎች ማበረታቻ በመስጠት ረገድ ሴቶችን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር የተለያዩ ቃላትን በመጠቀም እንደሚያበረታቱ የገለጹ ሲሆን ከወንዶች ጋር ያሉትን የሚያስተምሩት መምህር ግን ከበድ ያለ ጥያቄ በሚያቀረቡበት ጊዜ እና ትክክል በሚሆኑበት ጊዜ ብቻ ተማሪዎቹን በማስጨብጨብ እንደሚያበረታቱ ገልጸዋል፡፡ ተማሪዎቹ የተሳሳተ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ሁለቱም መምህራን ተማሪዎቻቸው ከስህተታቸው እንዲማሩ ለማድረግ እንደሚጥሩና ስህተታቸውን ለማስተካከል እንዲችሉ እድል እንደሚሰጧቸው አስረድተዋል፡፡ በንግግር መሀል ጣልቃ በመግባት ተሳትፎው እንዲቀንስ ያደርጋሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄም ሴቶቹን ብቻ የሚያስተምሩት ስህተት ሲናገሩ ለማስተካከል አንዳንዴ ጣልቃ እንደሚገቡ ሲያመለክቱ የሴትና ወንዶች የሚያስተምሩት መምህር ግን ተማሪዎቹ ተናግረው እስከሚጨርሱ እንደሚጠብቁ ገልጸዋል፡፡ ባጠቃላይ በቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ሁለቱም መምህራን እጃቸውን ላወጡ ተማሪዎች እንዲመልሱ እድል ይሰጣሉ፡፡ ትክክለኛ ምላሽ ለሰጡ ተማሪዎች ማበረታቻ በመስጠቱ ረገድ የሴቶቹን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በንግግር መሀል ጣልቃ በመግባት ተሳትፎው

እንዲቀንስ ባለማድረጉ ረገድ ሴትና ወንዶችን የሚያስተምሩት መምህር የተሻሉ እንደሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡

ባጠቃላይ ከጽሁፍ መጠይቁና ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ሁለቱም መምህራን ተማሪዎቻቸው መልስ ለመሰጠት እጃቸውን በሚያወጡበት ጊዜ ያለማዳላት እድል ይሰጣሉ የሚለውን ሲያመለክት ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው ውጤት ግን መምህራኑ ተማሪዎቻቸው መልስ ለመስጠት አጃቸውን በሚያወጡበት ጊዜ ያለማዳላት ስማቸውን በመጥራት እንዲሳተፉ በማድረግ በኩል ድክመት አለባቸው የሚል ነው፡፡ በሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኘው መረጃ ትክክለኛ መልስ ለሚሰጡ ተማሪዎች ማበረታቻ በመስጠት ረገድ ሴቶችን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር የተሻሉ ሲሆኑ፣ ሴቶች ተማሪዎች በሚናገሩበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ተማሪዎቹ ንግግራቸው እንዲቋረጥ ባለማድረግ በኩል ደግሞ ከወንዶች ጋር አብረው የሚማሩትን የሚያስተምሩት መምህር የተሻሉ ሆነው እንደተገኙ ያስገነዝባል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሴቶች ብቻቸውን እና ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ በሚማሩባቸው የግል ትምህርት ቤቶች የሴት ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በማነጻጸር መመርመር ሲሆን በተጨማሪም በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው ምን ይመስላል?፣ ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው ምን ይመስላል?፣ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መካከል የተሳትፎ ልዩነት አለ? ካለ የልዩነቱ ምክንያት ምንድን ነው? የሚሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስም ምልከታ፣ የምስል ቀረጻ ፣ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ መረጃውን ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በተገለጹት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው የሚከተሉት ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡

### 5.1 ማጠቃለያ

- ለጥናቱ በተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኙት መረጃዎች ብቻቸውን በሚማሩ ሴት ተማሪዎችና ከወንዶች ጋር በሚማሩ ሴት ተማሪዎች መካከል በክፍል ውስጥ በሚደረገው የተሳትፎ እንቅስቃሴ መካከል ልዩነት መኖሩን አስገንዝበዋል፡፡ ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ከሚማሩት ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በፍላጎታቸው መልስ በመመለስ፣ጥያቄ በመጠየቅና ሌሎች በሰጡት መልስ ወይም ሀሳብ ላይ አስተያየት በመስጠት ከወንዶች ጋር ከሚማሩት ሴት ተማሪዎች የተሻለ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የልዩነቱ ምክንያትም ከወንዶች ጋር የሚማሩት ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚሳተፉበት ጊዜ ብንሳሳት ወንድ ተማሪዎች ሊስቁብን ይችላሉ? በሚልና መምህሩ እድል የሚሰጧቸው እጃቸውን በሚያወጡበት ጊዜ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡
- በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ያሉ ሴት ተማሪዎች የተሳሳተ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ድጋሚ ለመሳተፍ የሚሞክሩ ቢሆንም በመካከላቸው ልዩነት መኖሩ ታይቷል፡፡

ይህም ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር አብረው ከሚማሩ ሴት ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸሩ የተሳሳተ መልስ በሚመልሱበት ጊዜ እንደማይፈሩና ድጋሚ እንደሚሳተፉ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ብቻቸውን የሚማሩት ተማሪዎች ድጋሚ ለመሳተፍ የማይፈሩት ሁሉም ሴቶች በመሆናቸውና እንደጓደኛ ስለሚተያዩ ሲሆን ከወንዶች ጋር የሚማሩት ተማሪዎች ሲሳሳቱ ወንድ ተማሪዎች ይስቁብናል ብለው ስለሚሰጉ ቀድሞውንም የመልሱን ትክክለኛነት እርገጠኛ ካልሆኑ በስተቀር ለመሳተፍ እጃቸውን የማያወጡ መሆኑን ማወቅ ተችሏል፡፡

- በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙት መምህራን ሴት ተማሪዎችን እንዲሳተፉ ለማድረግ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በዚህም መሰረት የሁለቱም ትምህርት ቤት መምህራን በፍላጎታቸው እጃቸውን የሚያወጡትን ተማሪዎች እንዲሳተፉ ለማድረግ እድል እንደሚሰጡ መገንዘብ ተችሏል፡፡
- መምህራኑ እጃቸውን ላወጡ ተማሪዎች ምላሽ እንዲሰጡ ቢያደርጉም፣ አብዛኛውን ጊዜ እድል የሚሰጡት ግን በክፍል ውስጥ በተሳትፏቸው ጎልተው ለሚታዩ ማለትም ብዙ ጊዜ ለመሳተፍ እጃቸውን ለሚያወጡ የተወሰኑ ተማሪዎች እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡
- ሁለቱም መምህራን መልስ እንዲመልሱ እጃቸውን ላላወጡ ተማሪዎች እድል የመስጠት ሁኔታቸው ዝቅተኛ ቢሆንም ሴቶችን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር በመጠኑ እድል እንደሚሰጡ ተረጋግጧል፡፡
- ትክክለኛ መልስ ለሚሰጡ ተማሪዎች ማበረታቻ በመስጠት ረገድ ሴቶችን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር የተሻሉ መሆናቸውን ማወቅ ተችሏል፡፡
- መምህራኑ ሴት ተማሪዎች በሚሳተፉበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ተሳትፏቸው እንዲቋረጥ የማድረግ ሁኔታቸውን በተመለከተ ሴቶቹን ብቻ የሚያስተምሩት መምህር በንግግራቸው መሃል ጣልቃ በመግባት ተሳትፎው እንዲቀንስ የሚያደርጉ ሲሆን ከወንዶቹ ጋር ያሉትን የሚያስተማሩት መምህር ግን በንግግር መሀል ጣልቃ በመግባት ተሳትፎው እንዲቀንስ እንደማያደርጉ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

## 5.2 አስተያየት

በዚህ ጥናት የተገኙትን ውጤቶች መሰረት በማድረግ ማጠቃለያ ተሰጥቷል፡፡ ከማጠቃለያው ሀሳብ በመነሳት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡

- ሴት ተማሪዎች ብቻቸውንም ሆነ ከወንድ ተማሪዎች ጋር ሆነው በሚማሩበት ጊዜ እጃቸውን በማውጣት እንዲሳተፉ ለማድረግ መምህራኑ ቢያበረታቷቸው፣
- መምህራኑ አብዛኛውን ጊዜ እንዲሳተፉ እድሉ የሚሰጡት ለተወሰኑ ተማሪዎች በመሆኑ ይህን ሁኔታ ለመቀየር ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ቢያነሳሱና ለሁሉም እድል በመስጠት እንዲሳተፉ ቢያደርጉ፣
- ሴት ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ ተማሪዎቹ እንዳይደናገጡ በማድረግ ድጋሚ እንዲሞክሩት ወይም የተሳሳቱትን ጥያቄ እንዲያስተካከሉት እድል ቢሰጣቸው፤
- ከወንድ ተማሪዎች ጋር የሚማሩ ሴት ተማሪዎች እጃቸውን እንዲያወጡና ወደ ተሳትፎው እንዲገቡ ለማድረግ መምህሩ ማበረታቻ ቢያደርጉላቸው፣
- ለቀላልም ሆነ ከባድ ጥያቄ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ተማሪዎቹን ጥሩ፣ በጣም ጥሩ፣ እጅግ በጣም ጥሩ የመሳሰሉትን ቃላትን በመጠቀም መምህራን ቢያበረታቷቸው፣
- ተማሪዎቹ መልስ በሚሰጡበት ወይም በሚናገሩበት ጊዜ መምህራን አስተያየት እንኳን ቢኖራቸው በንግግራቸው መሀል ጣልቃ ከመግባት ይልቅ ንግግራቸውን አስኪጨርሱ ድረስ ቢጠብቋቸው፣
- በቋንቋ መማሪያ መጻሀፍት ላይ ሴት ተማሪዎች መልስ በሚመልሱበት ጊዜም ሆነ በሚሳተፉበት ጊዜ ወንድ ተማሪዎች እንዳይስቁባቸው የሚያደርጉ ምክር አዘል የሆኑ ምንባቦች እንዲካተቱ ቢደረግ፣
- በሌሎች የክፍል ደረጃዎች ተመሳሳይ ጥናት ቢደረግ የሴት ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የተራክቦ ክሂላቸውን እንዲጨምር የሚያደርጉ መፍትሄዎችን ለማግኘት ያስችላል፣

# ዋቢ ጽሁፎች


ማስተዋል ወርቁ፡፡ (1999)፡፡‹‹በባህርዳር ከተማ በሚገኙ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የስርአተ ጾታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ (ያልታተመ)

በላይ ሰይድ፡፡ (1992)፡፡‹‹የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት፡፡›› በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ጥናት፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ (ያልታተመ)

ፋንቱ ደምሴ፡፡ (1989) ‹‹የጾታ ልዩነት የአማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና፣ በእንጦጦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች አጠቃላይ የቋንቋ ብቃት ላይ የተካሄደ ጥናት፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ (ያልታተመ)

Almaz Eshete. (1991).“Perspectives on Gender and Development.” In *Gender Issues in Ethiopa.*” Tsehay Berhane Selassie(Ed.) Addis Ababa.

Amanuel Gebru. (1996). Gender Differences in Participations in Group Discussion in Freshman English Classes at AAU.” (Unpublished M.A. Thesis) Submitted to ILS, Addis Ababa University.

Andrew Mullins (2005). Single-sex Scools. Finch publishing፡ USA.

Ashcroft, k and Foremanpeck, I (1994). *Managing Teaching and Learning in Further and Higher Education.* London:

Bailey, K.D. (1994) *Methods of Social Research.* Singapor: The Free Press.

Bank,B.J. and Hall, P.m 1997. *Gender Equality and Schooling: Policy and Practice.* New York: Grand PubliShing, Inc

Bendera, S. and Mboya, M. (1996). *Gender and Education in Tanzanian Schools.* Dares Salaam: DUP

Betz., N. and L. Fitzgerald. (1987). *The Career Psychology of Women.* London: Academic Press, Inc.

Genet Zewdie. (1991). "*Women in Education: A Study of Academic Performance and Participations of Female Students in High Schools* in Addis Ababa." Tsehay Berhane Selassie(Ed.) Addis Ababa.

Jimenez, E. and Lockheed, M.E.(1989). "Enhancing Girls' Learning Through Single Conunderum," *Educational Evaluation and Policy Analysis*, Vol. 11, No. 2, pp. 117- 142.

Kidane degefaw.(2006). "A Communicative study of Male-Female Students' EFL Classroom Participation: with special Reference to Four non Gevernment Secondary Schools in Addis Ababa." (Unpublished M.A. Thesis) Submitted to ILS, Addis Ababa University.

Levinson,S.C (1983). *Pragmatics.* Cambridge: Cambridge University Press.

Little, W.(1984). *Foreign and Second Language Learning.* Cambridge: Cambridge University press.

Maccoby,E.(1990). "*Gender and Relation Ships:* A Development Account."

Nunan, D (1993) *Introducing discourse analysis.* London: Penguin English.

Nunan, D. and Lamb, C.(1996) *The Self-Directed Teacher Managing The Learning Process.* Cambridge: Cambridge University Prees

Odaga, A. and Heneveld, W. (1995). *Girls and Schools in Sub- Saharan Africa: From Analysis to Action.* Washington DC: World Bank

Potter, E.F. (1978). " Sex Differences in Classroom Participations." *A paper Present at the Annual Convention of the South Eastern Psychological Association.* Atlanta: Georgia, March, 15-18, 1978.

Richards, J. and Nunan (1990). *Second Language Teaching Education.* Cambridge: CUP.

Santrock, J.W. (2001). Educational Psychology. California: Mc Graw Hill Companies.

Semunesh Abebe (1997). "Female Students Level of Assertiveness and their Verbal Interaction in EFL Classrooms in High School in Addis Ababa." (Unpublished M.A. Thesis) Submitted to ILS, Addis Ababa University

Seyoum Tefera. (1991). "The Participation of Women in Higher Education in Ethiopia". Tsehay Berhane Selassie (ed.).

Spender,D. (1982). *Invisible Women*. London: The Women's Press.

Sunderland, J. (1992). "Gender in the EFL Classroom." *ELT Journal.* Vol. 46(1)81-90.

——— (1994). " Differential Treatment by Gender in the EFL Classroom: Using in participant Perspectives". In Sunderland. J. (ed.) *Exploring Gender Quesitons and Implications for English Language Education*. New York: Prentice Hall.

Taddele Adamu. (1990). " Individual Difference in Second Language Learning in formal Context." University of Reading. Unpeblished PH.D Thesis.

Webb, N. (1984). "Sex Difference in International and Achievement in Co-Operative Small Grop." *Journal of Educational psychology.* 78(1): 33-44.

# ሙዳየ ቃላት

| | |
|---|---|
| Verbal interaction | ቃላዊ ተራክቦ |
| Single sex school | ሴቶች ብቻ የሚማሩበት ትምህርት ቤት |
| Mixed sex school | ወንዶችና ሴቶች የሚማሩበት ትምህርት ቤት |
| Non-verbal | ኢ. ቃላዊ |
| Answering | መመለስ |
| Lecturing | ማስተማር |
| Questioning | መጠየቅ |
| Praising | ማሞገስ |
| Criticizing | መተቸት |
| Check list | የመከታተያ ቅጽ |
| Observation | ምልከታ |
| Self —esteem | ለስራ የሚሰጥ ግምት |
| Sex | ፆታ |
| Gender | ስርአተ ፆታ |

# አባሪዎች

አባሪ አንድ፡- የምልከታ ቅጽ

አባሪ ሁለት፡- የምስል ቀረጻ ዝርዝር ሀሳብ

አባሪ ሶስት፡- የጽሁፍ መጠይቅ

አባሪ አራት፡- ቃለ መጠይቅ

# አባሪዎች

አባሪ-አንድ

**የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅጽ** (Check List)

በዚህ የምልከታ መከታተያ ቅጽ ሴት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያላቸውን የተሳትፎ እንቅስቃሴ ለመመርመር የሚያስችሉ ጥያቄዎች ተካተዋል፡፡ በመከታተያ ቅጹ ላይ ያሉ ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ ከተተገበሩ ይህን(✓) ምልክት በማድረግ ምልከታው ተከናውኗል፡፡

**የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሁኔታ ለማነጻጸር የተዘጋጀ የመከታተያ ቅጽ**
**(Teachers observation Checklist)**

**አጠቃላይ መረጃ፡-**

የትምህርት ቤቱ ስም፡- ____________________
ምድብ፡- ----------------------
ቀን፡- -------------------------

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ድግግሞሽ | ብዛት |
|---|---|---|---|
| | | ሴቶች | |
| 1 | ለጥያቄዎች መልስ ለመመለስ በራሳቸው ፍላጎት በተደጋጋሚ እጃቸውን ያወጣሉ? | | |
| 2 | በራሳቸው ፍላጎት ጥያቄ ለመጠየቅ እጃቸውን ያወጣሉ? | | |
| 3 | በክፍል ውስጥ ሌሎች ተማሪዎች በሚመልሱት መልስ ላይ አስተያየት ይሰጣሉ? | | |
| 4 | ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ ይደናገጣሉ? | | |
| 5 | ተማሪዎቹ በፍላጎታቸው መልስ ለመመለስ እጃቸውን ሲያወጡ መምህሩ ያለማዳላት እድል ይሰጣሉ? | | |
| 6 | ተማሪዎቹ መልስ እንዲመልሱ እጃቸውን ላላወጡ ተማሪዎች መምህሩ እድል ይሰጣሉ? | | |
| 7 | ተማሪዎቹ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እጃቸውን በሚያወጡበት ጊዜ መምህሩ ያለማዳላት እድል ይሰጣሉ? | | |
| 8 | መምህሩ ትክክለኛ መልስ ለሚሰጡ ተማሪዎች ማበረታቻ ይሰጣሉ? | | |
| 9 | ተማሪዎች በሚሳተፉበት ጊዜ መምህሩ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ ይገባሉ? | | |

አባሪ- ሁለት፦- የምስል ቀረጻ ዘገባ

ቀረጻ አንድ፦- ልደታ ማርያም የልጃገረዶች ትምህርት ቤት

ምድብ 9B

ክፍለ ጊዜ- 3ኛ

ሰአት 4፡15- 5፡00

ቀን 11/07/2004 ዓ.ም

የተማሪዎች ባዛት- 57

መምህሩ ወደ ክፍል ሲገቡ ተማሪዎቹ በሙሉ ተነስተው እንደምን አረፈዱ መምህር በማለት ተቀበሏቸው፡፡ መምህሩም እንደምን አረፈዳችሁ ተማሪዎች ካሉ በኋላ ለተማሪዎቹ እንዲቀመጡ ትእዛዝ ሰጧቸው፡፡

መምህሩ ከተማሪዎቹ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጡና ተማሪዎቹም ከተቀመጡ በኋላ በሰሌዳው ላይ ቀን እና ‹‹የሀዘን በትር›› የሚል ርዕስ ጻፉ፡፡ ከዚህ በኋላ መምህሩ በሰሌዳው ላይ የጻፉትን ርዕስ ታሪክ ማንበብ ጀመሩ፡፡ ተማሪዎቹም ታሪኩን በጥሞና ከተከታተሉ በኋላ መምህሩ ስለ አጭር ልቦለድ ባህሪ ገለጻ ሰጡ፤ ከዚህ በኋላ ካነበቡት ታሪክ የወጡ ጥያቄዎችን በቃል ማጻፍ ጀመሩ፡፡ ጥቄዎቹን አጽፈው እንደጨረሱ ተማሪዎቹ መልሱን የሚሰሩበት ጊዜ ሰጥተው እየተዘዋወሩ ተማሪዎችን መቆጣጠር ጀመሩ፡፡ ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን ሰርተው መጨረሳቸውን ካረጋገጡ በኋላ መምህሩ ለተማሪዎቹ ያጻፏቸውን ጥያቄዎች በቃል እያነበቡ ተማሪዎቹ እንዲመልሱ ማድረግ ጀመሩ፡፡ የጥያቄና መልስ ሂደቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

❖ **የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቀረቡላቸው ታሪክ መሰረት መልሱ**

መም፡- በላይነህ ጉብኝቱን ሳይጨርስ በመሀከሉ አቋርጦ የወጣው ለምን ነበር?

ሴተ1፡- በመቃብሩ ያያት ልጅ ስላሳዘነችው ምን ሆና እንሆነ ለማጣራት ነበር፡፡

መም፡- በላይነህ ልጅቷን ፍለጋ ገና ከመቃብሩ እንደወጣ መልካው ላይ ያየው ነገር ምን ነበር?

ሴተ2፡- ጥቁር ነገር ወይም ባና

መም፡- ከወንዝ ወዲያ ማዶ ሆነው ሲያወሩ በነበሩ ሰዎች ላይ ለምን ነበር በላይነህ የተናደደው?

ሴተ3፡- ጥቁር ነገር ተንሳፎ እያዩ እያወሩ መስሎት፡፡

መም፡- አይደለም፤

ሴተ4፡- የሞተ ሰው ወድቆ እያዩ እነሱ ዝም ብለው እያወሩ መስሎት፡፡

መም. በመጨረሻ ልጅቷን ሲያገኛት የቻለው እንዴት ነበር?

ሴተ4፡- ፊት ለፊቱ ካለው ዛፍ ላይ ተቀምጣ፡፡

መም. በዛፉ ላይ ተንጠልጥሎ የነበረው ገመድ በመቃብሩ ስፍራ ላይ ከታየው ያንገት ልብስ ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

ሴተ5፡- ሁለቱም ጥቁር መሆናቸው፡፡

መም. በላይነህ በሀሳቡ ሲያወጣ ሲያወርድ የነበረውና ለሰው ግን ተናግሮት የማያውቀው ነገር ምንድን ነው?

ሰተ2፡- ሰው ሲሞት ለምን እናዝናለን፡፡

❖ **ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ**

መም፡- የአጭር ልቦለዱ ርዕስ ለጭብጡ ምን ሚና አለው?

ሀ. ያጎላዋል ለ. ይደብቃል መ. ያብራራዋል

ሴተ6፡- ያጎላዋል

መም፡- የጽሁፉ ድባብ ምን ይመስላል?

ሀ. የሀዘን ለ. የደስታ

ሴተ7፡- የሀዘን

መም፡- ሀመልማል የገባችበት የግጭት አይነት የትኛው ነው?

ሀ. አካላዊ ለ. ሀሊናዊ

ሴተ9፡- ሀሊናዊ ግጭት

መም፡- የጽሁፍ ማዕከላዊ ሀሳብ (ጭብጥ) ምንድን ነው?

ሀ. ከመጠን ያለፈ ደስታ ሐ. ዘመድን በህይወት እያለ መርዳት

ለ. ሀዘንን በልክ ማድረግ መ. ለእና ሐ መልስ ናቸው

ሴተ10፡- ሀዘንን በልክ ማድረግ እንደሚገባ

መም፡- በዚህ ልቦለድ ውስጥ በዋና ገጸ ባህሪነት የምናገኛቸው ስንት ሰዎች ናቸው?

ሀ. አምስት ሐ. ሶስት

ለ. ሁለት መ. አራት

ሴተ11፡- ሶስት

መም፡- የልቦለዱ መቼት የት ነው?

ሀ. በቤተልሄም ሐ. በመካነ መቃብር

ለ. በቤተመንግስት መ. በቤተ መቃብር

ሴተ6፡- በመካነ መቃብር ስፍራ

መም፡- ልቦለዱ የተጻፈው በስንተኛ መደብ አንጻር ነው?

ሀ. 1ኛ መደብ ሐ. 3ኛ መደብ

ለ. 2ኛ መደብ

ሴተ12፡- በአንደኛ መደብ

መም፡- ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የልቦለድ አላባ አይደለም፡፡

ሀ. ግጭት ሐ. መቼት

ለ. ጭብጥ መ. ምናብ

ሴተ13፡- ምናብ

መም፡- የአጭር ልቦለድ ባህሪ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ጥቂት ገፀ ባህሪያት ሐ. ነጠላ ውጤት

ለ. ከልደት እስከ ሞት መተረክ መ/ ወሰን መቼት

ሴተ14፡- ከልደት እስከ ሞት መተረክ

መም፡- የአጭር ልቦለድ አጻጻፍ ስልት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ድንገታዊ አጨራረስ ሐ. ትረካዊ አጻጻፍ

ለ. ደብዳቤያዊ አጻጻፍ መ. ዘገባዊ አጻጻፍ

ሴተ15፡- ዘገባዊ አጻጻፍ

በመጨረሻም አንዲት ተማሪ ጥያቄ ለመጠየቅ እጇን ብታወጣም መምህሩ እድል አልሰጧትም፤ መምህሩ እድል ያልሰጧት ክፍለ ጊዜው በማለቁ ምክንያት በመሆኑ ጥያቄውን በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ እንድታቀርብ ለተማሪዋ ተናግረው ክፍለ ጊዜው አልቋል፡፡

**ቀረጻ ሁለት ፡- ልደታ ማርያም ልጃገረዶች ትምህርት ቤት**

**ምድብ 9C**

**ክፍለ ጊዜ- 4ኛ**

**ሰአት 5:30- 6:15**

**ቀን 11/07/2004 ዓ.ም**

**የተማሪዎች ባዛት- 56**

መምህሩ ወደ ክፍል ሲገቡ ተማሪዎቹ በሙሉ ተነስተው እንደምን አረፈዱ? መምህር በማለት ተቀበሏቸው፤ መምህሩም እንደምን አረፈዳችሁ ተማሪዎች? ካሉ በኋላ ለተማሪዎቹ እንዲቀመጡ ነገራቸው፤ ተማሪዎቹም ተቀመጡ፡፡

መምህሩ ከተማሪዎቹ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጡና ተማሪዎቹም ከተቀመጡ በኋላ መምህሩ በሰሌዳው ላይ ቀን እና ‹‹የሀዘን በትር›› የሚል ርዕስ ጻፉ፡፡ ከዚህ በኋላ መምህሩ ለተማሪዎቹ ደብተራቸውን እንዲያወጡ ካዘዙ በኋላ ከዚህ ክፍለ ጊዜ በፊት የተነበበላቸውን የሀዘን በትር በሚል ርእስ ታሪክ እንደሚያስታውሱ ከጠየቋቸው በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማጻፍ ቀጠሉ፡፡ ተማሪዎቹም ታሪኩን እንደሚያስታውሱት ለመምህራቸው ከነገሩ በኋላ ደብተራቸውን አውጥተው ጥያቄዎቹን መምህሩ በቃል እያነበቡላቸው መጻፍ ጀመሩ፡፡ ጥያቄዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- **ለሚከተሉት ጥያቄዎች ታሪኩን መሰረት በማድረግ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን ምረጡ**

1. የአጭር ልቦለዱ ርዕስ ለጭብጡ ምን ሚና አለው?

   ሀ. ያጎላዋል     ለ. ይደብቃል     መ. ያብራራዋል

2. የጽሁፍ ድባብ ምን ይመስላል?

ሀ. የሀዘን ለ. የደስታ

3. ሀመልማል የገባችበት የግጭት አይነት የትኛው ነው?

ሀ. አካላዊ ግጭት ለ. ህሊናዊ ግጭት

4. የጽሁፉ ማዕከላዊ ሀሳብ (ጭብጥ) ምንድን ነው?

ሀ. ከመጠን ያለፈ ደስታ ሐ. ዘመድን በህይወት

ለ. ሀዘንን በልክ ማድረግ መ. ለእና ሐ መልስ ናቸው

5. በዚህ ልቦለድ ውስጥ በዋና በገጸ ባህሪነት የምናገኛቸው ስንት ሰዎች ናቸው?

ሀ. አምስት ሐ. ሶስት

ለ. ሁለት መ. አራት

6. የልቦለዱ መቼት የት ነው?

ሀ. በቤተልሄም ሐ. በመካነ መቃብር

ለ. በቤተመንግስት መ. በቤተ መቃብር

7. ልቦለዱ የተጻፈው በስንተኛ መደብ አንጻር ነው?

ሀ. 1ኛ መደብ ሐ. 3ኛ መደብ

ለ. ውስን ሁሉን አወቅ መ. ሁሉን አወቅ

8. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የልቦለድ አላባ አይደለም።

ሀ. ግጭት ሐ. መቼት

ለ. ጭብጥ መ. ምናብ

9. የአጭር ልቦለድ በህሪ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ጥቂት ገፀ ባህሪያት ሐ. ነጠላ ውጤት

ለ. ከልደት እስከ ሞት መተረክ መ/ ወሰን መቼት

10. የአጭር ልቦለድ አጻጻፍ ስልት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ድንገታዊ አጨራረስ ሐ. ትረካዊ አጻጻፍ

ለ. ደብዳቤያዊ አጻጻፍ መ. ዘገባዊ አጻጻፍ

መምህሩ ጥያቄዎቹን ካጻፉ በኋላ ለተማሪዎቹ የመስሪያ ጊዜ ሰጧቸው (ሰአት ግን አልወሰኑም ነበር) ከትንሽ የቆይታ ጊዜ በኋላ መምህሩ ጥያቄዎቹን አብረው እንዲሰሩ አዘዙ። በዚህ ጊዜ ተማሪዎቹ ታሪኩን በትክክል ማስታወስና ጥያቄዎቹን መስራት አልቻልንም በማለት በድጋሚ ታሪኩ እንዲነበብላቸቸው በጅምላ መምህራቸወን ጠየቁ። መምህሩም ተስማምተው የሀዘን በትር የሚለውን ታሪክ ለተማሪዎቹ አነበቡ። መምህሩ ታሪኩን እንደጨረሱ ከተማሪዎቹ ጋር መልሶቹን ለመስራት ተስማምተው ወደ ጥያቄና መልሱ ገቡ።

መም፡- የአጭር ልቦለዱ ርዕስ ለጭብጡ ምን ሚና አለው?

ሀ. ያጎላዋል ለ. ይደብቃል ሐ. ያብራራዋል

ሴተ1፡- ጭብጡን ያጎላዋል።

መም፡- የጽሁፉ ድባብ ምን ይመስላል?

ሀ. የሀዘን ለ. የደስታ

ሴተ2፡- የሀዘን

መም፡- ሀመልማል የገባችበት የግጭት አይነት የትኛው ነው?

ሀ. አካላዊ ግጭት ለ. ህሊናዊ ግጭት

ሴተ3፡- ህሊናዊ ግጭት

መም፡- የጽሁፉ ማዕከላዊ ሀሳብ (ጭብጥ) ምንድን ነው?

ሀ. ከመጠን ያለፈ ደስታ ሐ. ዘመድን በህይወት

ለ. ሀዘንን በልክ ማድረግ መ. ለእና ሐ መልስ ናቸው

ሴተ4፡- ሁሉም

መም፡- በዚህ ልቦለድ ውስጥ  በዋና በገጸ ባህሪነት የምናገኛቸው ስንት ሰዎች ናቸው?

ሀ. አምስት ሐ. ሶስት

ለ. ሁለት መ. አራት

ሴተ5፡- ሶስት

መም፡- የልቦለዱ መቼት የት ነው?

ሀ. በቤተልሄም ሐ. በመካነ መቃብር

ለ. በቤተመንግስት መ. በቤተ መቃብር

ሴተ6፡-በመካነ መቃብር

መም፡- ልቦለዱ የተጻፈው በስንተኛ መደብ አንጻር ነው?

ሀ. 1ኛ መደብ ሐ. 3ኛ መደብ

ለ. ውስን ሁሉን አወቅ መ. ሁሉን አወቅ

ሴተ7፡- በአንደኛ መደብ

መም፡- ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የልቦለድ አላባ አይደለም፡፡

ሀ. ግጭት ሐ. መቼት

ለ. ጭብጥ መ. ምናብ

ሴተ8፡- ምናብ

መም፡- የአጭር ልቦለድ በህሪ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ጥቂት ገፀ ባህሪያት ሐ. ነጠላ ውጤት

ለ. ከልደት እስከ ሞት መተረክ መ/ ወሰን መቼት

ሴተ9፡- ከልደት እስከሞት መተረክ

መም፡- የአጭር ልቦለድ አጻጻፍ ስልት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ድንገታዊ አጨራረስ ሐ. ትረካዊ አጻጻፍ

ለ. ደብዳቤያዊ አጻጻፍ መ. ዘገባዊ አጻጻፍ

ሴተ10፡- ዘገባዊ አጻጻፍ

ጥያቄና መልሱ ካለቀ በኋላ ተማሪዎቹ አጠቃላይ ስለተነበበላቸው ታሪክ የተረዱትን ሀሳብም ሆነ ያላቸወውን አስተያየት እንዲሰጡ በጠየቁት መሰረት ተማሪዎቹ የሚከተሉትን ሀሳቦች ሰጥተዋል።

ሴተ11፡- ‹‹ሀመልማል ባሏ ሞቶባት በሀዘን የተቆራመደች ሴት ናት። በላይነህ ደግሞ በጣም ለሰው አዛኝና ጥሩ ሰው በመሆኑ ሀመልማልን ለመርዳት የተነሳ ሰው እንደሆነ ተረድቻለሁ።››

ተማሪዋ በምትናገርበት ጊዜ መምህሩ ተማሪዋ የተናገረችውን ሀሳብ በመድገም ንግግሯን ያቋርጧት ነበር።

ሴተ12፡- ‹‹በላይነህ የሚባለው ሰውየ ለሰው የሚያዝን፣ ለሰው የሚጨነቅ ነው። **በላይነሽ** ደግሞ የእሱ ሚስት ስለሆነች ሀመልማልን ለመርዳት ከበላይነህ ጋር ተስማምታለች። ሀመልማል ደግሞ በሀዘን የተጎዳች ሴት ናት። የታሪኩ ጭብጥ በላይነህና አልማዝ ሀመልማልን ለመርዳት የሚያደርጉትን ውጣ ውረድ የሚያሳይ ነው። እኔ ከዚህ ታሪክ የተረዳሁት ሀዘንችንን፣ ጭንቀታችንንና ደስታችን በልክ ማድረግ እንዳለብን፣ ለሰው መጨነቅና ለሰው ማሰብ እንዳለብን፣ ሰው ችግር ካለበት ወደ ባሰ ችግር እንዳይገባ መንከባከብ እንዳለብን ነው።››

ተማሪዋ የበላይነህን ሚስት አልማዝ ማለት ሲኖርባት በላይነሽ ብላ በመመለሷ ተማሪዎቹ ሲስቁባት ተደናግጣ ተሳትፎውን ከማቋረጥ ይልቅ የፈገግታ ምልክት

በማሳየትና የገፀበህሪዋን ስም በማስካከል ተሳትፎዋን(በንግግሯን) ቀጥላለች፡፡ በመጨረሻም መምህሩ በጣም ጥሩ የሚል ማበረታች ሰጥተዋል፡፡

ሴተ13፡- ‹‹ ሀመልማል ባሏ የሞተባት ሴት ናት፡፡ ከዛ ... ››ብላ ንግግሯን ስትጨርስ መምህሩ ታሪኩን ራሳቸው መናገር ጀመሩ ተማሪዋ ለትንሽ ጊዜ ከቆመች በኋላ መምህሩ ራሳቸው ታሪኩን ማስፋት ስለጀመሩ ተቀመጠች፡፡ መምህሩም ሴላስ በማለት ለሌላ ተማሪ እድል ሰጡ፡፡

ሴተ14፡- ‹‹በታሪኩ ውስጥ ሶስት ገጸባህርያት አሉ፡፡ አልማዝ፣ በላይነህና ሀመልማል፡፡ ሀመልማል ገና በአፍላነት እድሜዋ ባሏ በመሞቱ የተነሳ በሀዘን የተጎዳች ሴት ናት፡፡ አልማዝ ደግሞ የበላይነህ ሚስት ናት፡፡ በላይነህ ለሰው ቀብር ሄዶ ነው ሀመልማልን ያያትና የረዳት፡፡ የሀመልማል ታሪክ በጥሩ ጎኑ አለቀ እንጂ አንዳንድ ሰዎች ሰውን ለማታለል ብለው እንደዚህ አይነት ታሪክ በውሸት የሚፈጥሩ አሉ፡፡ ሰውን ከመደርዳት በፊት ስለ ሁኔታው እውነተኛነት በመጀመሪያ ማጣራት ጥሩ ነገር ነው፡፡››

ሴተ12፡- ‹‹ወደፊት የሚመጣውን ነገር ባለማየትና ለባሏ ባላት ፍቅር በመታለል እራሷን ልትጎዳ ነበር፡፡ ነገር ግን አልማዝና በላይነህ ወደፊት አዲስና ጥሩ ነገር ሊገጥማት እንደሚችል በማስረዳት ወደ ጥሩ ነገር መልሰዋታል፡፡››

መምህሩ ጥሩ አስተያየት እንደሆነ ተናግረው ክፍለ ጊዜው አለቀ፡፡

**ቀረጻ ሶስት፡- ልደታ ማርያም ልጃገረዶች ትምህርት ቤት**

**ምድብ 9B**

**ክፍለ ጊዜ- 3ኛ**

**ሰአት 4፡15- 5፡00**

**ቀን 18/07/2004 ዓ.ም**

**የተማሪዎች ባዛት- 57**

መምህሩ ሰላምታ ሰጥተው ወደ ክፍል ከገቡ በኋላ በጥቁር ሰሌዳው በስተግራ በኩል ቀን፣ ወደ መሀል ገባ ብለው ደግሞ ዘገባ የሚል ርዕስ ጻፉ፡፡ ከዛም ስለዘገባ ምንነት ለተማሪዎቹ ገለጻ ከሰጡ በኋላ ስለዘገባ ተማሪዎቹን እያሳተፉ ማስተማር ቀጠሉ፡፡

ሴተ1፡- ያለፈው ዘገባ ስለ ህዝብ ቆጠራ ሲያወራ የአሁኑ ደግሞ ስለ ወርሀዊ ዘገባ ያወራል፡፡
መም፡- ወርሀዊ ዘገባ የአሁን የተሰራ ስራ ስለሚቀርብለት ወቅታዊ ልንለው እችላለን?
በህብረት፡- አዎ
መም፡- ጽሁፉ የተዘጋጀው በምን መነሻነት ነበር?
ሴተ3፡- የትምህርት ምርምር መመሪያ በሚል ርዕስ
መም፡- በጣም ጥሩ በጣም ጥሩ
መም፡- በጽሁፉ ውስጥ በዘገባው ላይ የተነሱ ዋና ዋና ነገሮ የትኞቹ ናቸው?
ሴተ4፡- የአማርኛ መጽሀፍ እንዲቀየር፣ አውደ ጥናት እንዲካሄዱና፣ ኮሚቴ እንዲቋቋም
የሚሉ ናቸው
መም፡- የዚህ አይነት ጽሁፍ ዋና አላማው ምንድን ነው ትላላችሁ
ሴተ5፡- ስለ ሚደረገው ነገር ወይም ስለትምህርቱ አጠቃላ እንቅስቃሴ ያሳያል፡፡
መም፡-በዚህ አመት ትምህርታችሁ ያያችሁት ወይም የታዘባችሁትን ነገር በዘገባ መልክ አቅርቡ፡፡ ብለው አዘዙ ተማሪዎቹም በደብተራቸው ላይ የጻፉትን ዘገባ በየተራ እጃቸውን እያወጡ ማቅረብ ጀመሩ፡፡

የቀረቡት ዘገባዎች ሰባት ናቸው፡፡ በዚህ ጊዜ መምህሩ በየመሀሉ ማብራሪያ እየሰጡና ተማሪዎቹን እያበረታቱ ዘገባውን የማቅረብ ሂደቱ ተጠናቋል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች እጃቸውን እያወጡ ያዘጋጁትን ዘገባ ለማቅረብ ቢፈልጉም ክፍለ ጊዜው በመጠናቀቁ የተነሳ ሁሉንም እንዲያቀርቡ ማድረግ አልተቻለም፡፡

**ቀረጻ አራት፡- ልደታ ማርያም ልጃገረዶች ትምህርት ቤት**

**ምድብ፡-** 9C

**ክፍለ ጊዜ፡-** 4ኛ

**ሰአት** 5፡30፡- 6፡15

**ቀን፡-** 18/07/2004 **ዓ.ም**

**የተማሪዎች ባዛት፡-** 56

መምህሩ ለተማሪዎቹ ሰላምታ ሰጥተው ወደ ክፍል ከገቡ በኋላ በጥቁር ሰሌዳው በስተግራ በኩል አስምረው ቀን እና ዘገባ የሚል ርእስ ጻፉ፡፡ መምህሩ ስለዘገባ አጠቃላይ ገለጻ ከሰጡ በኋላ በትምህታቸው ላይ ያጋጠማቸውን ነገር በዘገባ መልክ እንዲያቀርቡ ተማሪዎቻቸውን አዘዙ፡፡ ተማሪዎቹም በታዘዙት መሰረት በደብተራቸው ላይ ዘገባ መጻፍ ጀመሩ፡፡ ከቆይታ ጊዜ በኋላ ተማሪዎቹ ሰርተው መጨረሳቸውን ለመምህራቸው ነገሯቸው፡፡መምህሩም ቅድሚያ በፈቃዷ ለምታቀርብ ተማሪ እድል እሰጣለሁ ብለው ሲጠይቁ ተማሪዎች በፈቃደኝነት እጃቸውን እያወጡ ያዘጋጁትን ዘገባ ማቅረብ ጀመሩ፡፡ የጻፉትን ዘገባ ያቀረቡት ተማሪዎች አስር ናቸው፡፡ ተማሪዎቹ ያዘጋጁትን ዘገባ በከፍተኛ ፍላጎትና በመሻማት ነበር፡፡

ክፍል ሁለት፡- ልደታ ማርያም የወንዶች ትምህርት ቤት

ቀረጻ አምስት፡-

ምድብ፡- 9A

ክፍለ ጊዜ፡- 5ኛ

ሰአት፡- 6፡15- 7፡00

ቀን፡- 19/08/2004 ዓ.ም

የተማሪዎች ብዛት፡- 27

መምህሩ እንደተለመደው ወደ ክፍለ ሲገቡ ለተማሪዎቹ ሰላምታ ሰጡ፡፡ ተማሪዎቹም ሰላምታውን መለሱ፤ ከዚያም በጥቁር ሰሌዳው ላይ የቃል ክፍሎች የሚል ርዕስ ጻፉ፡፡ መምህሩ ተማሪዎቹን የቃል ክፍሎች ስንት ናቸው የሚል ጥያቄ በማቅረብ እንዲሳተፉ አዘዙ፡፡

መም- የቃል ክፍሎች ስንት ናቸው?

ወተ$_1$፡- ሶስት

ወተ$_2$፡- ሰባት

ወተ$_3$፡- አምስት

መም፡- የተማሪ ሶስትን ሀሳብ በመደገፍ ‹‹ያንተ ይሻላል›› በማለት አስተያየታቸቸቸውን ሰጡ፡፡

መም፡- እሺ ስማቸውን ልትጠቅሱልኝ ትችላላችሁ

ወተ4፡- ግስ

ወተ 5፡- መስተዋድድ

ወተ 6፡- ስም

ወተ 7፡- ተውላጠ ስም

ሴት 1፡- መስተጻምር

መም- እሺ ተማሪዎች ጥሩ ነው የቃል ክፍሎች በአማርኛ በመጀመሪያው የሰዋስው ጥናት ለስምንት ተከፍለው ነበር፡፡ አሁን በቅርቡ ደግሞ የመስተጻምርን ስራ መስተዋድድ ስለሚሰራ አንድ ላይ መስተዋድድ ተብለዋል፡፡ የተውላጠ ስምን ስራ ስም ስለሚሰራው አንድ ላይ ስም ተብለው ተጠቃለዋል ቃል አጋኖ ደግሞ የቃል ክፍል ውስጥ ስለማይጠቃለል ከቃል ክፍልነት ተወግዶ በጥቅሉ የቃል ክፍሎች በአምስት ተከፍለዋል፡፡

እነሱም፡-

- ስም
- ቅጽል
- ግስ
- ተውሳከ ግስ
- መስተዋድድ ናቸው፡፡

መም፡- ተማሪዎች! እነዚህ የቃል ክፍሎች በእንግሊዝኛ ምን ምን ይባላሉ?

ወተ$_8$ ስም - Noun

ሴት$_2$ ግስ- Verb

ወተ$_9$ ቅፅል- adjective

ወተ$_2$ መስተዋድድ-Conjunction

ሴት$_3$ ተውሳከ ግስ- adverb

መም፡- የእንግሊዝኛው የቃል ክፍል ስምንት ናቸው፡፡ በእንግሊዝኛው የቃላት ክፍሎች Parts of Speech ይባላሉ፡፡

መም፡- ‹‹በመጸሀፋችሁ ‹‹እንዲህም ተኖረ›› ከሚለው ርዕስ ስር አንድ አጠር ያለ የክፍል ስራ አለ፡፡ ስምንና ግስን የሚመለከቱ ስለሆኑ እነሱን በደብተራችሁ ላይ ስሩና እዚሁ ክፍል ውስጥ እንነጋገርባቸዋለን፡፡ ከዛ በፊት ግን የሚከተሉትን ምሳሌዎች ልብ ብላችሁ አዳምጡ፡፡›› ብለው መምህሩ ምሳሌ መስጠት ጀመሩ፡፡

ለምሳሌ፡- ዘቀጠ የሚል ግስ ቢኖረን ዘቀጠ የሚለውን የግስ ቃል ወደ ስም ስንቀይረው ዝቃጭ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዚህ ምሳሌ መሰረት ገጽ 78 ላይ ያሉትን ጥያቄዎች

ስሩና ስትጨርሱ እንነጋገርበታለን በማለት መምህሩ ለተማሪዎቹ የክፍል ስራ ሰጧቸው ተማሪዎቹም ደብተራቸውን አውጥተው የክፍል ስራቸውን መስራት ጀመሩ፡፡

ተማሪዎቹም የተሰጣቸውን የክፍል ስራ ከጨረሱ በኋላ መምህሩ እያንዳንዱን ጥያቄ በቃል በማንበብ ተማሪዎቹን ማሳተፍ ቀጠሉ፡፡

መም፡- ጀርባው ላይ የወጣበት ———————— ፈረጠለት፡፡

ወተ10 ፡ እባጭ

መም፡- ሽንኮራውን ————————በየቦታው አትጣሉ፡፡

ወተ11፡- ልጣጭ

መም፡- የገብሱን ———————— ለላሞች ሰጠቻቸው

ሴት3፡- ውቃጭ

የትኛው - ቃል መረጥሽ

ሴት3፡- ወቀጠ

መም፡- የድስቱን———————— ጠራርጎ በልቶ ሄደ

ወተ12፡- ሙጣጭ

የትኛውን ቃል መረጥክ

ወተ12፡- ሟጠጠ

መም፡- ቅጠሉን ትተህ የእንጨቱን ———————— ማግድ

ወተ13፡- ቁራጭ

መም፡- አይደለም

ወተ14፡- ፍላጭ

መም፡- ከደመና ————————ተጠንቀቁ

ወተ15፡- ግላጭ- ገለጠን መርጨ ግላጭ አዳረኩት፡፡

መም፡- የጠላውን ————————ከምትደፊው ለምን ለከብቶች አትሰጫቸውም?

ሴተ4፡- ዝቃጭ

መም፡- አንድ ስንዝር የሲባጎ ————————ስጠኝ?

ወተ16፡- ጉማጅ

መም፡- ለሲባጎ ጉማጅ ይበላል? ሌላ ተማሪ

ሴተ5፡- ቁራጭ

መም፡- ልብስ ሰፊው የጨርቁን ———————— መለሰልኝ፡፡

ሴተ3፡- ቅዳጅ

መም፡- የትኛውን ቃል መረጥሽ

ሴተ3፡- ቀደደ

መም፡- የግንዱን ———————— ወራጅ ውሀ ወሰደው

ወተ17፡- ጉማጅ

መም፡- የትኛውን ቃል መረጥክ

በህብረት፡- ጎመደ

መምህሩ ከዚህ በኂላ ለተማሪዎቹ ስለቃል መጥበቅና መላላት ገለጻ ሰጡ፡፡ ከዚያም በመጻሀፋቸው ላይ የሚገኙትን ቃላት የመጥበቅና የመላላት ትርጉም እንዲሰጡ አድርገው እንዴት እንደሚሰሩ ምሳሌ ከሰጡ በኂላተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡

መም፡- ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ የፍቺ ልዩነት (ለውጥ) ያመጣሉ፡፡

ለምሳሌ፡- ኮቴ የሚለው ቃል ሲጠብቅ የእግር ድምጽ የሚል ትርጉም የሚሰጥ ሲሆን ሲላላ ደጎሞ የሚለበስ ጨርቅ የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡ በዚህ መሰረት ሁለቱንም ፍቺዎች የሚገልፅ ዐ.ነገር በመስራት እንዲያመለክቱ ትእዛዝ ሰጥተው እየዞሩ ተማሪዎቹን መቆጣጠር ጀመሩ፡፡ ተማሪዎቹ የክፍል ስራቸውን ሰርተው ከጨረሱ በኂላ መምህሩ ጥያቄዎቹን በቃል እያነበቡተማሪዎቹን ማሳተፍ ጀመሩ፡፡

መም፡- ኮቴ በሚለው

ወተ9፡- ሲላላ የኔ ኮት ንፁህ ነው፡፡

ሴተ6፡- ሲጠብቅ የፈረሱ ኮቴ ከሩቅ ይሰማል፡፡

መም፡- በሬ በሚለው

ወተ18፡- ሲላላ በሬው ሰውየውን ወጋው፡፡

ወተ19፡- ሲጠብቅ የትናንትናው ጎርፍ በሬን ገነጠለው፡፡

መም፡- ጠላት በሚል

ወተ20፡- ጠላቴን ገደልኩት፡፡

መም፡- ሲላላ

ወተ14፡- ሰውየው ሴትየዋን ጠላት፡፡

መም፡- ጥሪ በሚል

ወተ21፡- ሲጠብቅ የትምህርት ቤት ጥሪ ሰባት ሰአት ላይ ይደውላል፡፡

ወተ22፡- ሂጂና ሲምራንን ጥሪ፡፡

መም፡- ግቢ በሚለው

ወተ23፡- ቶሎ ብለሽ ወደ ቤትሽ ጊቢ፡፡

ወተ24፡- ሲጠብቅ የእነ አቶ በላቸው ግቢ በጣም ትንሽ ነው፡፡

መም፡- አባይ በሚል

ወተ5፡- ሲላላ እስራኤል አባይ ነው፡፡

ወተ12፡- ሲጠብቅ አባይ ሀገራችን ካሏት ሀብት አንዱ ነው

ክፍለ ጊዜው ተጠናቀቀ፡፡

**ቀረጻ ስድስት፡- ልደታ ማርያም የወንዶች ትምህርት ቤት**

**ምድብ፡-** 9D

**ክፍለ ጊዜ፡-** 7ኛ

**ሰአት፡-** 8፡45- 9፡30

**ቀን፡-** 19/08/2004 ዓ.ም

**የተማሪዎች ባዛት፡-** 24

መምህሩ ወደ ክፍል ከገቡ በኋላ ለተማሪዎቹ ሰላምታ ሰጡ ተማሪዎቹም በተራቸው ሰላምታ ሰጡ፡፡ ከዚያም መምህሩ ጥቁር ሰሌዳውን መሀል ለመሀል በመክፈል ካሰመሩ በኋላ በስተግራ በኩል ቀን ጻፉ፡፡ ከዚያም ‹‹የቃል ክፍል›› የሚል ርዕስ ከጻፉ በኋላ ስለ ቃል ክፍሎች ገለጻ ሰጡ፡፡

መም፡- የቃል ክፍሎች የሚባሉት እነማን ናቸው

ወተ$_1$፡- ስም

ወተ$_2$፡- ግስ

ወተ$_3$፡- ተውላጠ ስም

ወተ$_4$፡- ቅጽል

ሴተ$_1$፡- መስተዋድድ

ወተ$_5$፡- መስተጻምር

ተማሪዎቹ ሌላ የሚያውቁት እንደሌለ ለመምህራቸው ከነገሩ በኋላ መምህሩ የቃል ክፍሎች በቀድሞው ሰዋስው በ8 ተከፍለው እንደነበር፣ በአዲሱ የሰዋስው ክፍል ደግሞ ስምና ተውሳጠ ስም በአንድ ላይ ተጠቃለው ስም መባላቸውንና መስተዋድድና መስተጻምርም በአንድ ላይ ተጠቃለው መስተዋድድ እንደተባሉ አመለከቱ። ቃለ አጋኖ ደግሞ የዲስኩር ቃል እንጂ የቃል ክፍል አይደለም ተብሎ ከቃል ክፍል ስለተለየ የቃል ክፍሎቹ 5 ሆነዋል።

እሰኑም፡-

- ስም
- ቅጽል
- ግስ ተውሳከ ግስ
- መስተዋድድ ናቸው፤ ብለው ገለጻ ሰጡ።

ከዚያም መምህሩ ከመጸሀፋቸው ገጽ 78 ላይ ያሉትን ጥያቄዎች የክፍል ስራ እንዲሰሩ ተማሪዎቹን አዘዟቸው። ተማሪዎቹ የክፍል ስራቸውን ሰርተው እንደጨረሱ መምህሩ ጥያቄዎቹን በቃል እያነበቡ ተማሪዎቹን ማሳተፍ ጀመሩ።

መም፡- ጀርባው ላይ የወጣበት ———— ፈረጠለት።

ወተ6፡- እባጭ

መም፡- የሽንኩራውን ———— በየቦታው አትጣሉ።

ወተ7፡- ልጣጭ

መም፡- የገብሱን ———— ለላሞች ሰጠቻቸው።

ወተ8፡- ወቃጭ

መም፡- የድስቱን ———— ጠራርጎ በልቶ ሄደ።

ወተ9፡- ሙጣጭ

መም፡- ቅጠሉን ትተህ የእጨቱን ———— ማግዱ

ወተ10፡- ግንድ

መም፡- አይደለም

ሴተ2፡- ፍላጭ

መም፡- ከዳመና ——————— ተጠንቀቁ

ወተ11፡-ግላጭ

መም፡- የጠላውን---------- ከምትደፊው ለምን ለከብቶች አትሰጫውም

ወተ12፡- ዝቃጭ

መም፡- አንድ ስንዝር የሲባጎ ---------- ስጠኝ ስጠኝ?

ወተ13፡- ቁራጭ

መም፡-ልብስ ሰፊው የጨርቁን ------- መለሰለኝ

ሰተ3፡- ቅዳጅ

መም፡- የግንዱን ---------- ወራጅ ውሀ ወሰደው

ሴተ3፡- ጉማጅ

መምህሩ ጥያቄዎቹን ካሰሩ በኂላ የቃላት መጥበቅና መላላት የትርጉም ለውጥ እንደሚያመጣ ገልጸውና የቤት ስራ ሰጥተው ክፍለ ጊዜው አለቀ፡፡

**ቀረጻ ሰባት፡- ልደታ ማርያም የወንዶች ትምህርት ቤት**

**ምድብ፡-** 9A

**ክፍለ ጊዜ፡-** 5ኛ

**ሰአት፡-** 6፡15- 7፡00

**ቀን፡-** 26/08/2004 **ዓ.ም**

**የተማሪዎች ባዛት፡-** 27

መምህሩ ሰላምታ ሰጥተው ወደ ክፍል ከገቡ በኂላ ከዚህ ክፍለ ጊዜ በፊት ተምረውት በነበረው የአካባቢ ገለጻ የሚል ርዕስ ላይ ክለሳ ሰጡ፡፡ በጥቁር ሰሌዳው መሀል ላይም የአካባቢ ገለጻ የሚል ርዕስ ጻፉ፡፡

መም፡- ስለ አካባቢ ገለጻ በምንጽፍበት ጊዜ የምናካትታቸው ሀሳቦች ምን ምን ናቸው፡፡

ወተ1፡- ህይወት ያላቸውና የሌላቸውን ነገሮች

ወተ2፡- የእምነት ቦታዎች

ወተ3፡- ባህሎች

ወተ4፡- መንደሮች

ወተ5፡- ቁሳቁና ቁሳዊ ያልሆኑ ነገሮችን

ተማሪዎቹ ያላቸውን ሀሳብ ከሰጡ በኂላ መምህሩ ስለ አካባቢ ገለጻ በተመለከተ አጠቃላይ ገለጻ ሰጥተው ግለ ታሪክ የሚል አዲስ ርዕስ ጀመሩ፡፡ ስለ ግለ ታሪክ አጻጻፍ ገለጻ ከሰጡ በኂላም ተማሪዎቹን መጸሀፋቸውን ገጽ 78 እንዲገልጡ አዘዙ፡፡

መም፡- በፈቃደኝነት የሚያነብ ተማሪ

ሴት፡- ገጽ 75 ላይ ያለውን ግለ ታሪክ የሚል ርዕስ ያለው ምንባብ አነበበች፤ ከምንባቡ አጋማሽ ላይ ስትደርስ መምህሩ ሌላ ተማሪ እንዲያነብ ጥያቄ በማቅረባቸው የተነሳ ወንድ ተማሪ ተቀብሎ ማበብ ጀመረ፡፡ ከዚያም ሌላ ወንድ ተማሪ እንዲያነብ ተደርጎ ምንባቡ ተጠናቀቀ፡፡

ምንባቡ ከተጠናቀቀ በኂላ መምህሩ የክፍል ስራ ተማሪዎቹን ጥያቄ ማጻፍ ጀመሩ፤ ጥያቄውን ካጻፉ በኂላ መምህሩ ጥያቄውን በቃል እያነበቡ ተማሪዎቹ እጃቸውን በማውጣት እንዲመልሱ ማድረግ ጀመሩ፡፡

መም፡- ጸሀፊው በየትኛው ክልል ተወለደ?

ወተ3፡- በደቡብ ክልል

መም፡- ፀሀፊው ትምህርቱን ከስንተኛ ክፍል አቋረጠ?

ወተ6፡- ከአስራ አንደኛ ክፍል

መም፡- ፀሀፊው ሚስት ማግባት ያሰበው በስንት ዓ.ም ነበር?

ወተ7፡- መስከረም 1989 ዓ.ም፡፡

መም- ባለታሪኩ የኤች አይቪ ተሸካሚ ለመሆኑ መገለጫው ምንድን ነው?

ወተ8፡- የተለያዩ የህመም ስሜቶች ስለሚሰሙት፡፡

መም፡- ባለታሪኩ ለኤች አይ ቪ የተጋለጡት ምክንያት ምንድን ነው?

ወተ፡9- የተለያዩ ሱሶችና ልቅ ግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረጉ፡፡

መም፡- ባለታሪኩ ለእናንተ ለተማሪዎች ምን መልዕክት አስተላለፉ?

ወተ10፡- አላስፈላጊ ሱሶች ለኤድስ እንደሚያጋልጡ፡፡

መም፡- የባለታሪኩ የኤች አይቪ ቫይረስ ተሸካሚ መሆን ጉዳት ያደረሰው በእነማን ላይ ነው፡፡

ወተ11፡- በሚስቱ እና በልጁ ላይ፡፡

መም፡- ምንባቡ ከምን ተቀንጭቦ የተወሰደ ነው?

ወተ12፡- የሚናፍቅ ሰውጥ ከተሰኘ መጸሀፍ ላይ ተሻሽሎ የተወሰደ ነው፡፡

መምህሩ ጥያቄዎቹን አስርተው እንደጨረሱ ክፍለ ጊዜው ተጠናቀቀ፡፡

**ቀረጻ ስምንት፡- ልደታ ማርያም የወንዶች ትምህርት ቤት**

**ምድብ፡-** 9D

**ክፍለ ጊዜ፡-** 7ኛ

**ሰአት፡-** 8፡45- 9፡30

**ቀን፡-** 26/08/2004 **ዓ.ም**

**የተማሪዎች ባዛት፡-** 24

መምህሩ ሰላምታ ሰጥተው ወደ ክፍል ከገቡ በኋላ አካባቢ ገለጻ በሚጽፍበት ጊዜ መካተት የሚገባቸው ነገሮች አሉ፡፡ እናንተ ስለአካባቢ ገለጻ ጻፉ ብትባሉ ምን ትጽፋላችሁ ብለው ለተማሪዎቹ ጥያቄ አቀረቡ፡፡

ወተ1፡- ስለምንኖርበት አካባቢ

ሴተ1፡- የምንማርበትን አካባቢ እንገልጻለን

ወተ2፡- ሙሉ ስም

መም፡- ሙሉ ስም ግለ ታሪክ እንጅ አካባቢ ገለጻ ላይ አይገባም፡፡ ሌላ ተማሪ ብለው ለሌላ

ተማሪ እድል ሰጡ፡፡

ወተ3፡- የቤተሰባችንን ታሪክ

መም፡- እሱም ግለ ታሪክ ላይ የሚካተት ነው

ወተ4፡- መንደራችንን

ወተ5፡- አኗኗራችንን

መም፡- የእምነት ቦታዎች ሊጠቀሱ አይችሉም? ብለው ማጠቃለያ ከሰጡ በኋላ ከዚህ ክፍለ ጊዜ በፊት ተምረውት በነበረ ግለታሪክ የሚል ርዕስ ላይ ከጻፉት ማስታወሻ በመነሳት ተማሪዎቹ በግለ ታሪክ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ወይም ሊመለሱ የሚገባቸው ሀሳቦች ምን ምን እንደሆኑ እንዲያስረዱ ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ተማሪዎቹም በየተራ እጃቸውን እያወጡ መሳተፍ ጀመሩ፡፡

ወተ6፡- ሙሉ ስም

ወተ7፡- የትና መቼ እንደተወለደ

መም፡- የመጀመሪያው ጥያቄ ላይ ነው ያለነው የትና መቼ የመጀመሪያው ጥያቄ በሙሉ ከተመለሰ በኋላ የሚቀጠል ነው ከዛ በፊት ያለውን መልሱልኝ?

ሴተ2፡- ለስማችን አወጣጥ ምክንያት የሆነ ነገር

መም፡- አዎ ከዚህ ጋር ግን ተያይዞ የሚነሳ ነገር አለ እሱ ምንድን ነው?

ወተ8፡- ቅጽል ስም ካለ መገለጽ አለበት

መም፡- ቅጽል ስም ማለት ምን ማለት ነው

ሴተ፡- የቤት ስም ወይም ቤተሰቦችህ ብቻ የሚጠሩበት

በመጨረሻም መምህሩ ግለታሪክ ተሟልቶ ተጽፏል የሚባለው ባለፈው በማስታወሻ የጻፋችኋቸውና አሁን እዚህ የዘረዘርናቸውን ነገሮች በሙሉ አካቶ የያዘ እንደሆነ ነው፡፡ በማለት ገለጻ ሰጡ፡፡

ከዚህ ቀጥለው መምህሩ ተማሪዎቹ አማርኛ መማሪያ መጸሀፋቸው ገጽ 75 ላይ ያለውን ታሪክ አውጥተው እንዲያነቡ አዘዙ፡፡

ወንድ ተማሪ በፈቃደኝነት ተነስቶ አነበበ፣ መምህሩ በግማሽ አቋርጠው ለሌላ ወንድ ተማሪ እንዲያነቡ እድል ሰጡ አሁንም በግማሽ አቋርጠው ለሴት ተማሪ እድል ሰጥተው ምንባቡ ተጠናቀቀ፡፡ በዚህም ክፍለ ጊዜው በማለቁ ምንባቡን መሰረት አድርገው የሚሰሩ ጥያቄዎችን የቤት ስራ ሰጥተው ክፍለ ጊዜው አለቀ፡፡

አባሪ ሶስት ፡- የተማሪዎች ጽሁፍ መጠይቅ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የቋንቋዎች ጥናት ተቋም**

**የአማርኛ ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር**

**ለሴት ተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሁፍ መጠይቅ**

የዚህ የጽሁፍ መጠይቅ ዋና አላማ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ሴቶች ብቻቸውን ሲማሩ ያላቸውን የተሳትፎ ሁኔታ ለማወቅ ከተማሪዎች መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡ ስለሆነም ውድ ተማሪ ለዚህ መጠይቅ የምትሰጪው ምላሽ ለጥናቱ መሳካትና ትክክለኛነት ወሳኝ በመሆኑ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና አንብበሽ ትክክል ነው የምትይውን መልስ እንድትሰጪ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ለሚደረግልኝ ትብብርም በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

**አጠቃላይ መረጃ፡-**

የትምህርት ቤቱ ስም፡- ____________________

የክፍል ደረጃ (ሴክሽን)፡- __________________

ዕድሜ፡- ____________________

**መመሪያ አንድ ፡-**

*1. መጠይቁን ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም*

*2. መጠይቁን በጋራ እየተመካከሩ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው፡፡*

**መመሪያ ሁለት ፡-**

**ዝርዝር ጥያቄዎች**

1. በአማርኛ ክፍለ ጊዜ __________________

ሀ. እሳተፋለሁ ለ. አልሳተፍም መ. አልፎ አልፎ

2. ለተራ ቁጥር አንድ ጥያቄ መልስሽ (ለመረጥሽው አማራጭ ) ምክንያትሽ ምን እንደሆነ ግለጭ።

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

______

3. በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በተደጋጋሚ በራስ ተነሳሽነት እጅ በማውጣት ትመልሻለሽ?

ሀ. እመልሳለሁ

ለ. አልመልስም

ሐ. አልፎ አልፎ

4. በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በራስሽ ተነሳሽነት ላልተረዳሽው ሀሳብ ጥያቄ ታቀርቢያለሽ

ሀ. እጠይቃለሁ

ለ. አልጠይቅም

ሐ. አልፎ አልፎ

5. በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የተሳሳተ መልስ ስትመልሺ ትፈሪያለሽ;

ሀ. እፈራለሁ ለ. አልፈራም

6. ለተራ ቁጥር አምስት ጥያቄ መልስ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ግለጭ።

________________________________________

________________________________________

7. የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ በክፍል ውስጥ የሁሉንም ተማሪዎች ስም በመጥራት እንድትሳተፉ ያደርጋሉ?

ሀ. ያደርጋሉ

ለ. አያደርጉም

ሐ. አልፎ አልፎ

8. የአማርኛ መምህራችሁ የተሳሳተ ምላሽ በምትሰጪበት ጊዜ ምን አይነት ምላሽ ይሰጡሻል?

   ሀ. በድጋሚ እድትሞክሪ ማበረታታት

   ለ. ድጋሚ እንድትሞክሪ እድል አለመስጠት

9. የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ተማሪዎች በሚሳተፉበት ጊዜ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ተሳትፎው እንዲቀንስ ያደርጋሉ?

   ሀ. ያደርጋሉ

   ለ. አያደርጉም

   ሐ. አልፎ አልፎ

10. ለተራ ቁጥር ስምንት ጥያቄ መልስሽ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ግለጭ፡፡

___________________________________________

___________________________________________

አባሪ አራት፡- የመምህራን ቃለ መጠይቅ

**ክፍል አንድ፡-** ሴቶች ብቻቸውን በሚማሩበት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፡፡

- **የመልስ ሰጪው አጠቃላይ መረጃ**

የትምህርቱ ቤቱ ስም፡- ልደታ ማርያም ልጃገረዶ ትምህርት ቤት

የትምህርት ደረጃ፡- በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ የመጀመሪያ ዲግሪ (ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)

ፆታ፡- ወንድ

ዕድሜ፡- 57

- **ዝርዝር ጥያቄዎች**

**ጥያቄ፡-** በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ሴት ተማሪዎች ይሳተፋሉ? ለመለሱት መልስ ምክንያትዎን ቢገልጹልኝ?

**መልስ፡-**አዎ ይሳተፋሉ፡፡ ምክንያቱም ከእኔ ጋር ያላቸው ግንኙነት በጣም ጥሩ ስለሆነና የፈለጉትን ቢናገሩ የሚቆጣቸው ስለሌለ በዚህ ምክንያትም በደስታ ይሳተፋሉ፡፡

**ጥያቄ፡-**ሴት ተማሪዎች ለጥያቄዎች መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ማበረታቻ ይሰጣሉ? ለመለሱት መልስ ምክንያትዎን ቢገልጹልኝ?

**መልስ፡-** አዎ በራሳቸው ተነሳሽነት ይጠይቃሉ፡፡ ምክንያቱም በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ከመምህሩ ጋር ያላቸው ቀረቤታ ነጻ ስለሆነና ምንም አይነት ፍርሀት ስለሌለባቸው በራሳቸው ተነሳሽነት ጥያቄ ይጠይቃሉ፡፡ ምን አልባት በሳምንት ውስጥ ያለው ክፍለ ጊዜ ሁለት በመሆኑ የክፍለ ጊዜው ማነስ ያግዳቸው እንደሆነ ነው እንጂ ያልገባቸው ነገር ከመጠየቅ ወደኋላ አይሉም፡፡

**ጥያቄ፡-**ሴት ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁና አስተያየት እንዲሰጡ ያደርጋሉ? ለመለሱት መልስ ምክንያትዎን ቢገልጹልኝ?

**መልስ፡-**ሴት ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ በጣም ግፊት አደርጋለሁ፡፡ የማይናገሩትን ተማሪዎች በተለየ መልኩ ለማበረታታት ጥረት አደርጋለሁ፡፡ የሚናገሩትን ምን ጊዜም ቢሆን መናገራቸው ስለማይቀር የማይናገሩትን ተማሪዎች ማበረታታት ላይ አተኩራለሁ፡፡ ይህን እንዳደርግ ያነሳሳኝ ምክንያት ደግሞ ትምህርት ቤት ሀሳባቸውን መግለጽ የማይችሉ ተማሪዎች በወደፊት ህይወታቸውም ቢሆን የሚሰማቸውን ነገር ለመግለፅ አይችሉም፤ ስለዚህ ይህን መለማመድ ያለባቸው እዚሁ ትምህርት ቤት ስለሆነ እንዲበረታቱና እንዲናገሩ ስለሚፈለግ ነው፡፡ ከትምህርት ቤት ይህን ዝምታ ይዘው ከወጡ ግን ለወደፊት ህይወታቸው በጣም አስቸጋሪ ይሆናል ብየ ስለማስብ ነው፡፡

**ጥያቄ፡-**ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መልስ በሚመልሱበት ጊዜም ሆነ ጥያቄ በሚጠይቁበት ጊዜ ይፈራሉ? ለመለሱት መልስ ምክንያትዎን ቢገልጹልኝ?

**መልስ፡-**አዎ ይፈራሉ ይህ ያለ ነገር ነው፡፡ተማሪዎቹ ብዙ ጊዜ ትክክለኛ ንግግር ቢናገሩ እንኳን ተሳስቼ ይሆን? የሚል ፍራቻ አለባቸው፡፡ እነዚህን የሚፈሩ ልጆች እንዲናገሩ የማደርገው በማደፋፈርና ቢሳሳቱ እንኳን እንዳልተሳሳቱ አድርገው ራሳቸውን እንዲገልጹ በማድረግ ነው፡፡ ከሰው ፊት ደፍሮ ለመናገር ብሳሳትስ የሚለው ሀሳብ ማህበረሰቡ ለሴቶች የሚሰጠውን ግምት ከቤተሰቦቻቸው ይዘው ስለሚመጡ በትምህርት ቤት ለመናገርም ፍራቻ ያድርባቸዋል፡፡

**ጥያቄ፡-**የማህበረሰቡ ተጽዕኖ በሴቶ ተሳትፎ ላይ ተጽዕኖ የሚያመጣው እንዴት ነው ብለው ያስባሉ?

> *መም፡-* ሴት ልጅ እንደዚህ አትናገርም፣ ሴት ልጅ እንደዚህ አታደርግም … ወዘተ የሚለውን አስተሳሰብ እየሰሙ ስለሚያድጉ ይህ ነገር እንደ ልማድ ይሆንና በትምህርት ቤት ተሳትፏቸው ላይ ተጽእኖ ያመጣል፡፡ አሁን ያለው ትውልድ ግን ይህንን አስተሳሰብ እየጣሰው የመጣ ይመስላል፡፡ ነገር ግን አሁንም በመጠኑ ተጽእኖው እንዳለ ግልጽ ነው፡፡

**ጥያቄ፡-**በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ በተደጋጋሚ እድል የሚሰጡት ለምን አይነት ተማሪዎች ነው? ለመለሱት መልስ ምክንያቱ ምን ይመስለዎታል?

**መልስ፡-**ለሁሉም እድል እሰጣለሁ፤ ነገር ግን እጃቸውን ለሚያወጡት ቅድሚያ እሰጣለሁ አልከለከላቸውም፡፡ ግን ደጋግመው ደጋግመው የሚያወጡትን እተውና አይናፋር ለሆኑ ልጆች ተነስተው እንዲሞከሩ አድርጋለሁ፡፡
**ጥያቄ፡-**በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሴት ተማሪዎች የተሳሳተ ምላሽ ሲሰጡ ምን ያደርጋሉ? ለመለሱት መልስ ምክንያቱ ምን ይመስለዎታል?

**መልስ፡-** እኔ እምፈልገው እንዲሳሳቱ ነው፡፡ እየተሳሳቱ ደግሞ ከስተታቸው እንዲማሩ ነው፡፡ ምክንያቱም ሲሳሳቱ ተሳስተሻል ካልኩሽ ለወደፊቱ አትናገሪ ማለት ነው ስለዚህ ቢሳሳቱ እያረምኩ እያስተካከልኩ እንዲበረታቱና እንዲናገሩ አደርጋለሁ፡፡ይህን የማደርገው ተሳሳትን ብለው ፍራት እንዳይዛቸውና በንግግር መካከል ወደፊትም ቢሆን ስህተት እንዳለ እንዲያውቁና በንግግር እንዲያርሙት ስለምፈልግ ነው፡፡
**ጥያቄ፡-**ሴት ተማሪዎች ለጥያቄዎች መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ማበረታቻ ይሰጣሉ? ለመለሱት መልስ ምክንያትዎን ቢገልጹልን?

**መልስ፡-** አዎ አበረታታለሁ- በጣም ጥሩ፣ እጅግ በጣም ጥሩ፣ ጎበዝ ነሽ፣ ይህ ሀሳብ ተደብቆ እንዳይቀር አውጭው....ወዘተ. እያልኩ አበረታታቸዋለሁ፡፡ አንዳንድ ሴት ተማሪዎች ካሰብኩት በላይ (ያላሰብኩትን) ሀሳብ የሚናገሩም አሉ፡፡ እንደዚህ በሚያደርጉበት ጊዜ ከጠበኩት በላይ ስለሚያቀርቡ ይህን ነገር ባትናገሪ ኖሮ ተደብቆ ይቀር ነበር አሁን ስለተናገርሽው ወጣ በርቺና ቀጥይ እያልኩ አበረታታቸዋለሁ፡፡ መልሱን እያወቁ መናገር ያቃታቸውን ተማሪዎች ከራሳቸው ልምድ በመነሳት ተማሪዎቹ እንዲናገሩም አደርጋለሁ
**ጥያቄ፡-**ሴት ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁና አስተያየት እንዲሰጡ ያደርጋሉ? ለመለሱት መልስ ምክንያትዎን ቢገልጹልኝ?

**መልስ፡-** አዎ አደርጋለሁ፡፡ የራሳቸውን አስተያየት ሳይፈሩ ሳይጨነቁ እንዲሰጡ አደርጋለሁ፡፡ ሌሎች ጓደኞቻቸው እንኳን ቢስቁባቸው እነኛን የሚስቁባቸውን ልጆች እቆጣቸዋለሁ፤ ቢሳሳቱም የፈለጉን ይናገሩ ምንም አትበሏቸው እላለሁ፡፡ በገለጻ ሰአትም ብዙ ውይይት እንዲያካሂዱ አድርጋለሁ፡፡
**ጥያቄ፡-**ከዚህ በፊት ሴትና ወንድ ተማሪዎች በሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ አስተምረው ያውቃሉ? መልስዎ አወ ከሆነ ልዩነቶቹን ቢገልጹልን?

**መልስ፡-** እድሜ ልኬን በሙሉ ሴትና ወንድ ተማሪዎች በሚማሩበት ትምህርት ነው ሳስተምር የኖርኩት እዚህ ትምህርት ቤት ማስተማር ከጀመርኩ ሁለተኛ አመቴ ነው፡፡ እዛ ያሉት ከመጀመሪያው ጀምሮ ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው ስለሚማሩ ሀሳባቸውን ያለምንም ፍርሀት ይገልጻሉ፤ ነገር ግን እዚህ የሚማሩ ተማሪዎች ለወደፊት ወንድ ተማሪዎች ጋር በሚማሩበት ጊዜ ችግር ያጋጥማቸው ይሆና ብሎ አስባለሁ፤ እዛ ያሉት ተማሪዎች መተፋፈር የሚባል ነገር የለባቸውም፤ በውጭም ሆነ በክፍል ውስጥ ባለው ነገር ሀሳባቸውን ከወንዶች እኩል መግለጽ ይችላሉ፡፡ እርግጥ ነው እዚህ ያሉት ሴቶች ብቻ ስለሆኑ ሴት ለሴት አይተፋፈሩም፡፡ ግን ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው ሲማሩ ችግር ሊገጥማቸው (ሊፈሩ) ይችላሉ፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት ያሉ ተማሪዎች ጎበዞች ናቸው፡፡ የዚህም ምክንያቱ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ስለሆኑ በቤትም ሆነ በትምህርት ቤት ቁጥጥር ስለሚደረግላቸው ይመስለኛል፡፡ የክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራቸውን ሳይዘናጉ ሰርተው ይመጣሉ፡፡ ባጠቃላይ በዚህ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ጥሩ ተሳትፎ ያደርገሉ፡፡ የተሳትፎ ልዩነት እንዲኖር ያደረገው ግን ተለያይተው መማራቸው ሳይሆን የቤተሰባቸው ቁጥጥርና የሚማሩበት ትምህርት ቤቱ ትምህርት አሰጣጥ እንጂ ተለያይተው መማራቸው ሳይሆን የተማሪዎቹ የቤተሰብ ሁኔታና የትምህርት ቤቱ የትምህርት አሰጣጥ ነው፡፡

**ጠያቂ፡-** ጥያቄዎቼን ጨርሻለሁ፤ ስለተሰጠኝ ገለጻ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

**መላሽ፡-** ምንም አይደል፡፡

**ክፍል ሁለት፡-** ሴቶችና ወንዶች አብረው በሚማሩበት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፡፡

- **የመልስ ሰጪው አጠቃላይ መረጃ**

የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም፡- ልደታ ማርያም ወንዶች ትምህርት ቤት

የትምህርት ደረጃ፡- በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ የመጀመሪያ ዲግሪ (ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)

ፆታ፡- ወንድ

ዕድሜ፡- 60

- **ዝርዝር ጥያቄዎች**

**ጥያቄ፡-**በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ሴት ተማሪዎች ይሳተፋሉ? ለመለሱት መልስ ምክንያትዎን ቢገልጹልን?

**መልስ፡-**አዎ ይሳተፋሉ፡፡ ሴት ተማሪዎች በግል ትምህርት ቤትም ሆነ በመንግስት ትምህርት ቤት ከወንዶች የበለጠ ተሳታፊ ናቸው፡፡ ውጤታቸውም ይህንኑ ይመሰክራል፡፡ ወንዶቹ ጊዜያቸውን ለቋንቋ ትምህርት ስለማይሰጡና የክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ ስለማይሰሩ በክፍል ውስጥ ለመሳተፍ ያላቸው ፍላጎት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ሴት ተማሪዎች በክፍል ትዕዛዝ ይቀበላሉ፣ ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎትም ከፍተኛ ነው፣ የሚሰጣቸውን የቤት ስራዎች በሙሉ ሰርተውና ተዘጋጅተው ስለሚመጡ በክፍል ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡

**ጥያቄ፡-**በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ሴት ተማሪዎች ለሚጠየቁት ጥያቄዎች በራሳቸው ፍላጎት እጃቸውን በማውጣት ይሳተፋሉ? ለመለሱት መልስ ምክንያትዎን ቢገልጹልኝ?

**መልስ፡-** እንደገለጽኩት ሴት ተማሪዎች በክፍል ትዕዛዝ ይቀበላሉ፣ ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎትም ከፍተኛ ነው፣ የሚሰጣቸውን የቤት ስራዎች በሙሉ ሰርተውና ተዘጋጅተው ይመጣሉ፡፡ ይህን የሰሩትን የቤት ስራና የክፍል ስራ ለመመለስ እጃቸውን በራሳቸው ፍላጎት ያወጣሉ፡፡

**ጥያቄ፡-**ሴት ተማሪዎች ለጥያቄዎች መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ማበረታቻ ይሰጣሉ? ለመለሱት መልስ ምክንያትዎን ቢገልጹልኝ?

**መልስ፡-**አዎ እሰጣለሁ፡፡ ጠበቅ ያለ ጥያቄ ከሰጠሁ እንዲጨብጨብላቸው አደርጋለሁ፡፡

**ጥያቄ፡-**ሴት ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁና አስተያየት እንዲሰጡ ያደርጋሉ? ለመለሱት መልስ ምክንያትዎን ቢገልጹልኝ?

**መልስ፡-**ከጥያቄዎቹ መሀል በስፋት መመለስ የሚፈልጉ ጥያቄዎችና ሰፊ ማብራሪያና አስተያየት የሚፈልጉ ጥያቄዎች ሲኖሩ እንዲመልሱ እሚያስቡበት ጊዜ ጭምር እሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ በጣም ተሳታፊቹ ሴቶቹ ናቸው፡፡

**ጥያቄ፡-**ሴት ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁና አስተያየት እንዲሰጡ ያደርጋሉ? ለመለሱት መልስ ምክንያትዎን ቢገልጹልኝ?

**መልስ፡-**ሴት ተማሪዎች ከቤታቸው ተዘጋጅተው ስለሚመጡ የሚመልሱት መልስ ግልጽና የተብራራ ነው፡፡ አጭር መልስ የመለሱትን ልጆችና የተብራራ መልስ የመለሱትን ልጆች ነጥየ ራሳቸዋለሁ አጭር መልስ የመለሱትን ልጆች ረጅምና የተብራራ መልስ የመለሱ ልጆች ጋር መልሳቸውን እንዲያስተያዩና የጎዳላቸውን ነገር አውቀው ድጋሚ የተብራራ መልስ እንዲመልሱ አድርጋለሁ፡፡

**ጥያቄ፡-**ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ጥያቄ በሚጠይቁበት ወይም መልስ በሚመልሱበት ጊዜ ይፈራሉ? ለመለሱት መልስ ምክንያቱ ምን ይመስለዎታል?

**መልስ፡-** አዎ ይፈራሉ ይህ ያለ ነገር ነው፡፡ የተወሰኑ ተማሪዎች ይፈራሉ፤ አንዳንዶቹ ግን ከወንዶች የተሻለ ግልጽና የተብራራ መለስ የሚሰጡት ራሳቸወ ሴት ተማሪዎች በመሆናቸው በመሆናቸው መልስ ሲመልሱም በችሎታቸው ስለሚተማመኑ ብዙም አይፈሩም፡፡ ቢሆንም ግን ሲጨብጨብላቸው እንኳን ይፈራሉ፡፡ ወንድ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በሴት ተማሪዎች መልስ ላይ እንዲስቁም ሆነ እንዲያሾፉ ስለማይፈቀድላቸው አያሾፉም አይስቁም፡፡ ይሄ የግል ትምህርት ቤት እንደመሆኑ አንዳንድ ከስርአት የወጡ ተማሪዎች በሚኖረበት ጊዜ እንዲህ አይነት ነገር ይከሰት እንደሆነ ነው እንጂ በጭራሽ እንደዚህ አይነት ነገር እንዲፈጽሙ እንፈቅድላቸውም ሴት ተማሪዎቹም ቢሆኑ ይህን ነገር አይፈሩም(ከቁብ አይቆጥሩትም) የሳቁ ሁኔታ ከመንግስት ትምህርት ቤት ይልቅ በመጠኑም ቢሆን እዚህ የግል ትምህርት ቤት ይታያል፡፡

**ጥያቄ፡-**በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ በተደጋጋሚ እድል የሚሰጡት ለየትኞቹ ተማሪዎች ነው? ለሴቶች ወይስ ለወንዶች? ለመለሱት መልስ ምክንያትዎን ቢገልጹልኝ?

**መልስ፡-**ቀድሞ እጁን ያነሳ ወንድም ሆነ ሴት እድሉን ያገኛል፡፡ ነገር ግን ወንድና ሴት በአንድ ላይ እጃቸውን ካወጡ ቅድሚያ ለሴቷ ተማሪ እድል እሰጣለሁ፡፡

**ጥያቄ፡-** እጃቸውን ሳለወጡ ሴት ተማሪዎችስ እድል ይሰጣሉ?

**መልስ፡-** አዎ እሰጣለሁ፡፡ ድንገተኛ ጥያቄ በማቅረብ እንዲሳተፉ አድረጋለሁ፡፡

**ጥያቄ፡-**በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሴት ተማሪዎች የተሳሳተ ምላሽ ሲሰጡ ምን ያደርጋሉ?

**መልስ፡-** በቋንቋ ትምህርት ተሳስተሀል/ሻል ስለማይባል መሳሳታቸውን አልነግራቸውም፡፡ የተመለሱትን መልሶች በሙሉ ጥቁር ሰሌዳው ላይ እጽፍና ተማሪዎቹ እንዲወያዩባቸው አደርጋለሁ፤ ከዛ በኋላ የተሳሳተ መልስ የመለሰችው ልጅ ማስተካከያ እንድታደርግ ሴት ከሆነች ቅድሚያ እድል እሰጣለሁ፡፡ ተማሪዎች ሲሳሳቱ መሳሳታቸው ከተነገራቸው ነገ ድጋሚ አይሞክሩም ስለዚህ መደረግ ያለበት ከስህተታቸው እንዲማሩና ስህተታቸውን እንዲያርሙ ስለሆነ መሳሳታቸውን አልነግራቸውም ድጋሚ እንዲያስተካክሉ ግን አደርጋለሁ፡፡ ሌላው ባህላችን አስቸጋሪ ነው ጥሩ ነገር ሲደረግ ከማበረታታት ይልቅ ስህተት ሲሰራ ማሳቅ ላይ እንበረታተለን፡፡ ስህተት መስራቱን የሚያውቁ ልጆች ሊስቁ ይችላሉ፤ ነገር ግን ተማሪዋ እንዳትጎዳ መምህሩ ሌሎቹን በመገሰጽ መልሱን እስከምታሰብ ድረስ ወደ ሌላ ስራ በመግባት ድጋሚ እንድትሞክር ይደረጋል፡፡ ልጆቹ ግን የተሳሳተ ምላሽ በሚመለስበት ጊዜ ይሰቃሉ፡፡

**ጥያቄ፡-**ከዚህ በፊት ሴቶች ብቻ የሚመማሩበት ትምህርት ቤት አስተምረው ያውቃሉ?

**መልስ፡-**በፍጹም አላውቅም፡፡

**ጠያቂ፡-** ጥያቄዎቼን ምልሻለሁ ስለተደረግልኝ ትብብር በጣም አመሰግናለሁ፡፡

**መላሽ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ማረጋገጫ

አኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለፀው፣ ይህ ጥናት የራሴ ስራ መሆኑን እንዲሁም በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ፅሑፎችና ምንጮች በሙሉ የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- ለዘር አሌ

ፊርማ፡- ___________

አድራሻ- በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሂዩማኒቲስ፣

የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ቀን፡- ሰኔ 2004 ዓ.ም